
P.①h7-101



Meysor Bro
t.me/BooksandYou

ሰ፡ ሕጎች መንግሥት ይሆር የሥልጣን ግዕዜ ሆኖ የኖረችው ሕጉ ነዉ ። ሕጎ ማኅበራዊ እንቅስቃሴ ፡ ከአዲሱ የአዎዩ ርእዮት ሥርዓት ጠቋሚ ፡ በረሃ

እያወሳወዙ በእጠባቸው ያለፉትን ካህን በዐይንዋ እያመለከተች ፣ ከኋላቸው ሁለት ደቀ መዛሙርት ይከተሉዋቸዋል ።

“ አንድ ቄስ ናቸዋ ! ” ገብርዬ በማታለል ፈገግታ መለሰላት ።

“ አታውቃቸውም ? ”

“ የጉንደርን ቄስ ሁላ የታውቀዋለሁ ብለሽኝ ! ”

“ እሪ እኘህ ትልቅ ናቸው ! ” አለች ላለመረታት ።

“ ግዴለሽም እየቆየሽ ታይዋለሽ ። ”

“ እሪ እንተዬ ” ብላ ሳትጨርስ ተወችው ። የሐር ጥላ አሲዛ በሠጋር ግራጫ በቅሎ የምትፈስሰውን እንዲት ወይዘሮ በእድናቆት ዐይንዋን ትክል አድርጋ ትመለከታለች ።

“ ምነው ? ”

“ ያች ወይዘሮ ማናት አንተዬ ? ”

“ የጉንደር ሴት ? ”

“ ማለ — ማለቴ የማን ምሽት ናት ? ”

“ የታባቴን ዐውቃታለሁ ብለሽኝ ? ”

“ እህ — ጉንደር ተቀምጫለሁ ትላለህ እንጂ እንደኔው ባላገር ነህ ። አንጹንም ሰው አታውቀው ” አለችው በቀልድ ሽጉጥጫ ።

“ ምን አታከረሽ ። ይሽኔ ኮማሪት ትሆናለች ።”

“ እንደዚህ ያለችው ? ” ማመን አቃታት ፤ ‘ ዛዲያ ባሎቻችን እንዚህን እያዩ ’ የሚል የፍራቻ ሐሳብ ውልብ አለባት ።

ማረፊያ ቤታቸውም ቢሆን ፣ በመጀመሪያ እንደ ቤተ ክርስቲያን አስፈርቷት ነበር ። ከአጣጣሚ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ግቢና የግንቡን ጥግ ይዞ የተሠራ ደርብና ምድር ቤት ነው ። ከአካባቢዎቹ ሕንፃዎች ጋር ሲነጻጸር እስከዚህም ትልቅ አይደለም ። ደርቡ ሰፋ ያለ አዳራሽ ፣ መለስ ተኛ አልፍኝ ፣ በሁለት በኩል አነስ አነስ ያሉ ሁለት ጓዳዎች ፣ ከወደኋላው ለብቻ ማድቤትና የዕቃ ቤቶች አሉት ። ዱሮ የደጃዝማች ወንድይራድ የነበረው ይህ ቤት ፣ ራስ ዐሊ ከነመኳንንታቸውና ከነሠራዊታቸው ጎንደርን ለቀው ከሸሹ በኋላ ወና ሆኖ ቆይቷል ።

“ ይሽን ሁሉ ምን ልናረገው ነው ? ” ስትል ጠየቀች ፣ ገብርዬ አስገብቶ እንዳሳያት ። ዕቃ የሌለበት አዳራሽ ከትልቅ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት የሰፋ መስሎ ታያት ። “ ልጅ የለን ውላጅ የለን ” አለች በቅሬታ መልክ ።

“ እንግዲህ መቸስ የቋራ ጎጆ ይዘን አንመጣ ። እንደሚሆን አሚሙ ቂው እንጂ ፣ እንግዳም መምጣቱ እይቀር ። እግዚአብሔር ታለ ደሞ ! ”

ታንጉት ልጅ አለመውለድዋ ሁልጊዜ እንደሚያሳስባት ስለሚያውቅ ከፈገግታ ጋር በማባበል የጉንጩዋን ስርጉዳት በጣቱ ጠት አደረጋት ።

እንዳለውም ቤቱ ዕቃ ሲገባበት ፣ እሳት ሲጫርበት በብሰብ ያለ መሰለ ። ታንጉትም ቤት ማሰናዳቱ ፣ ምግብ ማዘጋጀቱ ጊዜ እያሳሰፈላት ፣ ፍርሃት ፍርሃት ማለቱ ተዋት ። ወደ መጀመሪያ ገደማ እናዲሰ ዕንግዳ ግን ወደ ቤታቸው አልመጣም ። ቤተ ክርስቲያን ስትሔድ ፣ ገበያ ሲጠ ፣ በቤተ መንግሥት አካባቢ ስትገኝ የሚያጋጥሟት እነዚያ የተሽ ሞንሞኑ የጉንደር ወይዛዝርት ፣ የተኩፈሱ መኳንንት ሰውነ ያህል እን ገት ቀልበስ አድርገው በሩት ፣ ‘ ጤና ይስጥልን ! እንደምን አደራችሁ ? እንደምን ዋላችሁ ? ’ ከማለት በተቀር አልቀረቧትም ። ጉንደሮች ግን ምን እንደሆነ እስኪያውቁ ድረስ ገና እየፈተሹ እርስ በርሳቸው እየተጠ ያየቁና እያጠያየቁ ነበሩ ። የዘመነ መሳፍንት የሥልጣን ክዚህም ክዚ ያም መንተት ብዙ አስተምሯቸዋል ። ‘አይተህ ነው ጊዜ ወዳደላበት’ እን ዲሉ ፣ እንዲያው ለመወዳጀት ሲባል ብቻ ዘው ተብሎ ዕውቂያ አይደረ ግም ። በዚህ ላይ የመግደርደሩም ልማድ አለ ። አንዳንድ ቀን ወደ ግቃ ቤታቸው የሚመጡት የገብርዬ ጦር አበጋዞችና ታንጉት ቀደም ሲል የምታውቃቸው ሚስቶቻቸው ብቻ ነበሩ ።

ዐልፎ ዐልፎ ቴዎድሮስ ይመጣሉ ። መስተንግዶውም ፣ ጭውው ቱም ከወትሮው የተለየ አይደለም ። ስለ ወደፊቱ ዘመቻ ያወጋሉ ፤ ይመ ክክራሉ ፤ ይከራከራሉ ፤ በመካከሉ ያለፈ ትዝታ ያወሳሉ ። ቀልድ ወይም ተረብ ቢጤ ጣል ጣል የሚያደርግም አለ ። አብዛኛዉ ግን ፣ ቁም ነገር ብቻ ነው ። ቴዎድሮስ ስለ ዘመቻ በሚያወጉበት ጊዜ ዐይናቸው እንደ ጢፍ የሚበሩ ፣ ግድግዳውን ዐልፈው አድማስ የሚመለከቱ ይመስላሉ ።

በእንደዚህ ጊዜ ታንጉት ፣ አድናቆት አይሉት አዘኔታ አንዳች ዐይነት ስሜት ገረፍ ያደርጋታል ። ከሕፃንነቷ ጀምሮ አብራቸው ኑራ ለች ። አሳድገው ለገብርዬ ድረዋታል ። ግን ስለ እርሳቸው ያላት ስሜት ዐልፎ ዐልፎ ግራ ያጋባታል ።

ሴቶቹ ፣ ለብቻቸው ወደ አንድ ጥግ ሆነው ዝም ብለው ከማዳመጥ ወይም እርስ በርሳቸው የባጥ የቆጡን ከመንሾካሾክ በተቀር በወንዶቹ ጭውውት አይገቡም ።

እንድ ቀን እንደዚሁ ራት ተበልቶ ሲጨዋወቱ ለማቆላመጥ ባወ ጡላት ስም ፣ “ አንጓች ? ” ሲሉ ጠሯት ። በዚህ ስም ሊጠሯት መጀመ ሪያ ያወጡላት ቀን ብዙ ጊዜ ትዝ ይላታል ። በወይኒ መንደር እናቷ ታማ ቤት ከዋለች በኋላ ነው ። ያን ጊዜ ስሙን ባታውቀውም የበፊቱ ክማ ፣ የአሁኑ ቴዎድሮስ ከአንድ ሦስት ሰዎች ጋር ቤታቸው ይመጣል ። ዕጅ ተቀምጣ ትጫወት ነበር ። ‘ ነይ ላሚኝ አንቺ ’ ሲል ይስማትና ቤት ይገባል ። ከእናትዋ ጋር ረዘም ያለ ጊዜ ቆይቶ ሲወጣ ፣ ከምትጫወ

ትዕት ቆርጠዋ ዓይኑ ያቀመጣና ንጉሥዋን እያፍጠጠ ፡ " ሰምተ ማነው የኔ ደማም ? " ብል ያጠይቃቃል ፡ ትንባሪቃሪት = " እሷ ያው አንጎሳ ነው የምልሽ " ! አንዱን ሰውዬ እንዲሰውሙ ያዘዋል = ከዚያም ንጉ ቆጵውን በተሚሰዋ ሜና እያሰያቸ ፡ " ሴታንቲ ንጉ ታንጉትሰግሰኝ ፡ እቺ ! " አሉትና ጨደ =

" እጪት ! አለ ታውቅ " እሰት ታንጉት ከትዝታዋ ስትመለስ =

" ጉንጉርን ተቀመጪዉ ? "

" ኧረ እሷ እንጂ ! " እሰት የምትመልሰው ግራ ተጋጠቻት =

" እይዞሽ ትወምጅዋለሽ = ጉንጉርኮ እውሩም ያለለምንም = ግን ዋ ! ዋ ! እንሰን እንንትመሰይ ! ወንም ደሞ ወዲ ዋናር እንጉንጠመምኒ ! ንሰ ነግሬሻለሁ " አሏት በቀልድ ግቢዉሬራት =

" እኛ ምንደን ነን አለ ታውቅ ! " ብሎል የአንገሀ ምሬት ከሆን ጠየቀች = እንንሰን ከምገኝት በፊት ጉንጉር ተወልዳ ያደገች የመነ ንጉት ዙር ነበረች =

" ኧረኝ ! " አሉ ቴዎድሮስ የነገሰው መሰለው እየጉቱ = ሊሉኝም ጣቴ = " እንዳና ተቀበትጣ እንጎ መሰለችንል ፡ አጠምቀናችሁ ! "

እንጨንገሬ እንጨንገ: ቀሪይ ነበረውት በጋል ፡ ያስቃሉትና የተረሳ ይመሰል ሞውውንቱው ወደ ቁም ነገሩ ተመለሰ = ጀጋግ አለነሥትም =

ታንጉት ግን ወለዋታዉ ፡ ቀነም ከወለፈ በጋለ እንጨንጨት ግርት = እንጉ መግር ጉንጨት ቢሰሰነው መጎሳቆሉ አይቀሪም ፡ " ምን እንጨንጉ ርኩሳ ነው ? ምን እንጨለጀርግ ነው ! መጀለ ምን እንጨልውግ ነው ! " ብሎት ሥራዉን ሊታሸሸውን ጎያቂውን ዘረፈዉ ቢሰነሰነዉ መጀታ መሬ ሄንጉ ታሰለሰለት ፡ እጀመጫትም = ግን ግጉንጉር ወጀጠጠት ፡ መነጉን ትና ካወጉት በጀንጉት ሊጀጋግት እንጉት ዐጀነት ሰሚት ጀጉርሰል = ግላጀም አትለውም ፡ ሩቁብርም አትለውም ፡ እየቀሊሉት መጠጋት = እየዘረፉትው ገፈው የግውት ዐጀነት ሩሀጉታ ነው = ሊታሩሀለው ፡ እንጉርም ጀጀሀነት ዘጉሀሀውለው ዘሰለበሰት = በዘት ሥራዉ በግተጉሩ ዉሀርሰ ልትሀነውም ሞክረዘት = እንንጨጀ ነውን ረጉሳ ፡ እንንጨጀ ነውን ሀነት ዐጀነት ሰዘት ወተና አጀውትም = ሰበጀ ግጉንጉር ወጀጠ ዝርት መግዉ የንሰርዜ ሰሰጀ ፡ ዘንዶጀም ያለው ሰግት ያጠወሰ ያግሪ እንጉጀ የተደመጠ ሆኖ አልተሰማትም =

መቀል ግንጉር መጉም መሬነም ነውና ቀነት ቢያልፉ ፡ ጊዜዉን በወነውም ባልወነውም ሥራ ዘታሳልፍና ፡ ሐሰጎ, ጀሰሰዘ ግሰት ሰጀጀ ሥር ፡ መሊ ጉንጉደርን ሰመሬ ያተርመሰው የሹም ዝር ነገር መጣ =

ቴዎድርስ ፡ ብዙ ጊዜ በውጭ ችሎት ሳያቶመው ከውሰጥ ብቻዎ ውን ፡ እንጨንጉ ጊዜም ከበል ጋር እየዋሉ መሰናበታቸውን ታንጉት

ዐት መንግሥት ሰዋሐይ ዛንጨቀውም በከተማው የሚሰሰመውን ወሬ ያጀታመሳት ፡ ከነሱባይው የመን መሰሰን ጋር በተያያዘ የሚሰሰመው ጀጀ መሰሰውን እንሩተጉትና ወደንጉን እያጨሰሰውት የነበሰውትውን ወሬ ትንባሪትት =

—3—

ጉንጉር በወሬን በተንጀቆሰ ሊታመስ ሰንጨንጊል = ከንጨም ሰሰጀ ሰጀጉር ይረሰ ይጉን ሰጉውን ይ ፡ ከወሰው ጀጀስ እጦር ሳጀጉንጎ ጀጀስ ዛንጨንጉን - ጀሰስ በሥን ከመጉቆ፥ በጉጉር ዓንጀን ግሰት የሰሰሥውን ሁሉ ይ ፡ ሰሰጉሩሥን ቆሳ ቆሰው ፡ የሚል ፡ ጎጨር ከሰጀጎ ከጦር ግጉ ጀሰስ ገጨሥንና ጀሰስ ሰጉር ያሰውን ሁሉ ጀመጉው ፡ ተጣጉት ፡ ' ሳሩ ' ያጣል = ግሰት ጀጣንጉት የግሰውን መጉጀጉጎት ፡ ሰጉሩ ያሰው የጉሰጎ ጀደቃ ሁሉ ጉንጉር ከጉጣ ጀደሰ ጎጨጣችጉ = በጎንጉው ሰዋሰጉቆ የጉሰሥ የሥሰ ሰጉውን ጀጀር ገጨር ፡ ከጉጉት ሰጀጀር ጀጀር ጀሰስ ጉጨሰ ጀጀሰ ጀሰጉሰውም ጉንጉር ሰጉጉጉ ጎጉጉጉጉት ጉጉጉጉ ጀጀሰ ጀጀሰ ጀጀሰ

“ ወቸው ጉድ ! ደሞ እኔ ፣ ራሲዉ ነኝ የምመርጠው ! ለሁሉስ ነገ ትደርሽበት የለ ? ” አለና ጉንጯን ቄንጠጥ አደረጋት ።

በበነጋው ጧት ገብርዬ ከሐር እጀ ጠባብና ሱሪው ላይ የእንበሳ ለምዱን ደርቦ ፣ እንፋሮውን ደፍቶ በግራ ጉኑ ጐራዴዉን ፣ በቀኝ ጉኑ ሽጉጡን ታጥቆ ፣ ታንጉት በሐር ጥልፍ ቀሚስና በቀሞን ኩታዋ ላይ ጉንደር መዋታ ከሰነበቶች በኋላ ፣ ‘ እረ ጉንደሮች የቋራ ቡትቷም ብለው እንዳይሰድቡሽ ! ’ ብለው ቴዎድሮስ የሰጧትን ሐር ካባ ደርባ ወደ ቤተ መንግሥት ተጓዙና ሲገቡ ፣ እርሱ ወደ መሰሉቹ እርሷም ወደ መሰሉቿ ተሰደዩ ።

መኳንንቱ ከነሠራዊቱ ከሠፈሩበት ወይም ከዐረፉበት እየመጡ ወደ ዋናው የፋሲል ግንብ አዳራሽ ገቡ ። ትርምስ ፣ ግርግር ፣ ጩኸት የለም ። ከፋሲል ግንብ ግቢ ብዙ ሰዎች ቢኖሩም ፣ ብዙም ሳይንቀሳቀሱ ፣ ብዙም ሳይነጋገሩ በታዛቢነት የሚያስተውሉ ይመስላሉ ።

ሁሉም ገብቶ በአጋፋሪው እየተመራ በየሥፍራው ከተቀመጠ በኋላ ፣ ቴዎድሮስና ተዋበች እቡን ሰላማ ትንሽ ቀደም ብለው ፣ ገብርዬ ፣ ከንልሞ ፣ ከዓለሜና ከሌሎችም ጋር ሆነው ፣ እንደ ሥርዓቱ እስኪቀመጡ በአዳራሹ የነበረው ቆም ብሎ ተቀበላቸው ። ታንጉት ይሆንን አዳራሽ ቀደም ሲል ደጋግማ ያየችው ቢሆንም ፣ ከዚያ በፊት አይታ በማታውቀው ይሆንን በመሰለ ሥነ ሥርዓት ከፊትዋ ሲደቀን ፣ የመጀመሪያ ጊዜዋ ስለ ነበር የሚሰብ የሚማርክ ትርኢት ሆነባት ። ከውስጥ በኩል የሚሰናዳውን ፣ የሚቀራርበውን ለመረዳዳት ወጣ ገባ ብትልም ፣ ወይ ንዋ ፣ ጆሮዋ ፣ ሐሳብዋ ሁሉ በአዳራሹ እንቅስቃሴ ላይ ነበር ። ለምን እንደሆነ ራስዋም ምክንያቱ አልገባትም ። ገብርዬ እንደሆነ መሸሙ እንደ ማይቀር ታውታለች ።

ሊጋባው ከቴዎድሮስ አጠገብ ቁሞ ፣ የመኳንንቱን ስም እየጠራ ማዕረጋቸውንና ግዛታቸውን ወይም ሥልጣናቸውን ከፍ ባለ ድምፅ ሲናገር ፣ እንድ በእንድ ብድግ እያሉ ለቴዎድሮስ እጅ ይነሡና ተርታ በቅሙት አጋፋሪዎች እየተመሩ የዕታ ቤቱ ሹም ወደ አለበት ከፍል ያሔዳሉ ። ከዚያም ቀሚሳቸውን ለብሰው ሲመለሱ እንደ ገና እጅ ይነሣሉ ።

ሴቶቹ ፣ የየራሳቸው ባል ወይም ወገን ሲሾም ፈንደቅደቅ ፣ ሲሉታን ጉት አብራ ብታጅብም ፣ በአብዛኛው የሚሰማት ከተካፋያነት ያልቅ የተመልካችነት ስሜት ነበር ። ገብርዬ ፣ በፈታውራሪነት ማዕረግ የመር አዝማች ተብሎ ሲሾም ብቻ ልብዋ ትር ትር አለባት ። እንግዳ ‘ራስ’ ሲባሉ የገብርዬ ሹመት ቢያስደንቃትም ፣ ስሜቷ የደስታ ያውን የድንጋጤ በት ከክል አልታወቃትም ።

እያንዳንዱ ሹመት ሲነገር መኳንንቱ እርስ በርሱ ይታየያል ። አንዳንዱም ቀሚሱን ለብሶ ወደ ቦታው ሲመለስ ከንፈሩን እንደ መን

ከስ ሰ ያደርግ ያስታውቃል ። እንደ በፊቱ ራስ ወርቁ ፣ እንዲያም ሲል የጋብቻ መደለያው ፣ ሥልጣን ባይኖርበትም ሲጠሩት የሚከብድ ግዛት የሚሰጥ የመሰላቸው ብዙዎች ነበሩ ። አብዛኛዎቹ ያሰቡትን አላገኙም ።

ብዙውን መኳንንት ይባስ ያናደደው ሌላም ሹመት ተከተለ ። ሊጋባው ላንዳፍታ ገታ አለና ፣ ልጅ ዮሐንስ ብሎ ሲጣራ ፣ ጆን ቤል ተነሥቶ እጅ ነሣ ። መኳንንቱ ሁሉ የሚሰማውንና የሚያየውን ማመን እስኪያቅተው ድረስ ተደመመ ። ሊጋባው ፣ ‘ ሊቀ መኳስ ’ ብሎ ሲናገር ቴዎድሮስ የመኳንንቱ ስሜት ገብቷቸው ፈገግ አሉ ። ስምንት የሚጠይቁ ይመስልም ወደ አቡን ሰላማ ዘወር ብለው ተመለከቱ ።

ሹመቱና ሽልማቱ አብቅቶ ፣ ለስሙ ‘ ቁርስ ’ የተባለ ግን ፣ ከምሳ የከበደ የእልፍኝ ግብር ሲቀርብ የብዙው ሆድ ተዘግቶ ነበር ። አብዛኛው የፈለገውን አለማግኘቱ ሳያንስ ፣ ባሕር አቋርጦ የመጣ የውጭ አገር ሰው ‘ሊቀ መኳስ’ መባሉን እንደ ትልቅ ክህደት ቁጠረው ። ጆን ቤል ከቴዎድሮስ ዘንድ ባለሟልነቱን ካጠበቀ ወዲህ ፣ ተጠምቆ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት መቀበሉን ግን ብዙዎቹ አያውቁም ነበር ።

መጠጥ አሳላፊዎች እስቀድመው እንደታዘዙ ያህል መኳንንቱ ምግቡን ችላ ማለት ሲጀምሩ ማሳለፉን ትተው በየጥጉ ቆሙ ። ሊጋባው አጨበጨበና ፣ “ እስቲ እንደዚ ዝም በሉ ! ” አለ ። ሁሉም ከሐሳቡ ጋር ስለሚጋገር በፊትም ቢሆን ብዙ ድምፅ አልነበረም ። ታንጉትም ተረጋግታ ሁናቴውን ትከታተል ጀመር ።

ቴዎድሮስ ፣ ወይናቸውን ተራ በተራ በእያንዳንዱ መኳንንት ላይ አሳረፉት ። ሐሳባቸውን ለመገመት ከመሞከራቸው ጋር ፣ ‘ ሐሳቢን ተረዱልኝ ’ ፍቅራቸውንና ታማኝነታችሁን ስጡኝ ፣ በሚል አስተያየት አንገታቸውን ቀና አደረጉና ፈገግታ አሳዩ ። ምናልባት ራሳቸው አይታወቃቸውም እንጂ ፣ ከፈታቸው ቀድመው ሞትን የሚጋፈጡ ተከታዮች ከአፈ ራሳቸው የተፈጥሮ ወይም የመሪነት ችሎታ ጋር ፣ ስስና ዘርጋ ያሉትን ከንፈሮቻቸውን ሲገልጡ ብቅ የሚለው ፈገግታቸውና ጉድጉድ ብለው እንደ ቡቨር ወይን የሚቁለጨለጩት ወይኖቻቸው አስተያየት አንዳች የመሳብ ኃይል ነበራቸው ። ተመልካች ፣ ፍቅርንና ትሕትናን ፣ እውነተኛነትንና ቆራጥነትን አዋሕደው የሚገልጹ መስሎ ይሰማዋል ። በእውነቱ ጊዜ ግን ይሆንን ተአምር አልሠራላቸውም ። አብረዋቸው ከተንሡት የቅርብ ባለሟሎቻቸው በስተቀር ፣ ሹመት በዘር ፣ ቀሚስ ለስም የጠበቁት አብዛኞቹ መኳንንት የሕሊናቸው ትዝብት አገጫቸውን ወደታች እንደ ጎተተው ያህል አንገታቸውን አቀረቀሩ ። ከዘመቻ በፊት ፣ ከድል በኋላ ፣ የጦር አበጋዞቻቸውንና ሠራዊታቸውን በዙሪያቸው ሰብስበው መወያየት የሚያዘወትሩት ቴዎድሮስ ፣ በእሁኑ አዳራሽ ውስጥ አብዛኛው የቅሬታ ስሜት መታየቱን መገንዘባቸው አልቀረም ። በዙሪያቸው ያለውን ያቀረቀረ ፊት ሲያስተውሉ ለሚያቀርቡት ሐሳብ ተስማሚ ጊዜ አለመ

ሆኑ ተሰምቷቸዋል ። ነገር ግን ፣ የዘመነ መሳፍንት ዝብነና ላስለመደው ሥኣንንት ቅብጥብጥነት ፣ ፈት መስጠት ፣ ‘ ባለጌን ቢያከብሩት የፈሩት ይመስለዋል ’ እንደሚባለው የሚሆን መሰላቸው ። ከዚህም በቀር ከጀን ቤል ጋር ብዙ ከተመካከሩና ከተወያዩ ወዲህ ፣ ሐሳባቸው ጊዜ እንደ ማይሰጥ ምጥ ከውስጥ ይገፋቸው ነበር ።

‘‘ እህህህ ! ’’ ሲሉ ጉሮሮዋቸውን ጠረጉና ፣ አውንም ሰዉን እንደገና ቃኝተው ንግግራቸውን ጀመሩ ። ‘‘ ታሁን በፊትም ቢሆን በዚህ አዳራሽ ሹም ሽር ሲደረግ ፣ ቀሚስ ሲሰጥ የኖረ ነው ፣ አዲስ አይደለም ። እነ ራስ አሊ ፣ እነራስ ጉግሣ ፣ እነራስ ይማም ፣ እነራስ ማርዬ ፣ ኧረ ስንቱ ተቁጥሮ ! ሲሾሙ ፣ ሲሽሩ ፣ ርባና የሌለው ቀሚስ ሲያለብሱ ኑረዋል ። እኔ ግና አነሣዬ አገሬን ላቀና ፣ ወገኔን በመልካም ላስተዳድር ስለሆነ ፣ የምሾመው ፣ የምሸልመው ለዚህ ይረዳኛል የምለውን እንጂ ሌላዉን አይደለም ። ’’

በመከፋት አቀርቅሮ የነበረው መኳንንት ፣ በማድነቅ ሳይሆን ጉድና መዓት እንደ ሰማ ያህል ቀና ብሎ እየተመለከተ ያዳምጣቸው ጀመር ።

‘‘ እናንተም ቢሆን ታሁን በፊት ተሹማችሁ የነበረ አላችሁ ። ታሁን በፊት አገር ተሹማችሁ የማታውቁም አላችሁ ። ዛዲያ የዛሬው ሹመት እንደ ድሮው ልትቀማጠሉበት ሳይሆን ሕዝቡን እንድታስተዳድሩበት ፣ ዳኝነቱን በሚገባ እንድትፈርዱ ነው ። ወንበዴና ወስላታን አጥፍታችሁ አገሩ ሰላም እንዲሆን ታረጋላችሁ ። የምትቀበሉት ግብርም የተወሰነ ይሆናል ። ’’

ብዙዎቹ የባሰ በመገረም እርስ በርሳቸው ሲተያዩ ፣ አማርኛ በመ ጠኑ የሚያውቀው ሊቀ መኳስ ዮሐንስና ፣ አቶ ሳሙኤል ከኋላው ሆኖ የሚያስተረጉምለት ቆንስል ፕላውዴን በአድናቆት ራሳቸውን ያወዛ ውዛሉ ።

‘‘ ለዚህ ሁሉ በቅርብ እየተመካከርን የምናወጣው ሕግ አለ ። ሕዝቡን የሚበድል ፣ ሕግን የሚጥስ ሹም እንደ ሌላው ሁሉ ይቀጣል ። እንዲያውም አይማረኝ አልምረውም ፣ በሾምኩት ሰው ላይ ነው ቅጣቴን የባሰ የማከብድበት ! ! ’’

ቴዎድሮስ ፣ ንግግራቸውን ተግ አድርገው እንደገና ከመቀጠላቸው በፊት መኳንንቱን ሁሉ በዐይናቸው ቃኙት ። ‘‘ ከዚህም በስተቀር ወደ ሀገራችን እንዲገባ የምናስበው አዲስ ነገር አለ ። ይሉውም ሀገራችን እንደ ወትሮዋ ገናና እንድትሆን በማለት ነው ። በዚህ ቤተ መንግሥት ’’ አሉ ቴዎድሮስ የአዳራሹን ዙሪያ እየቃኙ ፣ ‘‘ መሳፍንቱ ፣ መኳንን ቱና ነገሥታቱ ሕይወታቸውን ለጠጅ ለጮማና ለዝሙት አውለው ሲማ ግው ሀገራችን ኢትዮጵያ እየሚሚች ሔደች ። ’’ ቴዎድሮስ አገጫቸውን እንደ ማሸት አደረጉ ። ‘‘ አገራችንንም እንደ ድሮው ፣ ከድሮዋም የበለ ጠች ገናና ለማድረግ ምን እንደሚበጀን ፣ ቆንስል ፕላውዴንና ሊቀ

መኳስ ዮሐንስ በሐሳብም በምክርም ይረዱናል ። የሚረዱን ወዳጆችም ያፈሩልናል ። ሊቀ መኳስ ! ’’ አሉ ወደ ጀን ቤል ዘወር ብለው ፣ ‘‘ እስቲ ለኔ ብዙ ጊዜ ያጫወትከኝን ተዚህ ላሉት ሁሉ ንገርልኝ ! ’’

ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ፣ ተነሥቶ ቁሞ አዲስ ከደረበው ቀሚስ በታች ድግድጉን እያስተካከለ ቴዎድሮስንና ሌላውን ሁሉ እጅ ነሣ ። ‘‘ እባታጠቅ መቸም አንድ አገር ትልቅ ፣ ገናና የሚሆን ሥልጣኔ ሲያገኝ ነው ። ሥል ጣኔ የሚገኘው ደሞ በትምህርት ብቻ ነው ። ስለዚህ ከሁሉ በፊት ትምህ ርት ያስፈልጋል ። ’’ ጀን ቤል ፣ የሚጠሩውን ቃል ከአቶ ሳሙኤል እየ ጠየቁ ፣ በሚገባ መግለጽ ሲያቅተው እንዲያሲተረጉምለት በእንግሊ ዝኛ እየነገረ የራሱ አገር እንግሊዝ ፣ በስፋትም በሕዝብ ብዛትም አነስ ተኛ ስትሆን ፣ በመሠልጠንዋ ምክንያት በእንግሊዝ ግዛት ላይ ፀሐይ አትጠልቅም እስኪባል ድረስ የዓለምን አብዛኛ ክፍል የምትገዛ መሆ ንዋን በመተረክ ሥልጣኔ የሚሠራውን ተአምር በሰፊው አስረዳ ። በመ ጨረሻም ትምህርት የሌለው ፣ ብሎም ያልሠለጠነ ሕዝብ በጦርነት እርስ በርሱ ስለሚፋጅ ደካማ ሆኖ በሠለጠነ አገር መገዛቱ እንደማይቀር ተና ግሮ አበቃ ።

ቴዎድሮስ ፣ ‘‘ ዛዲያ ስለዚሁ ጉዳይ ምን ታስባላችሁ ? ’’ ሲሉ ለሁሉም በደፈናው ጠየቁ ።

በተለይ በነጻድቁ ዮሐንስ ጊዜ ለዳኝነትም ፣ ለአስተዳደርም ተዘው ትሮ ይሠራበት የነበረው የሸንጉ ውይይትና ትችት በዘመነ መሳፍንት ቀርቶ ወደ መረሳቱ ደርሶ ስለ ነበር ፣ በመፍራትና በመፈራራት ሁሉም ለጥቂት ጊዜ ዝም አለ ።

‘‘ ሊቀመኳስ ዮሐንስ እንዳጫወተኝ የሱም አገር ነገሥታትና ንግ ሥታት የሚሠሩት ነገር ሁሉ በመኳንንቱ እየተመከረበት ነው አሉ ። በኛም አገር ፣ ‘ አንድ ዕንጨት አይነድ ፣ አንድ ሰው አይፈርድ ’ እንደ ሚባለው ፣ ትልቅ ያገር ጉዳይ ስለሆነ ተዚህ ያለነው ሁላችንም ብንመካ ክርበት መልካም ነው ’’ ሲሉ ቴዎድሮስ በድጋሚ አደፋፈሩ ።

ፊታውራሪ ሙጬ ፣ የኩታውን ጫፍ ጉትቶ እያጣፋ ሁለት ሦስት ጊዜ ለጥ ብሎ እጅ ነሣ ። ጥቅሻ ፣ የክንድ ጉሸሚያና ሹክሹክታ ባንደ ተዳርሶ ፣ ከኋላ ፣ ከፊት ፣ ከቀኝ ፣ ከግራ ያለው ሰው ሁሉ ወደርሱ ዞረ ። በአደባባይ ሳይሾም እንዳመቸው ራሱን ፣ ‘ፊታውራሪም ፣ ግራዝማችም ፣ ደጃዝማችም ’ እያለ ሲሠይም ኑሮ ፣ አሁን የፊታውራሪ ቀሚስ በመሰጠቱ ይደሰት ይከፋ በትክክል ባይገመትም ፣ ከዚያው ከጐንደር ዐለፍ ብሎ የፈንጠር ተወላጅነቱ ከአደባባይ ስለማይለይና በአነጋገር የሠለጠነ በመሆኑ ፣ የሚያውቁት ሁሉ የሚለውን ለመስማት ዝግ ። ‘‘ ጃንሆይ ! ’’ ሲል ጀመረ ፣ አሁንም ደግሞ እጅ እየነሣ ። ‘‘ መቸም እኝህ የባሕር ማዶ ሊቀ መኳሳችን ስለውቀት ጠቃሚነት የሰጡን ምክር እንዲህ ነው አይ ባልም ። ዕውቀት ጠቃሚ መሆኑን መቸስ ማን ያብላል ? ’’

‘የባሕር ማዶ ሊቀ መኳስ’ ሲል ብዙ መኳንንት አሸሙሩ ገብቷቸው በጉሪጥ ተያዩ ።

“ ዕውቀትማ መቸም ለሰማዩም ለምድሩም ይበጃል ። ” አውንም እጅ ነሣ ። “ ዛዲያን ፣ አውንም የትኔ ፣ የትርጓሜ ፣ ያቋቋም ፣ የዝማሬ መዋሲት ፣ ሊቃውንት የሞሱበት አገር ናት ። ሌላው ቀርቶ የጉንደር ሊቃውንት ለድፍን ኢትዮጵያ እሬ እንዲያው ሊቀ መኳስ ዓለም ለሚሏት አይተርፉም ! እና ጃንሆይ ፣ ዕውቀት ያላቸው ሊቃውንት ካሉን እንዴት ነው ነገሩ ፣ ደንቆሮች እንባላለን ወይ ብዙ ነው ! ” ሲል በንግግሩ ማሳረጊያ እጅ ነሣ ።

ሊቀ መኳስ ዮሐንስ መልስ ለመስጠት ቃጣና አቅማማ ። የቀለምና የሃይማኖት ትምህርት ብቻውን በቂ ዕውቀት ሊሆን እንደማይችል ለመግለጽ ትክክለኛ ቃል ጠፍቶት ደንቆሮ ማለቱ ትልቅ ስሕተት መሆኑን ተገንዝቧል ። “እኔ ደንቆሮ ለማለት - ” ብሎ መልስ ሲፈልግ ቴዎድሮስ ቀበል አደረጉለት ።

“ መቸም ፣ ሊቃውንትና ካህናትማ ሞልተውናል ” አሉ ቴዎድሮስ በሽሙጥ ዐይነት ወደ አቡነ ሰላማ እየተመለከቱ ። “ ፈታውራሪ እንዳለው ሊቃውንት እንዳሉን እውነት ነው ። ግናስ ፣ የማያውቁትን የማዕዝ ቋንቋ የሚያነቡ ፣ የሚያነቡትን የማይጽፉ ፣ ትርጉሙም ምኑም ላይገባቸው የሚያዜሙ ፣ የሚጸልዩ ፣ እንዲያው ሲጠይቋቸው የሚያነቡ ንቡት ነገር ርግማን ይሁን ምርቃት ፣ ውግዘት ይሁን ምስጋና መናገር የማይችሉት ስንት ናቸው ! ውሽት አንናገር ከተባለ አብዛኞቹ አይደሉም ፈታውራሪ ! ”

ፈታውራሪ በመልሱ ትንሽ አቅማማ ። “ በመላእክት ቋንቋ መናገር መቸም እኔ ዕውቀት እንጂ ድንቁርና አይመስለኝም ” አለ ። በሹመቱ የተከፋ መኳንንት መልሱ ቁጭቱን ያወጣለት ይመስል በአድናቆት ራሱን አወዛወዘለት ።

ቴዎድሮስ ፣ ነገሩን ፍሬ ፈርስኪ በማድረግ ዐይነት እንደ ሙግቅ አሉ። “ ነገሩስ ያባቶቻችን ቋንቋ ነው ። የመላእክት ቋንቋስ ቢሆን ትርጉሙን ፣ ምሥጢሩን ካላወቁት ፣ እንደ ደመ ነፍስ እንስሳት ተንጫጩበት እንጅ መች ተነጋገሩበት ? ” ወደ አቡነ ሰላማ ዘወር ብለው ጠየቋቸው ። “ ምን ይመስልዎታል አባታችን ? ”

ሳይፈልጉ ጥያቄው የተሰነዘረባቸው አቡነ ሰላማ ከረዛቸው ጋር ጥቂት አጉተመተሙ ። ግዴታ ካልሆነባቸው በተቀር ከቴዎድሮስ ጋር ብዙም መነጋገር አይፈልጉም ። ደጃች ውቤ የሚያነጋግሩዋቸው እንደ አባት እያከበሩ ፣ እያባበሉ ስለነበር ጭውውታቸው ይጥማቸዋል ። ቴዎድሮስ የሚያነጋግሩዋቸውና አንድ ነገር የሚጠይቁዋቸው ግን በሚ ያፋጥጥ የክርክር መልክ ነው ። “ መቸም ... መቸም ” አሉ ረዛቸው ንሳብ ሳብ እያደረጉ ፣ “ የእግዚአብሔርን ቃል ከአጥናፍ አጥናፍ የሚሰብኩ ካህናት ሊመሰገኑ እንጂ ሊነቀፉ አይገባም ። ”

ቴዎድሮስ ፣ ድንገት በግራሚ ፈንቅሉ የመጣ ማታቸውን ለማመቅ ይመስል እፋቸውን በግራ እጃቸው ከደን አደረጉ ። “ እሱንማ መቸ አጣ ነው ፣ አባታችን ። ነገር ግናስ እየጠመጠመ ቁስ ፣ ካህን ነኝ ባይ ፣ ቆብ እየደፋ መነኩሴ ነኝ ባይው ሁሉ ፣ በዚህም ልቆ ርቆ ካገር ግዞ ፣ ባሕር ተሻግሮ በሃይማኖት መሪነት የሚመጣው ሁላ ፣ ” ቴዎድሮስ ሆን ብለው ከዚህ ላይ ንግግራቸውን ረገጥ ረገጥ አደረጉት ። “ የዓለሙን ነገር ውሉ ትቶ የእግዚአብሔርን የክርስቶስን ቃል ለማዳረስ የዘመተ ነው ብለው ያምናሉ ? ” ሲሉ ከአስክንድርያ ከመነሣታቸው በፊት ብዙ ሺህ ብር የተከፈላቸው ፣ ከመጡም በኋላ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የበላይነታቸው የሚሰበስቡትን ሰፍር ቁጥር የሌለው ሀብት ወደ አገራቸው የሚያግዙ መሆናቸውን በሚጠይቅ አስተያየት ተመለከቷቸው ።

አቡነ ሰላማ ፣ የቴዎድሮስን መቅን ዘይቤ በትክክል ባይረዱትም በነገር የተነኩ ወይም የተደፈሩ መሆናቸው ከሰዉ አስተያየት በስ ተሰማቸው ፣ ያወሰወሰ ያ ቀይ ፈታቸው የባሰውን የተሰረበ ጉበት መሰለ ። ግን መልስ አልሰጡም ። ነገሩ የገባው በማዘን ከንፈሩን ሲመጥላቸው ፣ ሌላዉም ለቅጽበት የራሱን ቅሬታ ረስቶ በውርደታቸው እንደ መሣቅ ሲቃጣው ፣ ጸጥ ብሎ የቆየው አዳራሽ ትንሽ ውካታ አስተጋባበት ።

ቴዎድሮስ ፣ ሁናቴውን በፈገግታ ለጥቂት ጊዜ ከተመለከቱ በኋላ ወይናቸውን ወደ ሊጋባው መለስ ሲያደርጉ ፣ “ እሺሺ—እሺታ ! እሽታ ! ” ሲል አጨበጨበ ። ወዲያው አዳራሹ ጸጥ አለ ።

“ የጸድቁን የኃጥኡን ጉዳይ አውን ለርሱ ፍርድ ትተን እንለፈውና ፣ እስቲ ሊቀ መኳስ ስለ ትምህርትና ስለ ዕውቀት እስታውን በኛ አገር ስለ ሌለው እንመካከርበት ” ሲሉ ቴዎድሮስ ቀኝ እጃቸውን እንደ መዘርጋት አደረጉ ።

አውንም ብዙው መኳንንት በማመንታት እርስ በርሱ ሲተያይ ፣ ግዙፍ ቁመናው ቂላ ቂል የሚያስመስለው ቀኖማች አሥማረ ብድግ ብሎ እጅ ነሣ ። “ ጃንሆይ መቸም የዚህ የኛው አገር ትምህርት ርባና የሌለው ተሆነ ፣ የባሕር ማዶውን ዕውቀት ያሉትን እንዴት ነው የምናመጣው ? ” እንደ ገራም አነጋገሩ ጥያቄው አለማወቅ ይመስላል ። ቆጻው አሳላች መሆኑን በቅርብ የሚያውቁት ግን ፣ ምክንያት ያለው ጥያቄ እንደሚሆን አላጡትም ። ምንም ቢሆን ከደጃች ውቤ ቤት ያደገ ሰው ነው ።

ቴዎድሮስ እንደ መሣቅ አሉ ። “ ቀኖማች አሥማረ ፣ መቸስ በወርቅ ተገዝታ በስልቻ ተቋጥራ ፣ በከብት ተጭና የምትመጣ እንዳትመስልህ ! ”

“ እዛዲያ እንዴት ነው ጃንሆይ ? ” ሲል አውንም በግራገር አነጋገር ጠየቀ ።

“ ነፍጥ ፣ መድፍ የሚሠሩ ፣ እናጢነት ፣ ግንበኝነት ፣ እንጥረኝነት ፣ ሌላውንም ጠፍ ከመሆን የደረሰች አገራችንን ለማልማት ፣ ሕዝብን ለማሠልጠን የሚበጅ ሙያ የሚያስተምሩ ፈረንጆች ለማምጣት አስ በናል ። በዚህ ረገድ ክርስቲያንዋ የንግሊዝ መንግሥት ግርማዊት ቪክ ቶሪያ ልትረዳን እንደምትችል . . . ’’ እያሉ ቴዎድሮስ ወደ ሁለቱ እንግሊ ዛውያን ዘወር ብለው ተመለከቱ ። “ ቆንስል ፕላውዴንና ሊቀ መኳስ ዮሐንስ አሜው-ተውኛል ። ”

መኳንንቶቹ እርስ በርሳቸው ተያዩ ። ‘ ፈረንጅ-ፈረንጅ ’ የሚለውን ቃል በሹክሹክታ ተቀባበሉት ።

“ እንጥረኛና ግንበኛኩ ባነራችን መች አጣን ፣ ጃንሆይ ” የሚል ጥያቄ ከሌላ መኳንን ቀረበ ።

“ አሄሄ ! ” አሉ ቴዎድሮስ በቅፌታ መልክ ። “ያገሬን ሰው መን ቀፍ አይሁንብኝ እንጅ ፣ ለጕንደር ወይዛዝርት እምባርና አልቦ ከመሥ ራት የማያልፈውን እንደ ባለሙያ ቁጠርከው ? አሁን ማ — ይሙት ፣ ከስንት ስንት ዓመት በፊት ባባቶቻችን ጊዜ የተሠራውን ይህንን የመ ሰለ ግንብ የሚሠራ ግንበኛና አናጢ ዛሬ አለ ? አስቲ እምጡልኝና ላሠ ራው ፣ ልሹመው ! ” በመጋበዝ ወደ መኳንኑ እጃቸውን ዘረጉ ። መረታ ቱን የተቀበለው መኳንን እጅ ነሥቶ ተቀመጠ ።

“ ጃንሆይ ! እንዲያው ” ሲል ከቀድሞ ፊታውራሪነት አሁን የማ ራዝማች ቀሚስ የተሸለመው ወገፈው ጕበና የሚጠይቀው ነገር የጠፋው ይመስል ከአጠገቡ የተቀመጡትን ሰዎች በዐይኑ ፈለገ ። “ እንዲያው እነዚህ ፈረንጆች ያሏቸው ለማስተማር የሚመጡት ፣ አስላሞች ናቸው ወይስ አረመኖች ? ”

ቴዎድሮስ ፣ ሐሳብ የሚጠይቁ ይመስል ወደ አቡነ ሰላማ ተመለከቱ ። ጳጳሱ ግን ፣ እንዳልሰሙ በመምሰል አንገታቸውን ቀርቀር አድርገው ጭጭ አሉ ። አብዛኞቹ መኳንንት ነገሩ ገባቸው ።

ቴዎድሮስም ጥቂት አሰቡበት ። በአቡነ ሰላማና በካቶሊኩ በአባ ያዕቆብ ፣ እንደዚሁም በእነሱና ‘ ፕሮቴስታንት ’ በሚባሉት ሚስዮናውያን መካከል ያለውን ጥላቻ አሳምረው ያውቁታል ። ከዚህ ሁሉ በላይ ግን እንደ ራሳቸው ስሜት የሚያሳስበው እደጋ ሌላ ነው ። ኢትዮጵያ የሚያስ ፈልጋት ጉዳይም ከእነዚህ ጠብ ሁሉ በላይ ነው ። ግን ከዚያ በፊታቸው ?ተሰበሰበው መኳንንት ይህንን ነገር አሣምሮ አይረዳውም ። ጕጂው ንም ፣ ጠቃሚውንም የሚያውቅ የተማረ ፣ የሠለጠነ ሕዝብ ነው ብሏ ቸው ነበር ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ። አንገታቸውን ቀልበስ አድርገው ላንዳፍታ እንደ መቆዘም አሉ ። “ መቸም አገራችንን እንውረር ፣ እንግዛ የሚሉት ግብጦች ፣ ቱርኮች ፣ ያው እስላሞች ስለሆኑ ፣ ከነሱ ጋርማ እንዴት እንሰማማለን ብላችሁ ነው ? ከሃይማኖታቸው እንኳን

ነገር የለንም ፣ በክፋት ስለ መጡብን ነው እንጂ ። አሁን እኛን እንዲያ ስተምሩን ያሰብናቸው ግን ክርስቲያኖች ናቸው ። ግና ክርስቲያንነታቸው እስተዚህ ተኛም ቅባት ፣ ጸጋ እንደሚባለው ስለሆነ ተዚህ ምናለን ? ” አሉና መኳንንቱን በአጠቃላይ ትኩር አድርገው ተመለከቱ ። የቴቀበ ላቸው አስተያየት እንደ አለት የጠጠረ ነበር ።

“ አባታችን ፣ አንድ ይበሉኝ እንጂ ! ” አሉ ቴዎድሮስ ኮስተር ባለ አነጋገር ።

አቡነ ሰላማ ፣ ሪዛቸውን እየጕተቱ በሐሳብ ስልምልም አሉ ። ከየትም ተነሥቶ ፣ ራሱን መሪ አድርጎ እንዳሰብኩት ፣ እንደ ፈለግሁት ልሥራ ከሚል ቴዎድሮስ ጋር ፊት ለፊት መጣላቱንና መጋፋቱን ፣ ቀርቶ ፣ መከ ራከሩን ስለሚፈሩት እያስታመሙ ቆይተዋል ። አሁን ግን ፣ ከመኳንንቱ በቀረበው ጥያቄ መሠረት ፣ አስተያየታቸውን ከተጠየቁ መልሳቸውን መስጠት የተሻለ አጋጣሚ መሆኑ ታያቸው ። የአብዛኛው መኳንንት ስሜት ገብቷቸዋል ። በዚህም ላይ የቴዎድሮስን ፈታድ መፈጸማቸው ነው ። “ መቸስ እሱማ እረመኔና እስላም ፣ እስላምና ክርስቲያን እንደ አይደ ለም ፣ ተየት ተቀራርቦ ። ግና ደሞ ክርስቲያን በሚባሉት መካከል የማይስማሙበት ብዙ ፣ ብዙ ” አሉና ከዚህ ላይ ራሳቸው ታላቶችን በመርገጥ ፣ እንደ አስተርጓሚ ለሚረዳውም ረጂኢያቸው ጣታቸውን በመቀሰር ፣ “ጥልቅ ምስጢር አለ ሲሉ አስገነዘቡ ። ” ተዚህም የተነሣ ልክ እኛ የማርቆስ መንበር ሆነን ፣ የጴጥሮስ መንበር ነን የሚሉት ብዙ ጉዳት አድርሰውብናል ። ይኸ መቸም በመጣፍ ያለ ነው ። በጥንቱ የማ ርቆስ መንበር ትምህርት መናፍቅ ተብለው የተወገዙት ካቶሊኮችና — ፕሮቴስታንቶች ሲሆኑ ፣ እርስ በርሳቸው እንደዚሁ እንደ ተፋጁ ነው ። ዛዲያ በስመ ክርስቲያን ሃይማኖት መቸስ — ” ሲሉ ትረካቸውን አቋ ረጡና ጸሎት የሚያደርሱ ይመስል ወደ አዳራሹ ጣሪያ እንጋጠጡ ። አሁ ንም መለስ ብለው ሪዛቸውን ጕተቱ ። እንዳሰቡት የቴዎድሮስ የቅርብ ባለሟሎች ሳይቀሩ መኳንንቱ ሁሉ ዐይኑን በርሳቸው ላይ ተክሎ የሚ ናገሩት ቃል እንዳያመልጠው ጆሮዉን ለግቷል ። ቴዎድሮስ ብቻ የመ ድረኩን ወለል በቀስታ በእግራቸው ይቆረቁራሉ ።

“ ክርስቲያን ነኝ የሚለው ሁሉ ክርስቲያን ባለመሆኑ ብርቱ ጥል እንደሚፈጠር በናንተም አገር መድረሱን መቸም አሳምረው የሚያው ቁት ታሪክ ነው ። ” አቡነ ሰላማ ፣ ነገራቸውን ሁሉም እንዲከታተ ለው ሪዛቸውን እየሳቡ አሁንም ተግ አሉ ። “ በአጤ ሱስንዮስ ዘመን እነዚያ በመንበረ ማርቆስ ላይ የተነሡት የካቶሊክ እምነት ተከታዮች መዋተው እንደዚያ በማድረጋቸው ያ ሁሉ እልቂት ደረሰ ፤ ያ ሁሉ ሰው አለቀ ፤ ያዉ እንደሚያውቁት ልጃቸው ፋሲል ነግሦ ፣ ‘ ሃይማኖት እንደ አባቶቻችን የመንበረ ማርቆስ ’ ‘ ሲል ያ ሁሉ በረደ ፤ ሰላም ወረደ ፤ ይኸው ነው የሃይማኖት ታሪኩ ” ሲሉ ደመደሙ ።

ብዙ ጦር ሜዳ ላይ ስልት እያወጡና እየመሩ ያሸነፉት ቴዎድሮስ ጋሻቸውን በአንገቱ አንከርፍፈው እንደ ተሙቱ ወዲያው ገባቸው ። በአቡኑ መልስ ቆስለዋል ። እንደ ቆሰለ አልሃም አውሬም አውንም ወደፊት ተጋፈጡ ።

“ ምኑን ከምን አመሳሰሉት አባታችን ። ያ ሌላ ፡ የአውኑ ሌላ ። ” ቴዎድሮስ ወዲያው መልሰው እንደበታቸውን ረገብ ለማድረግ ሞከሩ ።

“ የእኔ ሐሳብ ለሥራ የሚመጡት ወዲያ ወዲህ ውልፍት ሳይሉ ሥራቸውን ብቻ እንዲሠሩ ነው ። አይ ሌላ ነገር ውስጥ እንገባለን ካሉ እኔ የማደርገውን ዐውቃለሁ ። እንኳንስ ከባዕድ አገር የመጡ ፡ ተዚህ ካገራችንም ካህን ነኝ እያለ ሲወላገድ የሚውለው ሁሉ ፡ አርሶ ፡ ቆፍሮ ፡ ወይም በሚያውቀው በሌላ ነገር ሁሉ ሠርቶ እንዲኖር ነው የሚሆነው ። መጽሐፉም ‘ብላዕ በአፈ ገጽከ’ ብሏል ” አሉ ወደ አቡነ ሰላማ ዘወር ብለው እየተመለከቱ ። “ አይደለም አባቴ ? ” ሲሉም ጠየቋቸው ።

አቡነ ሰላማ ፡ እምንታ አይሉት አሉታ ፡ አውንም በከንፈራቸው ውስጥ ከአጉመተመቱ በኋላ ፡ “ ግና ” አሉ ግልጽ በሆነ አነጋገር ፡ “ አምላካችን ሁሉንም በየሥራው ደልድሎታል ። ሙሴ የእሥራኤልን ሕዝብ እንዲመራ ሲመርጠው ፡ አሮንን ደግሞ ለቤተ ካህናቱ መድቦታል ።”

“ እውነትዎን ነው አባታችን ” አሉ ቴዎድሮስ ፡ በሐሳባቸው ሳለው ጉዳይ አውን ደጎና መንገድ የተከፈተላቸው መሰላቸው ። “ እንዳሉትም ፡ መጽሐፉም እንደሚነግረው እግዚአብሔር አሮንን ለክህነት መረጠው ። ግና ስንት ዕልፍ ዕማዕላፍ ለሆነው ለቤተ እሥራኤል ሕዝብ ካህን ሆኖ የተሾመው አሮን ብቻ ነበር ። ባገራችን ግን እንደሚያዩት አገር ምድሩ ካህን ነው ። ዝም ብሎ የሚቀለበው ሁሉ እየሠራ ቢያድር ምን ይመስል ዎታል ? ” ሲሉ ጠየቁ ።

አቡነ ሰላማ ፡ መልስ መስጠት ባያቅታቸውም ከራሳቸው ይልቅ በዚያ አዳራሽ የተሰበሰበው አብዛኛውን መኳንንት የበለጠ እንደሚቆነጥጠው በመገመት ለጥቂት ጊዜ ዝም ብለው ጠበቁ ። “ መቸስ ቢሆን ቤተ ክርስቲያን ሁላ ይዳፈን አይባል ። ዛዲያ ፡ ለጧት ኪዳን ፡ ለምሽት ቁርባን ፡ ለቅዳሴ ፡ ለማኅሌት ፡ ቤተ ክርስቲያን ያለ አገልጋይ ካህናት እንዴት ቤተ ክርስቲያን ትሆናለች ? ” አሉ በመጨረሻ ።

“ቤተ ክርስቲያን ይዳፈን አልወጣኝም ። ያልታሰበ ነገር አያምጡ ” አሉ ቴዎድሮስ ትንሽ የመበሰጫጨት ቃና ባዘለ አነጋገር ፡ “ በአንድ ቁስ ፡ በሁለት ዲያቆን ፡ በምስት እንደሚቀደስ እናውቃለን ። ቢበዛ በሁለት ቁስ ፡ በሦስት ዲያቆን ፡ በአምስት ይሁን ። ከዚህ በተረፈ ሥራ ፈትቶ እየተቀለበ የሚንጋጋው ሁሉ ምን ይጠቅማል ? ደሞስ እንድ ሰን በት ጧት ለመቀደስ ሳምንት ሙሉ ሥራ ፈትቶ መቀመጥ ምን ይባላል ? እኔምኮ ብችል እንደ ጻድቁ ዮሐንስ ፡ የሕዝቤን ገንዘብ ባልነካ ሰሌን እየ

ሠራሁ እየሸጥኩ ብተዳደርና ባስተዳድር ደስ ባለኝ ነበር ። ይኸ ሳይሆንልኝ ቢቀርም ፡ ሠራዊቴ ግን እንዳለፈው ጊዜ በየጢሱ እየተመራ ወይንም ያገሬን ገበሬ ሞሰብ እየደፋ ሳይሆን ፡ በቀለብ ሥራት የሚተዳደርበትን ደንብ ገና አወጣለታለሁ ። በሠጠኑት አገሮች እንደዚህ ነው የሚደረገው አሉ ። ስለ ቤተ ክርስቲያን የሆነም እንደሆነ ፡ ላንድ ቤተ ክርስቲያን ፡ በዛ ቢባል አምስት አገልጋይ እየተመደበለት ፡ ሌላው ካህን ነኝ ባይ ሁሉ ፡ እርሶ ፡ ነግዶ ፡ ወይም በሌላ ሙያው ሠርቶ እንደሚኖር ነው ያለኝ ሐሳብ ።”

ስለ ጻድቁ ዮሐንስ ሰሌን ሥራ ሲነገር ፡ በአድናቆት ከንፈሩን እንደ መምጠጥ እያደረገ ፈገግታ አሳይቶ የነበረው መኳንንት የምጽአት መዓት እንደ ሰማ ያህል በድንጋጤና በግራሚ አተመመ ።

“ ስንት ባሕታውያን የዘጉበትን ገዳም ፡ ስንት የቅኔ ፡ ያቋቋም ፡ የድጓ መንበር የተዘረጋበትን ደብር እንዴት እንዲህ ይሁን ይባላል ? ” ሲል ጠየቀ አንድ መኰንን ።

“ መቸም የተቸገረ ጠፍ ደብር ነው በሦስት የሚያስቀድሰው ። ለሆነለትማ ፡ ሰባትም ፡ ዐሥራ ሁለትም ፡ አውን እርስም የነገሡበት ደረ ስጌ ከሰባት ባነሰ ዓመት ባል ተቀድሶበት አያውቅም ” ሲል ጠቆመ ሌላዉ በተራው ።

“ መቸምኮ ፡ ለቤተ ክርስቲያን የሚያገለግለው ካህን ብቻ አይመ ስለኝም ። ከዚህ ከአባታችንና ከጨጌው ጀምሮ ትልልቆቹ ሊቃውንት ያለረድዕ አይሆንላቸውም ። እንዲያውም እንደ ጨዋ ገበሬ ይንከላወቱ ካልተባለ በስተቀር ! አውንም የሆነ እንደሆነ ፡ ቤተክሲያንም ከቀዳሹ ፡ ካወዳሹ ጋራ ሌላው ቢቀር ገበሬ መበለት አለው ፡ ባገራችን ” አለ አንዱ ደግሞ በማብራራት ።

ድንገት ቀርው እንደ ተነካበት ንብ ፡ ተራ ሳይጠባበቁ መኳንንቱ ፡ ከዚያም ከዚያም እየተነሣ ጥያቄውንና አስተያየቱን በላይ በላዩ አደራረበው ። ቴዎድሮስ ፡ ባንድ በኩል ላገር ይበጃል ብለው የቀረቡት ሐሳብ መኳንንቱ ለምን በመጥፎ እንደ ተመለከተው እየገረማቸውና እንደ መበሳጨትም እያሉ ፡ በሌላ በኩል ደግሞ በመጨረሻ የሁሉንም አጠቃልለው በጥሞና ለማስረዳት ትዕግሥታቸውን እየጨመቁ አዳመጡ ። ከሐሳባቸውና ከቃላቸው የማይወጡት የቅርብ ባለማሎቻቸው በመካከሉ ግራ ተጋብተው አንድ ጊዜ ወደ ቴዎድሮስ በጭንቀት ዐይነት ሲመለከቱ ሌላ ጊዜ ተናጋሪውን በቁጣ ይገላምጣሉ ፡ አልተገፋላቸውም ።

ቴዎድሮስን ጠቅ የሚያደርግ ጥያቄና አስተያየት በተሰነዘረ ቁጥር አንዳንዱ ፡ “ አሰይ ! አበጀህ ፡ እንዲያ ነው እንጂ ! ” እያለ በሆዱ ሲቅበጠበጥ በግልጥ ያስታውቃል ። በአንድ ጊዜ ብዙዎች ለመናገር ሲነሡ ፡ እንደ ቆረፈደ ቆዳ የሚንቋቋ ድምፅ ያለው አንዱ ቀደመ ።

“ የጠቢያ ሕዝብ ክርስቲያን ነው ። ያዕቆብ የሚባለው ካቶሊክ ባገራችን ምን ይሠራል ? ተዚህ ላይ ደሞ አሁን አጤ ፥ ቤተክሰያን ይዳፈን ሲሉ ፥ እኔ በውነቱ ለማተቤ ፥ ለዚች ለማተቤ ብሞትሞ ግዴለኝ ” አለ እንደ መቁነጥነጥ እንደ መንቀጥቀጥ እየታጣው ። የቴዎድሮስ ዐይን ድን ገት እየቀላ ሔደ ። “ አሁንም የሆነ እንደሆነ ፥ አሁን የታሰበው ግን መና ፍቅነት ” ብሎ ንግግሩን ሳይጨርስ ፥ መጨረሻ የተናገራቸውን ቃላት ሁሉም ሰው በሚገባ ሳያዳምጠው ፥ ቴዎድሮስ እመር ብለው ቆሙ ።

ስስ ከንፈራቸው እየተንቀጠቀጠ ፥ በስስ ከንፈራቸው ጠርዝ ድንገት አረፋ እዬወጣ ፥ ተፈናጥረው ተነሥተው ጐራዲያቸውን እስከ ጫፉ አጠገብ ድረስ ላጥ አደረጉት ። እፍ እንደ ተባለ መብራት እርጭ ባለው አዳራሽ ውስጥ “ መይሳው ካሣ ! ” የሚለው ድምፅ እንደ ነጐድጓድ አስተጋባ ።

ታንጉት ፥ በዚያ ጐራዴ መላ ሰውነቷ የተሰነጠቀ መስሎ ተሰማት ። ድንጋጤ ይሁን ፍርሃት አልታወቃትም ። ብቻ ካለችበት ደረቅች ። በቅጽበት ተዋበች ተፈናጥረው ከቴዎድሮስ ወገብ ሲጠመጠሙ ፥ በአጠገብ የነበሩት እነገብርዬ ፥ እነዓለሜ ፥ እነእንግዳ ተረባርበው የተመዘዘው ጐራዴ ጨርሶ ሳይወጣ ፥ ቴዎድሮስም ሌላ ቃል ከፍ አርገው ሳይናገሩ ፥ በጓደኝነት ገሥጸው ከባብበው ወደ እልፍኝ ሲወስዷቸው እላየችም ። ዐይኖቿን በመዳፍዋ ሸፍና ሐሳብዋ በተመዘዘው ጐራዴ እንደተተከለ ነበር ። ዐይንዋ ግልጥ ፥ አእምሮዋም መለስ ሲል ወደ እልፍኝ ሔደች ። የመጀመሪያዋ ጊዜ ባይሆንም አሁን ግን ለምን እንደሆነ ምክንያቱን አላሰበችውም ነበር ። እግርዋ እንደ መራት እንዲሁ ሔደች ። ሳታስበው ደርሳ ገርበብ ካለው በራፍ ግማሽ አካልዋ እንደ ገባ ድንገት ቆመች ።

ተዋበች ፥ ከቴዎድሮስ እግር ሥር ተንበርክከው ሁለት ቋንጃቸውን በማቀፍ ከታሩቸው ላይ ደፋ ብለው በጭንቀትና በፍቅር ይማጠናሉ ። “ የኔ ጌታ ፥ ኧረ ባክህ የኔ ጌታ ! ለምን እንደዚህ ትናደዳለህ ? ” የቴዎድሮስን ቋንጃ ጭምቅ አደረጉት ።

የንዴት ትንፋሻቸው እንደ ነበልባል በአፍንጫቸው ቡል ቡል የሚለው ቴዎድሮስ ጉልበታቸውን ለመገፍተር ቃጣውና መለስ አድርገው ፥ “ ተሰደብኩ ፥ ሰደበኝኮ ! ምን ላርግ ብለሽ ነው ተዋቡ ? ” አሉ ምርር ባለ አነጋገር ፊታቸውን በሁለት መዳፋቸው እየፈተጉ ።

“ የኔ ጌታ ! ዛዲያ እንደዚህ ይኮናል ? ”

“ ስድብ አልወድም ! ” እንደ መወራጨት ቃጣቸው ።

“ እህ ! መቸስ ምን ይደረግ ? ”

“ እናቴም ! እናቴም ያች የምወዳት እናቴም ትመክረኛለች ፥ ትገሥጸኛለች ፥ ትቆጣኛለች እንጂ የሚያዋርድ ነገር ሰድባኝ አታውቅም ። ” ፥ “ አሁን የተናገረው ምን ስድብ አለበት ? ”

“ መናፍቅ ብሎኛል ። ”

“ እኔ እንደ ሰማሁት ‘ መናፍቅነት ነው ’ነው ያለው ። እባክህ የኔ ጌታ ! ”

“ ያው ነው ! ! ” ቴዎድሮስ ጥቂት ተወራጩ ።

“ ኧረ ባክህ የኔ ጌታ ! ያው አይደለም ። እንተን መች አለህ ? ”

“ እም ያው ነው ! ሐሳቡን መናፍቅነት ነው ካለ እኔን ሰድቦኛል ። አገሬ ትልቅ እንድትሆን ባሰብኩ እኔን የሰደበኝ ደሞ አገሬንም ሰድቧል ! ”

“ ታዲያስ መቸስ እየቻሉ ነው እንጂ ! ”

“ የጭንት ከብት ብቻ ነው ቻይ ! ”

“ ኧረ ባክህ ተው የኔ ጌታ ! ” አሉ ተዋበች ፥ ፊታቸውን ቀና እድርገው ዕንባ ባቆረዘዘ ዐይን ተማጠኗቸው ። “ ራስህ ምከር ፥ ሐሳብ ጠይቀህ እንዲህ ስትሆን ምን ይባላል ? ያለ ትዕግሥት አገር ይዛል ? ”

“ በምክር ላይ ዛዲያ ዘለፋን ምን አመጣው ? ”

“ ምናልባት ደግ አሰብኩ መስሎት ይሆናል ። ”

“ ለምን ሐሳቢ አይገባቸውም ተዋቡ ? ” ከንዴት ይልቅ አጠያየቃቸው የብስጭት ነበር ።

“ እነሱ የሚያውቁት የለመዱትን ። አንተ እንዳልከው ፥ በአባቴ ዘመንና ተዚያም በፊት እንሥቶ መኳንንቱም ፥ ሰዉም ግምኛ ሆኖ ከቆዩ ፥ አሁን አንተ ላገርህ ትልቅ ሐሳብ ስታመጣበት ባያውቅልህ ምን ትፈርድ በታለህ ? ”

በተዋበች አነጋገር ተረትተው ቴዎድሮስ በሐሳብ ራሳቸውን አወዛወዙ ። “ ዛዲያ ምናርግ ትይኛለሽ የኔ መቢት ? ” ሲሉ በትካዜ እንደ በት ጠየቁ ። “ ያገሬ ነገር ሆኖብኝ ነው እንጂ ለኔና ላንቺ ሆድማ ፥ ቋራ አውፊ አድነን ብንበላ መች ያንሰን ነበር ? ”

“ እረቲ ! ዛዲያ ታጋሽ መሆን ነዋ ! በትንሽ በትልቁ ቢቆጡ ፥ ቢናደዱ ፥ አሁን እንዳረከው ብታረግ ፥ ሰውን ከማስበርገግ በቀር ፋይዳም የለው ! ” ተዋበች ከተንበረከኩበት ልጥጥ ብለው ፥ እንደ ማስተካከል ዐይነት የአዲ ቴዎድሮስን ቁንዳላ ዳበስ ዳበስ ያደርጉት ጀመር ። ቴዎድሮስ ዐይናቸውን በሐሳብ ክደን እድርገው ፥ የሚሽታቸው ለስላሳ ትንፋሽ ሲያ ባብላቸው ንዴታቸው በረድ እያለ ሔደ ።

“ እባክህ ፈጣሪዬ ፥ ትዕግሥቱንም አክለህ ስጠኝ ! ” አሉ በታ ክተ አነጋገር ። “ አንቺም እስቲ ተዋቡ የመታገሻውን መላ አስተምሪኝ ! ” በበኩላቸው የሚሽታቸውን ትክሻ ዳበስ ዳበስ እደረጉት ።

“ አሁን እስቲ ዐረፍ በል የኔ ጌታ ” አሉ ተዋበች ፥ ከንብርክካቸው ተነሥተው ፥ ዋልባቸውን እየነቀሱና ፥ ቀይ የሐር ቀልቢያቸውን እየፈቱ ።

“ እንቺም እስቲ ዐረፍ በይ የኔ እኅት ፣ አንቺንም ጨምሬኮ መከራ ሥቃይ አሳየውሽ ” ሲሉ የሚሽታቸውን ፊት በትካዜ ፍቅር አተኩረው ተመለከቱ ።

“ ለኔ ግዴለም እስቲ አንተ ዕረፍ ” አሉ ተዋበች መቀነታቸውን እየነካኩ ። ታንጉትን ከበሩ ላይ ቁማ ያዩዋት ፣ መዘጋቱን ለማረጋገጥ ዐይናቸውን ወደበሩ በመለሱ ጊዜ ነበር ። ታንጉትንም “ ምን ሆነሽ ነው ተሱ የቆምሽው ? ” ሲሉ ጠየቋት ። እነጋገራቸው ከግማጼ ይልቅ የማ ፈርና የመገረም ቃና ነበረበት ። ቴዎድሮስ ዝም ብለው አስተዋሏት ። በሌላ ሐሳብ ውስጥ ይመስላሉ ።

“ እኔማ — እኔማ አባ ታ — ታጠቅ . . . ” አለች ታንጉት የምት ናገረው ጠፍቷት ።

“ ምንም ነገር የለም ! ሲናደድ ታውቂው የለ ? ” ሲሉ ተዋበች አሰናበቷት ።

ታንጉት ‘ አላውቅም ’ ማለት ታጣት ። ስሜቷ የተቀላቀለ ነበር ። በሁለቱ ሕይወት ላይ በማጮለጉዋ ኃፍረት ተሰማት ። ለጊዜው በሁለቱ መካከል የማትፈለግ መሆንዋ ደግሞ አናደዳት ። ‘ በፊት የማውቀውስ እኔ ነበርኩ ! ’ አለች በሆድዋ ። ደረጃውን እየተንደረደረች ስትወርድ ፣ ገብርዬ ከግቢ መውጣቱን አላረጋገጠችም ፤ አልጠበቀችም ፤ ሩጫ በከጀለው አረማመድ ወደ ቤትዋ ሔደች ።

ገብርዬ ቤት ሲመጣ ፣ ታንጉት የአዘቦት ልብሷን ለውጣ ፊቷን በጣ ትዋ እየጠቋቆመች ከመስታወቷ ጋር ስትጫወት አገኛት ። “ አህ ? ” አለና ከጉንዋ ተቀምጦ በቀልድ ዐይነት ፊቱን ከመስታወቱ ትይዩ አስ ተካከለ ። ታንጉት ፣ ጉንደር እንደ ሰንበተች ስናር ድረስ ከሚመላለስ አንድ ነጋዴ ዘንድ ከአገኘቻቸው ዕቃዎች አንዱ ፣ ቁመቱ ወደ ከንድ የሚ ጠጋ ፣ ወርዱ ስንዝር የሚያክል መስታወት ነበር ። ዱሮ ፊትዋን በውሃ ውስጥ እያየች በደስታም በቅሬታም ትጫወት እንደ ነበር ሁሉ አሁን መስታወቱ ብርቅየ ሆኖባታል ። ገብርዬም ድንገት ቤት ሲገባ ብዙ ጊዜ ከፊቷ ደቅናው አግኝቷታል ። አንዳንድ ጊዜ ከራሱዋ ጋር ትግግል ለች። ሌላ ጊዜ ከምስሏ ጋር ፊቷን አኩፋትራ የምትሽሚጠጥ ትመስላለች።

ገብርዬ በመጠኑ አጠርና ሰፋ ካለ ፊቱ ፣ ዘወትር ከሚያፈጡት ጠባብ ዐይኖቹ ፣ አጠር ብሎ ቀዳዳዎቹ ሰፋፊ ከሆኑት አፍንጫዉ ፣ ወፈርፈር ካለ ከንፈሩ ፣ በጉልማሳነቱ በጓደኞቹ ዘንድ ‘ ሰደፍ ’ ወይም ‘ ሰፌድ ’ አገጭ የሚል ስም ካሰጠው ሰፊና ጠፍጣፋ ቢጤ ከሆነው አገጩ ፣ በመጠኑ ከርደድ ብሎ ጥቅጥቅ ያን ከመሰለው ጉፈራው ጋር ተፋጠጠ ። ወዲያውም በጠይምነቱ መኻል እንደ ማሽላ ቆሎ ድንገት የሚፈክውን ጥርሱን በፈገግታ ገለጥ አደረገና ወደ ታንጉት አምሳያ አተኩረ ። ቆንጆ እንደሚባሉት በጣም ሰልከክ ሳይል ከበብ ያለው

የፊት ቅርጽዋና ከእርሱ ገለጥ ብሎ እንደ ውሃ የጠራው ጠይምነቷ ፣ ከንፈሮቿን በፈገግታ ሳብ ስታደርግ ከጉንጮቿ ላይ ከሚወጡት ስርጉ ዶቿ ጋር የልጅ ውበት ፣ የልጅ ለዛ ይሰጣታል ። ደስ ያለችው ፣ በልቡ የደስ ደስ ያላት ልጅ ናት ያለው ፣ ገና ዳራ ከካማ ጋር ሲገናኝ ያያት ዕለት ነበር ። አለተለወጠችም ። ስለ እርሷ ደም ግባት ያለው አስተያየትም አል ተለወጠም ። ዐልፎ ዐልፎ ጣል ጣል ያደረገባት የኩፍኝ ጠቃጠቆ በንኳ እንደ ማርያም ስሞሽ አንዳች ዐይነት ውበት ጨመረላት እንጂ አልቀ ነሰባትም ። ሌላ ጊዜ በመስታወቷ ውስጥ ሲፋጠጣት እንደምታደር ገው አሁን ግን ስርጉዶቿ በፈገግታ አልወጡም ።

“ ምን ሁነሻል ? ” ሲል ጠየቃት ።

“ እህ ? ምንም አልሆንኩ ! ” አለች ቅዝዝ ባለ አንጋገር ።

“ በሹመቴ ደስ አላለሽም እንዴ ? ”

“ ለምን ደስ አይለኝም ? ”

“ ዛዲያ ሐሳብ የገባሽ ትመስያለሽ ። ”

“ ይሽን ነገር የሚያጠፋልኝ ነገር ቢኖር ! ” አለች ድንገት ችግ ርዋ የተገለጠላት ይመስል የኩፍኝ ጠቃጠቆዋን በጣቷ እየጠቋቆመች ።

“ አብሮሽ የኖረውን አሁን አስጨነቀሽ ? ”

“ ሲያስጠላኝስ ? ”

“ ዛዲያ አላስጠላብሽ ! ” አላት የስርጉድ ቦታዋን ጠቅ እያደረገ ። መልስ ሳትሰጠው መስታወቱን አስቀመጠችው ።

“ እውነት አንድ ነገር ሆነሻል ታንጉት ? ” ሲል እንደገና ጠየቃት።

“ እኔስ ምንም አልሆንኩ ። ግና አስፈራኝ ! ” አለች ታንጉት ከሐሳብ ማመንታት ጋር ።

“ ማን ? አባ ታጠቅ ? ”

ታንጉት ፣ በአወንታ መልክ ዝም አለች ።

“ ይህን ያህል ዘመን አብረሽው ኑረሽ እታውቂውም ? ”

“ እንደዚህ ሲሆን ? ” ታንጉት መልሳ ጠየቀች ።

“ እንቺ የምታውቂው ፣ በቤት ፣ በጉረቤት ፣ በሠፈር ተሆነ ከሁላ ችን የበለጠ ታጋሽ ነው ። በወርነት ፣ ላገሩ ባለው ሐሳብ ደግሞ ሌላ ይሆ ናል ። ጦር ሜዳ ላይ አላየሽውም ? ”

“ እንደዚህ ? ” አለች ታንጉት ስቅጥጥ እያላት ።

“ ምን መሰለሽ ታንጉት ። ” ገብርዬ በማባበል ትከሻዋን በእጁ ጨበጥ አደረገ ። “ ካማ እንደ ቀድሞው ካማ ልበለው ደግነቱ ትልቅ

ነው ። ዓላማው ትልቅ ነው ። በዚያው መጠን ቁጣውም ትልቅ ሊሆን ይችላል ። ”

“ እና . . . እንደዚህ ትልቅ እንቅፋት ሲያጋጥመው ደሞ ፣ ” ሐሳቧን አቋረጠችና ፣ “ እኔስ በጣም አስፈራኝ ! ” ሌላውን ሐሳቧን ሁሉትታ ።

“ ታወቅሽው እትፈሪውም ! አሁን ይኸን ተይውና ሰው መምጣቱ አይቀርም ። ጉድ ጉድ ብትይ ይሻላል ። አባ ታጠቅ እንዳለው ጉንደሮች የሚፈትሹሽ ዛሬ ነው ። ”

ሁለቱም ከደርብ ሆነው በበር በኩል ወደ ውጭ በኩል ሲመለከቱ እንኳን ደስ ያለህ ለማለት የሚመጣው የመጀመሪያው እንግዳ ከግቢው በር ደርሶ ነበር ።

—4—

ገብርዬና ታንጉት ፣ ስለ ሹመቱና ስለ ቴዎድሮስ በሚነጋገሩበት ጊዜ፣ ከግንቦቹ ግቢ በሰተምዕራብ ትንሽ ወጣ ብሎ በግምጃ ቤት ማርያም ሠፈር ሁለት ሰዎች እንደነርሱዉ ስለ ሹመቱ ፣ ስለ ቴዎድሮስና ስለነገ ብርዬ በመነጋገር ላይ ነበሩ ። ከጥሞና ጭውውትም ወደ ተጋጋለ ክርክር እያዘነበሉ ናቸው ።

ደብተራ አክሊሉ ፣ ከጋረድ ቤት የመጣው ቀደም ብሎ የሹም ሽሩ ስብሰባ ገና መበተን ሲጀምር ነበር ። የጋረድ ቅጥር ሚስት ፣ ጋረድ ገና እንዳልተመለሰ ስትነግረው ፣ ትንሽ እንደ ተቅበጠበጠና እንደ ተቁነጠነጠ ቆይቶ እንደ ቤተኛነቱ በምድር ቤቱ ገባና ፣ በደርቡ ሰገነት በኩል ሲመለከት የግቢው አካባቢ ጭር ማለት ጀምሯል ። ሥነ ሥርዓቱ እንዳበቃ ወወቀ ። “ እኮ የት ቆየ ? ” አለ ከራሱ ጋር ፣ ጥርጣሬም ፣ የቸኮላ ብስጭትም ተሰማው ። ‘ ደኅና ሹመት አግኝቶ ተስማምቶት ፣ በዚያው ለምከክር እልፍኝ ገብቶ ከቴዎድሮስ ጋር ቆይቶ ይሆን ? ይህማ ተሆነ ስንት የለፋ ሁበት ነገር ሁሉ ተመልሶ ከንቱ መሆኑ ነዋ ! ወይስ ወደዚያች ጋለሞታ ወዳጁ ዘንድ ሔዶ ይሆን ? ነገሩን ማወቅ መሻቴን እንዴት ችላ አለው ! ግን ከዚያች ጉንደርን ከአፋጀች ጋለሞታ ወዳጁ ዘንድ ከሔደ ቢናደድ ነው ’ ሲል አሰበ ። እንዲሁ መጠበቁ አላስችለው አለና ፣ በዚያው አቅራቢያ ወደሚገኙ አንዲት የሚያውቃቸው መሻች ቤት ሔዶ ፣ አረቄውን እየደጋገመ ሲጠጣ ቆይቶ ሲመለስ ጋረድ ለጥቂት ቤት እንደ ገባ ደረሰ ።

“ የት ጠፋህብኝ ልጅ ጋረድ ? ” አለ ደብተራ አክሊሉ ፣ ከጥያቄ ይልቅ አረቄ በገፋፋው ግሣጼ አንጋገር ። የነጠላ አለባበሱ ሳይቀር ዝር ከርክ ብሎ ነበር ።

“ የት ጠፋው ? ” ሲል ጋረድ በማፍጠጥ መልስ ጠየቀ ። የጋረድም ቀይ መልክ በሞቅታ ወይም በሌላ የስሜት ሙቀት ጉበት መስሎ ከግንባሩ ላይ ጅማቶቹ ተገታትረው ነበር ።

“ አሄሄ ! ዐውቁብሃለሁ የት እንደ ጠፋህ ! የእንተ ጉርምስናና ወንድነት መቸ ይሆን የሚበርደው ? ” አለና በንደኝነት ትከሻውን እንደ መታቀፍ አድርጎ ከአጠገቡ ተቀመጠ ።

“ እባክህ ምንላርግ ዛዲያ ? ” አለ ጋረድ ከቁጣ ወደ መኩራራት መለስ ብሎ ።

“ እረ አበጀህ ወንድሜ ! ” አክሊሉ የጋረድን ትከሻ ጠብ ጠብ አደረገ ፣ ቅጥር ሚሽቱ ወደ አለችበት ጓዳ በዐይኑ እያመለከተ ፣ “ ለመሆኑ ታውቃለች ? ” አለው በጥያቄ ሳይሆን የአድናቆት ምሥጢር በሚገልጽ ሹክሹክታ ። ጋረድ እኔ ምን ችገረኝ በሚል እኳኋን ትከሻውን ሰበቅ አደረገ ። “ ብቻ ጠንቀቅ ነው ። ገና ብዙ ዕድል የሚጠብቅህ ሰው ፣ የቀናተኛ ሴት ነገር አይታወቅም ልጅ ጋረድ ! ” አውንም ትከሻውን እንደ ማቀፍ አደረገው ።

“ እሺ እንዴት ነበር ? ” ሲል አክሊሉ በጉጉት ጠየቀው ።

“ እረ ተወኝ ! ሕዝብ አዳሜ ተፋጀእንጂ ! ካሣ ለየለት !! ” አለ ጋረድ በንዴት አነጋገር ።

“ እንዴት ? ”

ጋረድ የሆነውን በአጭሩ ተረከለትና ፣ “ እኔምኮ ፣ ያ — ፈንጠሬ ለጥቂት ቀደመኝ እንጂ ተነሥቼ ልክ ልኩን ልነግረው ነበር ” በማለት ፎከረ ።

አክሊሉ የደስታ ፣ የተሰፋ ስሜቱ እየፈካ ሔደ ። ጋረድን ቀስ እያለ ከጎፋፋው ፣ ከአሰበው ድረስ ይሔድለታል ። ትንሽ መጠጥ ቢጨመር ደግሞ ሁለቱንም የበለጠ ያደፋፍራቸዋል ። “ ዛዲያ የሹመት ቀን እኮ ነው ። ድግስም የለ ተቤትህ ? ” አለ በቀልድ መልክ ።

“ ኧረ — ኤጭ ! ” ጋረድ እንደ መወራጨት አለና መለስ አድርጎ ፣ “ ያንንስ እንተወውና ፣ ነገሩ ራሱ ያስጠላል ። አንች ግንሽ ! የሚጠጣ ነገር አምጭልን ። ምግብ ብጤስ ትቀምሳለህ ? እኔ እንደሆነ የዚያ ርጉም ግብር ልውጣ እያለ ይተናነቀኛል ። ”

“ እኔም አላስኘኝም ! ለመሆኑ ምን ተሾምክ ? ”

“ ምኑን ብዬ ልንገርህ ? ”

“ እህ ? መቸም ተሹመሃል ! ”

ጋረድ በምሬት ከት ብሎ ሣቀ ። “ አዎ ! መንገድ ላይ ትቸው መጣሁ እንጂ ፣ የፈታውራሪ ቀሚስና ወገራን ! ”

“ ወገራን ! ስሜንንም ፣ ወልቃይት ጠገዴንም ሳይጨምር ? ”

“ እንደ ቤት ውሻ ተሥሮ ተሥሩ ቱስ ቱስ ተሚሉት እንትናቹ በተቀር ሁሉም እንደዚሁ ነው የደረሰው ። የተግሪ ቱራሽ የምታካክል አገር ። ”

“ ወገራ ? የደጃች ክንፉ ልጅ ወገራን በካጣ ይሾም ? ወቸው ጉድ ! ዛዲያ አየህልኝ አይደለ የሱን ነገር ? ”

“ ሽቅብ እስቲለኝ ነዋ ! ”

“ በፊትም እኮ ነግሬህ ነበር ። ዘመዶቹን ነው ቀድሞ የሚጉዳ ፣ በእንተ ወንድሙ ላይ ነው ተቀዳድሞ የሚነሣ ብዬ ! ”

“ ምን በደልኩት ? አባቴስ ምን በደሉት ? ”

“ ምንም ! ምንም ! ” አለ አክሊሉ ንግግሩን በመርገጥ ። “ ደጃች ክንፉ ፣ በሰማይ ነፍሳቸውን ይማርና ፣ እኛ ደጉ ሰውማ ፣ ታንተ ሳይለዩ እንዳንተ እንደ ልጃቸው አቀማጥለው አሳደጉት እንጂ ደሞ ምን በደሉት ? በፊትም ነግሬሃለሁ ” አለ በድጋሚ አክሊሉ ።

ጋረድን በቴዎድሮስ ላይ ለማስነሣት ልቡን ማሻከር የጀመረው ገና ራስ አሊ ድል ከሆኑ ጊዜ እንሥቶ ነበር ። መጀመሪያ በእግድሞሽ አነጋገር በንቅስ ወጥቶ የአዲሱን የአስተዳደራቸውን ዐዋጅ ባስነገሩ ጊዜ ሁለቱ ወደ ዳር ሆነው እየተመለከቱ ፣ ‘ አሁን ማ— ይሙት እንተ እያለህ እርሱ ተዚያ ላይ ይውጣ ? ’ ሲል በግልጽ ነገረው ። የጋረድም ልብ በምኞት ወደ ግንቡ ሰገነት ወጣ ። የሙኅሳ ማር እየቀባ ዘወትር ተስፋ ሲመግበውም ፣ የጋረድ ምኞት በዚያ ሰገነት ላይ እንደ ተንጠለጠለ ቆይ ታል ። የአክሊሉ ሥጋት ጋረድ ደኅና ግዛት ይሾምና ልቡ ይረካ ይሆ ናል የሚል ነበር ። ሥጋቱ ሳይደርስ ቀረለት ።

“ ዛዲያ በምን ምህኛት ነው ? ” የሚለው የጋረድ ጥያቄ አክሊሉን ከሐሳብ መለሰ አደረገው ።

“ በምን ምህኛት ? ቅናት ነዋ ! ምቀኝነት ነዋ ! ሰው መቸም በሚ በልጠው እንጂ በሚያንሰው እንደማይቀና ታውቃለህ ። ትንሽ ሰው ምኑ ይፈራል ? ምኑስ ይቀናበታል ? ዛዲያ አሁንም የሆነ እንደሆነ ካማ ባንተ ያልቀናና ያልተመቀኘ በማን ይመቅኝ ? በኔ ሞት ! ወንድ ጀግና ነህ ። በሰማይ ነፍሳቸውን ይማርና ፣ የሕዝብ ፍቅር የነበራቸው የደጃች ክንፉ አንድ ልጅ ነህ ። ለያዘው ሥልጣን ካንተ የተሻለ ማን አለና ! እንዲያውም ፣ እንዲያውም ” አክሊሉ ንግግሩን አጠልዋሎ ተወውና ወደ አረቄ መለኪያዉ ዞረ ።

“ ‘እንዲያውም’ ያልከውን ጨርሰው እንጂ ! ” ጋረድ በበኩሉ አረ ቁውን ተጮነጨ ።

“ እህ ? ” አክሊሉ ለመናገር ያቅማማ መሰለ ።

“ ምን ነገር ከምላስህ እያደረስክ መልሰህ ትውጣለህ ! ” አለ ጋረድ ቆጣ ባለ አነጋገር ፣ ሁለቱም የአረቂዉ ሞቅታ እየተሰማቸው ሒዶ ነበር ።

“ ማለቴማ በነፍስህስ ባይመጣ ! ”

“ ሲገለኝ ? ”

“ እህ ? ልጃቸውን የጻሩለትን ያንን የመሰሉ ጌታ ይሽሙና ታገር አጥፍታቸው የለ ? ደጃች ወንዲራድስ ያንን የመሰለ መኳንን ኮሶ ግቶ አልገደለውም ? ”

“ ሳደበኝ ብሎ ነዋ እሱንማ ! ”

“ ቢሆንስ ! ለምሳሌ አሁን እንገብርዬ ፣ እንገልሞ ፣ እንዓለሚ ፣ እንዲህ ጣራ ሲነኩ አንተ ወገራን በመሾምህ ይምህ ፈልቶ አንድ ነገር ብትናገረው ፣ እንደዚያው መሆንህ አይደል ? ኧረ ጨካኝነትና እብሪት ነው ! ”

ጋረድ ፣ በዚያ የፋሲል አጻራሽ እንደ መብረቅ ብልጭ ብሎ የወ ጣው የቴዎድሮስ ጉራዴ ፣ በራሱም አንገት ላይ ሲያንገጥብብ ለቅጽበት በሐሳብ ታየውና ፊቱን ጨፍገግ አደረገ ። አክሊሉ እንዳያውቅበት ግን ወዲ ያው ፈገግታ አሳዩ ። “ ግና ምን ያህል ብትጠላው ነው እባክህ ? ” አለው አክሊሉን ።

“ ምን አገናኝቶን እጠላዋለሁ ? እርግጥ አልወደውም ። ”

“ ዛዲያ ባትጠላው ነው ፣ ፈረስክን ጫን እንጂ እያልክ እንደዚህ የምትቀሰቅሰኝ ? ”

“ በሱ ጥላቻ ሳይሆን ላንተ ፍቅር ስል ነው ። በሰማይ ነፍሳቸውን ይማርና ለዚያ ለደጉ አባትህ ውለታ ስል ነው ። አንተ ተሱ በታች ውለህ እያየሁ ዝም ብል እጮንታቸውስ አይረግመኝም ጋረድ ? ” በጎዘን ዕን ባው የመጣ ይመስል ዐይኑን ጭምቅ ጭምቅ አደረገ ።

“ ቢሆንም — ቢሆንም ” አለ ጋረድ በትዝብት መልክ ። “ ስለኔ ተኔ የበለጠ የምትጨነቅ ፣ መቸም አንተም ቂም ቢጤ ብትቋጥር ነው ። ”

“ ማን እኔ ? የሕይወታችን ጉዳና ለየብቻ ፣ እኔ ዓለም ነገሩን ትቼ ለነፍሴና ለእግዜር ብቻ ያደርኩ ። እሱ ጊዜ አንሥቶት መሬት ጠበበኝ ያለ ። እኔ እንግዲህ ተዚህ በኋላ ” እያለ አክሊሉ ጥምጥሙን ነካ ነካ በማድረግ አመለከተ ። “ በምድራዊ ሰው ቂም ብይዝ አምላኬስ ይወድ ልኛል ? ” ግን ሳይፈልግ ሐሳቡ ሰንት ዓመት ወደኋላ ተመለሰበት ።

ዐሥራ አምስት ይሁን ኻያ ዓመታት ገደማ ይሆናል ። ትክክለኛዉ የዓ መታት ቁጥር በቴጮት ጭጋግ ተሸፍኖበታል ። ድርጊቱ ግን ከሕይወቱ ጨርሶ አይጠፋም ፤ ውጤቱም እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ እብሮት ይኖራል ።

ካሣ ፣ አክሊሉና እርሻ የሰለቻቸው ፣ ጭቃ ሹምና ምስለኔ ያስመ
ረራቸው ሌሎችም የቅርብና የሩቅ ጉልማሶች ዕድላቸውን በነፍጠኝነትና
በእሽከርነት ለመሞከር ደጃች ክንፉ ቤት በባለሟልነት ገብተው ነበር ።
ደጃች ክንፉ ፣ እናቱም አባቱም ከሞቱ ወዲህ ለካሣ ፣ በአባቱ እንደ ተተኩ
አሳዳጊው የሚቈጠሩ ቢሆኑም ፣ አኗኗሩ ከሌሎች ባለሟሎች እምብዛም
የተለየ አልነበረም ። ከሌሎቹ ጋር ይበላል ፣ አብሮ ይኖራል ፣ አብረው
አደን ይሔዳሉ ፤ ጉግስ ይገጥማሉ ፣ ገበጣ ይጫወታሉ ፤ አንዱ ከሁሉም
ጋር ፣ ሁሉም እርስ በርሳቸው የልብ ወዳጅነት ባይኖራቸውም ፣ አብረው
በመኖራቸው ፣ “ የክንፉ እሽከር ” እያሉ በመፎከራቸው ፣ አብረው
በመዝመታቸውና ጉን ለጉን በመዋጋታቸው ፣ ከሌሎች መኳንንት ባለ
ሟሎች ጋር በየአደባባዩ ፣ በየመሸታ ቤቱ በመፎከራቸው እንደ ባል
ንጀራሞች ይታያያሉ ። ጠባያቸው ባይስማማ ይቻቻላሉ ። በዚህ መካከል
ግን ፣ የካሣና የአክሊሉ ኮከብ ከመጀመሪያ እንሥቶ የማይገጣጠም ሆነ ።
ውቃቢው የነገረው ይመስል አክሊሉ ፣ ካሣ የሚንቀው ይመስለዋል ።
በዚህ ላይ ፣ የካሣ ኩራትና መንጠራራት ያበሽቀዋል ፤ አጉል ድፍረቱ
ያናድደዋል ። ለምሳሌ አንድ ጊዜ ደጃች ክንፉ ለእደን በለሳ ወርደው
ሲመለሱ የመገጭ ወንዝ ሞልቶ ቆያቸው ።

“ ማነው እስቲ የሚፈትሽልን ጉበዝ ? ” ብለው ደጃች ክንፉ ንግ
ግራቸውን ሳይጨርሱ ካሣ ነጠላውን ወርውሮ ዘሎ ገባ ። ወዲያውም
ከአረፋው ጋር ይደፍቅ ጀመር ። ሰው እየተጨጨኸ ፣ ደጃች ክንፉ ፣
“ ዝም ብላችሁ ታያላችሁ ! ኧረ ልጂን ውሃ በላው ! ” ብለው ሲቆጡ ፣
አንድ መቶ ክንድ እንደ ተወሰደ ሦስት ብርቱ ዋናተኞች እንደ ምንም
አወጡት ። ከዚያም ራሱን ዘቅዝቀው ወደ ሆዱ የገባው ውሃ እንዲወጣ
ካደረጉና የተዘፈቀ ልብሱን አውልቀው ሌላ ነጠላ ከለበሱት በኋላ
ትንፋሹ መለስ አለለት ።

“ አሆሆ ! ኧረ እንኳን አተረፈህ ወንድሜ ! አፍላ ሙላትኮ አደገኛ
ነው ። ቆለኞች የውሃ ጠባይ አታውቁም መሰለኝ ! ታዲያ የውሃ ነገር
ለእኛ ለደምቤዎች ? ” ሲል አክሊሉ እንደ ቀልድ ተናገረ — በሆዱ ግን
“ ይበልህ ! የቅብጠትህ ዋጋ ሲያንስህ ነው ! ” ሲል ተመኘ ።

“ ለደምቢዎቹ ? ለጉርኖ ገፈዎቹ ? ለአጎት ዛፈዎቹ ? ታዲያ ምን
ትጠብቅ ነበር ? እጅህ በሶ ጨብጦ ነበር ? ” አለው ካሣ በመጠየፍ አካ
ኋን ከእግር እስከ ራሱ እየተመለከተ ።

“ እጓትኮ ያፋፋል ” በማለት አክሊሉ መለሰ ፣ በቀመሰው እሽሙር
መብሸቁን እንደ ምንም ውጦ ።

“ ገላ ቢያፋፋ ፣ ልብ ያሳላል ! ” ሲል ካሣ ሌሎቹ ተሣሣቁ ። እሽ
ሙሩ ግልጽ ነበር ። ልብ የለህም ማለቱ ነው ። ደጃች ክንፉን ባይፈራ
አክሊሉ ከዚያው በዚያው ፍልሚያ ለመጠየቅ ከጅሎት ነበር ። ግን “ ይህ
መላስህና ቅብጠትህ አንድ ቀን ” እያለ በማጉመትመት ዘወር አለ ።

ደጃች ክንፉ ፣ በእጉል ድፍረቱ ካሣን በመገሠጽ ፈንታ ሽለሙት ።
ከዚያም ፣ “ የመይሳው ልጅ ! ” እያለ በተጀነነ ቁጥር ፣ “ ቆማጣ —
ቆመጥማጣ ” እያለ ትልቅ ትንሹን በዘነጠለ ቁጥር ፣ ብዙው ጉረምሳ
“ ካሣ ኮስታራው ” ሲለው ጊዜ ፣ በሽንጎ ከሽማግሌዎቹ ልቆ ሽማግሌ
ልሁን ሲል ፣ በዘመቻ ከፊቱ እየቀደመ ጥላ በሚጋረድበት ጊዜ አክሊሉ
በካሣ ተፈጥሮ የባሰውን እየበሸቀ ሔደ ።

የጥምቀት ሰሞን እንድ ቀን ፣ የደጃች ክንፉ እሽከሮች ለገና ጨዋታ
ጉፋያ መስጫ መስክ ወጡና ካሣና አክሊሉ በተቃራኒ ቡድን ተሰለፉ ።
ከሠፈር ልጆች በስተቀር በበዓል ጊዜ እንደሚሆነው ፣ መኳንንት ለመመ
ልከት ያልተገኙበት የእዘቦት ጨዋታ ነበር ። አክሊሉ ግን፣ የቡድን አባት
ሆኖ ከካሣ ጋር ሲጋጠም የመጀመሪያው ጊዜ ስለነበር፣ ቁጭቱን ሁሉ የሚ
ወጣበት እንድ አጋጣሚ ያገኘ መስሎ ተሰማው ። በእርግጥም ፣ አክሊሉ
የቡድን ልጆችን እየመራና እያሠማራ ፣ ራሱም ሽንጡን ገትሮ ጥሩ እየ
ተጫወተ ሲረቱ እንደቆዩ ፣ ከሎው አጠገብ በድንገት ከካሣ ጋር ተጋጠሙ።
“ ሚናህን ብያለሁ ፣ ውርድ ከራሴ እንዳትለጋ ! ” አለው ካሣ እሩሩዋን
በእጁ ቀልቦ ። አክሊሉ ፣ ወደኋላው ፈንጠር ብሎ ከልጉ ማምለጥ ወይም
ደግሞ ወደሚናው መግባት ይችል ነበር ። ነገር ግን ፣ “ እስቲ ወንድ ! ”
የሚል ስሜት ላንዳፍታ ከቆመበት ቸኩሎ ያዘው ። ሁለቱም ገናቸውን
አንሥተው ዐይን — ለዐይን እንደ ተጋጠሙ ፣ አክሊሉ ከመመከቱ በፊት
የካሣ ክንድ ውልብ ሲልና ሰማይ ምድሩ ሲጨልምበት አንድ ሆነ ።
ከዚያም በሳንሳ ተሸክመው ቤት ሲያደርሱት ሁሉ አልታወቀውም
ነበር ። በሦስተኛው ቀን ፣ ካሣ ከአክሊሉ ቤት መጥቶ በመጠየቅ ክፋት
አለማሰቡን ገልጾለታል ። አክሊሉ ፈጽሞ አላመነውም ። ማ ይሙት ሁለት
ክንድ ከማይሞላ ርቀት የሊጋበት ክፋት ባያስብ ነው ? እማዋይሽ የተባለ
ችውን ወዳጁን ከአንድ ወር በፊት ሲወሽምበት ለእርሱ ሲል ደግ መሥ
ራቱ ነበር ? አክሊሉ ካሣን ሳያነጋግር ፈቱን ወደ ግድግዳው አዙሮ
ሸኘው ።

አንድ ወር ያህል ተኝቶ ተነሣ ። ከቸቸላ እየተመላለሰ መድኃኒት
የሰጠው ስመ ጥሩው የካይላ ዐዋቂ የዳነ መሆኑን ቢያረጋግጥለትም ፣ እንደ
ወትሮው ሆኖ አለመዳኑን ለማወቅ ጊዜ አልፈጀበትም ። በዚያ ጉርም
ስናው ፣ በዚያ በሚያውቀው ዐመሉ የጭንደርን ቆነጃጅት ሲያይ ፣ አንዳ
ችም እንቅስቃሴ የማይሰማው በመሆኑ በመጀመሪያ ጥርጣሬ ብቻ ነበር
ያደረበት ። አይቶ ፣ አይቶ ምናልባት ከሴት ወዝ ተለይቼ ስለቆየሁ ይሆ
ናል ብሎ ገመተና ዱሮ ወደሚያውቃት እንዲት ጋለሞታ ወዳጁ ዘንድ
ሔደ ። ምንም አልሆነም ። የደጃች ክንፉ ባለሟሎች ፣ በተለይም ካሣ
እንዳያውቁበት በድብቅ እያጠያየቀ የዐይነ ጥላ ክታብ አሠረ ። ጉንድ
ተክለ ሃይማኖት ጠበል ፣ ዋንዛዬና አለፋ መዋት ሔደ ። ስሚ ነው ለተ
ባለው ታቦት ሁሉ ተሳለ ። መጽሐፍ ገላጭ ፣ ቅጠል በጣሽ ፣ ሥር ማሽ
ዐዋቂ ጠየቀ ። አልተሻለውም ፤ በመጨረሻ ፍሬው መፍረሱንና መው

ለድና መከበድ የማይችል መሆኑን ቁርጡን የነገረው አንድ የታወቀ የፈንጂ ወጌሻ ነበር ። ጉዱን ለቅርብ ጓደኛው ስንኳ ሳይናገረው በሆዱ ውስጥ ቀብሮ ያዘው ። ሴሎቹ የዕድሜ እኩዮቹ ፣ ሲያገቡ ፣ ሲወልዱ ፣ ውሽማ ሲያበጁ ፣ በጐንደር ጋለሞታ ሲደባደቡ የሱ እንደዚያ ዝም የማለት ምክንያት እንዳይጠረጠርበት ወደ አንድ የገጠር ደብር ሔዶ ፣ ቅኔ ከቆጣ ጠረና እስከ ጾመ ድጓ ዜማ ካስኬደ በኋላ ጠምጥሞ ወደ ጐንደር ተመለሰ ። እንደ ዋዛ " ደብተራ አክሊሉ " የሚለው ስም ወጣለት ።

አንድ የገላው ክፍል መሞቱን አክሊሉ ማመን ቢፈልግም ፣ መን ፈሱ ለአካሉ ጉድለት አልገዛለት አለ ። የሴት ወዝ ጥማቱ ፣ የሥጋ ፍላጐቱ በተቀሰቀሰ ቁጥር እርሱ ይህን ዋና የሕይወት ክፍል የተነፈገበትን ዓለም 'እጥፋው' የሚል ስሜት ይገሩፋዋል ። ዐቅሙን ገምቶ ሲመራመር ፣ ራሱንም ሲቁጣጠር አስተሳሰቡ ከነገሩ መነሻ ላይ ያተኩራል ። በካሣ ላይ ። እም ! ቀደም ሲል ባልቀደም ባይነቱ ፣ ምኞቱን ጥላ እንደ ጋረደበት ሁሉ በዚያ ገና ጨዋታ ደግሞ ወንድነቱን ቀጥፎበታል ። ዐይነተኛ የሕ ይወት ጣዕሙን አጥፍቶበታል ፤ የወደፊት ዕድሉን አበላሽቶበታል ፤ ይህንን በደል እንደሚበቀል ከራሱ ጋር ደግሞ ደጋግሞ ተማምሏል ። ሲያስብ ፣ መንገድ ሲፈልግ ቆይቶ ወደ ጋረድ የተጠጋበት ዋናው ምክን ያት ይኸው ነበር ...

አክሊሉ ፣ በራሱ ሐሳብ ተውጦ ለጥቂት ጊዜ ዝም ማለቱ ጋረድንም፣ በሞቃት ፈረስ በራሱ ሐሳብ እንዲጋልብ ዕድል ሰጥቶት ነበር ... እር ሱም ካሣም የአንድ ቅድመ አያት ልጆች ናቸው ። ግን ደጃች ከንፉና ልጅ ኃይሉ የትና የት ተገናኝተው ። ልጅ ኃይሉ ከቋራ ጐጥ ሳይወጡ ነው ያረፉት ። አባቱ ደጃች ክንፉ ግን ፣ ከርብ እስከ መተማ ፣ ሰው ብቻ ሳይሆን ዛፍ ቅጠሉ ሳይቀር የሰገደላቸው መኰንን ነበሩ ። ጐንደር የሚ ገቡት ኑጋሪት እያስጐሸሙ ነበር ። አክሊሉ እንዳለው ከትውልድ ትው ልድ ሳያንሰው ፣ ከጀግንነት ጀግንነት ሳይጐድሰው መልክ ከቁመና ጋር ሲኖረው ፣ እንደ አዳኝ ውሻ ከፈቱ እየቀደመ ዕድሉን ምኞቱን የነ ጠቀው ካሣ ነበር ። ገና በእናቱ ጉልምስናው ተዋበችን ለማግባት በጣም ተመኝቶ ነበር ። በውበትዋ ከመነደሩ ሴላ ተዋበችን ማግባቱ የሚከፍት ለት የዕድል በር ወለል ብሎ ታይቶት ነበር ። ራስ አሊ እየሸመገሉ ሔደዋል። የሚተካ ወንድ ልጅ አልነበራቸውም ። ዛዲያ እንዲት ሴት ልጃቸውን ጋረድ ሲያገባ በእግራቸው የማይተካበት ምን ምክንያት አለ ? ምንም ! ግን ካሣ ፣ ቋራና አዳኝ አገር ወርዶ ባኮረፈ ፣ ራስ አሊ ተዋበችን በሚሰት ነት ሰጡት ፤ ተቀደመ ፤ ዕድሉን ተነጠቀ ፤ ደጃች ክንፉ ሲያርፉ ፣ ሲሆን የዋንቱን " ማሩ ቀመስ " አገር ፣ ያም ቢቀር የአባቱን ግዛት ለመሾም ተሰፋ አድርጎ ነበር ። ግን አሁንም ደጃች ተድላ ጓሉን ሳይቀር ወደ መኻል ጐጃም ገፍቶ ቴዎድሮስ ወሰደበት ። በኋላም እቴ በጉልበቱ ካሣ እየበረታ እቴጌ መነንና ራስ አሊ ድል ሆነው ከንመኳንንቶቻቸው ቢበታ ተኑ ፣ ምንም ቢሆን ሥጋ ነውና የአንድ ደጃዝማች አገር እንደሚሾመው

ገምቶ ነበር ። ግን ከባለሟልነት ቁምነገር ስንኳ ሳያስገባው ፣ ከደጃች ውቤ ጋር ለመዋጋት ወገራ ሲዘምት ሳያስከትለው ቀረ ። ካሣ ተቀብቶ አልተወሰደም ፤ ራሱን በራሱ ተቀባ ። ወይስ አክሊሉ እንዳለው እኛ እን ዲቀባ ተመቸነው ? . . .

" እና አሁንም የሆነ እንደሆነ የዚህ ዓለም ነገር ለኔ እንግዲህ ምኔም አይደለ ። እንተ ብቻ . . . " በማለት ጋረድን ከምኞት ሰመመኑ የቀሰቀ ሰው ፣ ቀደም ብሎ ከሐሳቡ ያነቃው አክሊሉ ነበር ።

" እኮ ም ናርግ ትለኛለህ ? ተነሥቼ ልሸፍት ነው ? በምን ሠራዊቴ ነው የማሸንፈው ? ' አያችሁት ወይ ያንን እብድ ፣ አምስት ጋሞች ይዞ ጉራምባ ሲወርድ ' ሲባል እሱም ተዘፍኖበት ነበር ። እና እንደ እሱ አድ ርግ ነው የምትለኝ ? " የጋረድ አጠያየቅ ብስጭት የሰፈነበት ነበር ።

" አላልኩም ። "

" ዛዲያስ ? "

" ቀስ በቀስ ዕንቁላል በእግሩ ይሔዳል ተብሏል ። "

" ሲቆይም ገምቶ ይቀራል ። "

" እንደሱ እንዳይሆንማ ነዉ እኔም የምፈልገው ። "

" እሺ ዛዲያ ምናርግ ነው የምትለው ? "

" እንደዚህ ረጋ ብለን ስንመካከርበትም መልካም " አለ አክሊሉ ፣ የጋረድ ቅምጥ ሚስት ከጓዳ ገባ ወጣ አያለች ለስንተኛ ጊዜ የቀዳችለትን አረቄ እየጨለጠ ። " አየህ ፣ ልጅ ጋረድ ፣ አንተ ጀግንነት አለህ ፤ የሰው መውደድ አለህ ። እንዳልከውም መኳንንቱ ሁላ ከተከፋበት ተአሁኑ መንገድ ከፈተልህ ማለት ነው ። እሱ ባወቀ ። እና ፣ አንተ ነገራችንን በሆ ድህ ይዘህ ውስጥ ውስጡን ተዘጋጅ ፤ እየመረጥክ ሠራዊት አሳድር ፤ ወገራ መሾምህኮ ለዚህ ይረዳሃል ። ከመኳንንቱም ወዳጅ አብጅ ፤ አብዛ ። ሴላውን ለኔ ተውልኝ ። የአንተ ወንድነት የኔ ብልሃት ፣ የፈጣሪ ረድኤት አንድነት ሲሆን ግዴለህም " አለ አክሊሉ ። የጋረድን ትከሻ በማደፋፈር መታ መታ አረገውና ፣ " ታንተ ቤት ' እንኳን ደስ ያለህ ' የሚል እን ግዳ አልመጣም ፣ አሁን እንግዲህ ተገብርዬ ቤት እንሒድ " አለ ።

" ምን ? እንኳን ደስ አለህ ልለው እኔ ተገብርዬ ቤት ? " ጋረድ ድምፁ ተስረቀረቀበት ።

" ምናለበት ? "

" በቁሜ ሙቻለኋ ! "

" አልሞትክም ፤ አትሞትም ፣ አየህ ጋረድ ፣ ' ንጉሡ እንትን ሲሉ ለመላ አጉሃበሱ ' ሲባል አልሰማህም ። ሙያ በልብ ነው ። ሔደህ ቸነገል

ከውና ራስህ ለራስህ ያለህ ክብር አልተቀነሰ ። ለራስህ ነገር ስትል ፀውቀህ ነውና ያደረከው ። ''

'' ባልሒድስ ! ''

'' ብትቀር ገብርዬን አትጐዳው ። ያሰብነውን ነገር ደግሞ እትጠቅመውም ። ''

'' ምህሯቱን አስረዳኝ ! '' አለ ጋረድ ወይኑን እያጉረጠረጠ ።

'' አየህ ፣ ገብርዬ ጦር እዝማች ተሹሞ የለ ? 'እሱን ቢያጣ የካሣ ጎይል ምን ይሆናል ?' ብለህ አስብ ። ስለ ገብርዬ ሐሳብ አለኝ ። ያች ሚሽቱም ገና ባላገር ገራገር ናት አሉ ። ስለርሷም ሐሳብ አለኝ ። እንዳልኩህ ብልሃቴን ለኔ ተውልኝ ! እምነግርህን ስማኝ ! አሁን እንሒድ !'' አክሊሉ ጋረድን በጨርቁ ሳብ አድርጎ ሲያስነሣው እንደገራም ከብት ተሳበለት ።

ከቤት ወጥተው መንገድ ሲጀምሩ ፣ አክሊሉ በሞቅታ ውጋገን ከሐሳቡ ቅኔ ፈለቀለት ።

'' — አያ ጋረድ ጅሌ ከጅልም ጅልሌ ፣
አክሊሉ ሲያቀምስህ የምኞት እሞሌ
አጉል ስትጋልብ ወድቀህ ብትሰበር ፣
መቸስ ምን ይያረግ ፣ እኔ እንደው ነገሬ ተዘያ ተከይሲ ጋር ''
የሚል ። በትኔው ሥምረት ከራሱ ጋር ፈገግ አለ ።

—5—

ታንጉት ፣ ቀደም ሲል የነበረባትን ሐሳብ ዘንግታ ፣ ሞንቀት በሞላበት የደስታና የኩራት ስሜት እንደዚህ ጊዜ ታውካ አታውቅም ። የጉንደር መኳንንትና ወይዛዝርት ፣ ሹመት የሚፈልግ ደጅ ጠኝ ሁሉም አሁን ሚዛኑን አይቶ እንደ ዐቅሙ የሹመት መጠየቂያውን እያስያዘ መጉረፍ ጀመረ ። ከበድ ያልን መኳንንት ነን የሚሉ አንድ ሁለት መኳንንትና ወይዛዝርት ከመኳትና ከሽሀር ጋር ግድጋ ጠጅ እያሸከሙ መጡ ። አብዛኞቹ ዝቅ ያሉት ደግሞ ዐሥርና ኻያ እንጀራ ከድስት ወጥ ጋር ፣ የሆነላቸውም ገምቦ ጠጅና ጠላ አብረው አስገቡ ። ባዶዋቸውን እየፎከሩ ፣ እዩሽለሉ ፣ አልል እያሉ የገቡም ነበሩ ።

ገብርዬ ፣ ከበር ውጭ ሰዎችን እየተቀበለ ፣ 'እንኳን ደስ አለህ' ሰላም ታቸውን በምስጋና እየመለሰ ሲያስተናግድ ፣ ከውስጥ ታንጉት ጓዳ የሚገባውን የበሰለ ነገር ከበለጡ ጋር ከጉረቤት የመጡ የቤት ሠራተኞችን እያመላከተች በየሥፍራው እንዲቀመጥ ታደርጋለች ።

ምን የመሰለ ሙከት ፣ ግድጋ ጠጅ ፣ ሞሰብ እንጀራ ፣ ከሁለት ድስት የዶሮ ወጥ ጋር ይዘው የመጡት እንድዋ ወይዘሮ ፣ በኋላ ራሳቸውን

እንዳስተዋወቁት ወይዘሮ ደብሬ የሚባሉ ነበሩ ። ገብርዬን በተገቢው ከበሬታ ' ሹመት ያዳብር ' ካሉት በኋላ ፣ ውስጥ የተቀመጠውን ሁሉ እጅ ነሥተው ፣ እንደ ቆሙ ታንጉትን ጥቂት አስተዋሏት ። ቁመታቸው ብዙ ወንዶችን ወደታች ሊያስመለከታቸው የሚችል ቢሆንም በደጓሣ አጥን ትና ይህንን ባለበሰ ሙሉ ሥጋ ተውጧል ። ግን ከፊት የቦርሙ ወይም ከኋላ የዳሌ ግርጌ ግፊት እይታይባቸውም ። መላ ቁመናቸው ተመጣጥኖ ፣ ተስተካክሎ የወጣ ነው ። ወደ ቀይ ዳማ የሚያደላው መልካቸው ፣ አሁን የዕድሜ መሥመር ቢታይበትም ፣ በጊዜው ብዙ ወንድ ያፋጅ እንደ ነበር ያስታውቃል ። ዐይኖቻቸው አሁንም እንደ ኮረዳ የሚቁለ ጨለጩ ብሩህ ናቸው ። በዚህ ላይ እንደ ተለመደው የጉንደር ወይዛ ዝርት ሹርባ ሳይሠራ ፣ ወይም በሻሽ ሳይታሰር በእንዝርት ዛቢያ ነቀስ ነቀስ ተደርጎ የተዘረዘረ የሚመስለውና እንደ መስከረም አደይ አበባ ፣ ሽበት በልግሥና የተበተነበት ጉፈሪያቸው ጋር ፣ የለበሱት ሰፊ አረንጓዴ ጥለት ቀሚስና ድርብ ኩታ ፣ ደርባባነታቸውን ተጨማሪ ግርማ ሰጥቶታል ። '' እረ ባባጃሌው ! እንቺ ነይ እንጂ ሳሚኝ ! '' አሏት ዓመት ሙሉ ናፍቆ እንደ ከረመ አክስት ።

ታንጉት ፣ የቴዎድሮስ ማስጠንቀቂያ ትውስ አላትና ፣ ድንገት እዳኝ እንዳየ አውሬ በድንጋጤ ወደ ኋላ በስሜት በረገገች ። ወዲያው ትኩር ብላ ስትመለከታቸው ፈገግታቸው ሳባት ። ጥርሶቻቸው እንደ አካላቸው ያጓጣ ናቸው ። በሌላ ሰው ፊት ላይ ቢሆኑ ፍልጥ ጥርስ ይባሉ ነበር ። ነገር ግን ፣ በወይዘሮ ደብሬ ላይ ትልልቅ አልመሰሏትም ። አብረው የሚሥቁ ከሚመስሉት ዐይናቸው ጋር ተቀናጅተው አንዳች የፈካ ማሽላ አበባ ፣ ቃሙኝ ቃሙኝ እያሉ የሚጋብዙ ዐይነት ናቸው ። ዕድሜ የዘረጉባቸው የፊታቸው መሥመሮች ስንኳ የሚስብ አንዳች ውበት ነበራቸው ። '' እረ ባባጃሌው ነይ እንጂ ! '' ሲሏት ድጋሚ ፣ ጠጋ ብላ ጉንጯዋን እያገላበጠች ሰጠች ። ባዳ እንደሚሰማት አልቀፈፋትም ። በኋላ ቀይታ ስታስበው ራቧም ገርሟታል ። ብዙ ጊዜ ከተለየችው ሰው የተገናኘች መስሉ ነበር የተሰማት ። '' በይ ሒጂ ወደ ሥራሽ ! '' ብለው ወደግድ ቤቱ ገፈተሩዋት ።

ታንጉት ፣ ጓዳ ገባና ወጣ እያለች ስትመለከት ወይዘሮ ደብሬ ሁሉንም የሚያውቁ ፣ ሁሉም የሚያውቃቸው ይመስል ከሁሉም አቅጣጫ ጨዋታ እየቀረበላቸው ከሁሉም ጋር ተዝናንተው ሞውውታቸውን ቀጠሉ ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተከትለዋት ጓዳ ገቡ ። '' እረ ባባጃሌው ምን እያረግሽ ነው እንቺ ልጄ ! '' አሏት ከልብ የተቆጣ የማይመስል ፊታቸውን አኩሳትረው ።

ታንጉት ፣ ምን አገባዎት የሚል ቁጣ ከጀላትና አልወጣላት አለ ። '' ምነው ? '' አለች በመገረም ጥያቄ ።

“እኮ ምን እየሠራሽ ነው?” አሉ ወይዘሮ ደብሬ ፣ እንደ ልጅ ለመቆን ጠጥ ይመስል ጣታቸውን ወደ ጉንጭዋ እየዘረጉ ።

“ ምን ሠራሁ ? ” ታንጕት አሁንም ጥርጣሬዋና የአቀራረባቸው ድፍረት ያሳደረባት ስሜት ጨርሶ አልጠፋም ። ግን አሁንም የቁጣ ፊት ማሳየት አልቻለችም ።

“ እንቺም ፣ እሱም ”አሉ ጉብርዬ ወደ አለበት ወደ በሩ በዐይናቸው እያመለከቱ ፣ “ አዬ የናንተ የሚካ ሰዎች ነገር ። ዝም ብላችሁ ሰውን ሁሉ ባንድነት በመደዳ ታስቀምጡታላችሁ ? ”

ታንጕት ነገሩ ስላልገባት ፣ በጥያቄ መልክ ተመለከተቻቸው ።

“ እየሽ ! ” አሉ ወይዘሮ ደብሬ ጠጋ ብለው በማንሾካሾክ ፣ “ ሰው እኮ የሚጨዋወተው ከመሰሉ ጋር ሲሆን ነው ። ታለማዕረጉ ሲዋሉትም ደስ አይለውም ። መቸስ ይኸው ነው ፣ ጕንደሮች ፣ ተኔ ጀምሮ የለመድ ነው ወግ ። ”

“ አሁን ዛዲያ ምን ላርግ ? ” አለች ታንጕት ፣ ሁሉም እንደገባ ባገኘው እንደ ተቀመጠ ገብቷት ።

“ አሁንማ ምን ታረጊያለሽ ። ከተቀመጡበት ተነሡ ማለት የባሰውን ማስቀየም ነው ። እንግዲህ የተቀመጠው እየወጣ ሲሔድ ፣ አዲስ የሚገባውን እንደ ምንም ማድረግ ነው ። እናንተ መቸም አታውቋቸውም፣እኔ ላግዛችሁ ? ” ሲሉ ጠየቋት ። ታንጕት ፣ ግራ ከሚያጋባት ከዚህ ሁናቴ ይልቅ ወደ ጓዳ ሥራዋ መመለስዋን አልጠላችውም ።

ወይዘሮ ደብሬ ፣ የአዳራሹን አስተናባሪነት እንደ ባለቤት ይዘው ጥቂትከቆዩ በኋላ ፣ አሁንም ጓዳ ገቡና አሁንም በውሽት ቁጣ ወይናቸውን በታንጕት ላይ አፈጠጡባት ።

“ ምነው እማማ ? ” አለች ታንጕት የመጨረሻው ቃል ሳይታወቃት ወጥቶ ፣ እንዳጠፋ ሕፃን በሚመስል ጥያቄ ።

“ ኧረ እንዲያው ምናችሁም አያምረኝ ! ” የተማረሩ መሰሉ ።

“ እህ ! ምን አረግነ አሁን ደሞ ? ”

“ ምን አረግነ ? ምግቡን መጠጡን ዝም ብላችሁ እግረ መንገዳችሁ እንዳደረሳችሁ አይደል የምታቀርቡት ? ” ሲሉ ወደ በለጡ ወደ ሌሎችም የቤት ሠራተኞች ጣታቸውን ቀስረው ጠየቁ ። ከታንጕት ጀምሮ ሁሉም ነገራቸው እንዳልገባቸው ከአስተያየታቸው ያስታውቅ ነበር ። ለጥቂት ጊዜ ተፋጥጠው ቆዩ ።

“ ኧረ ባባጃሌው ! መቸም የተሰናዳ ምግብም መጠጥም በቤት አለ ! ” ሲሉ በመጠየቅ ሳይሆን በማረጋገጥ ዐይነት ጠየቁ ።

“ አለ እንጂ ! ”

“ ዛዲያ እሱ ብቻ አይደለ ለመጣው ሁሉ የሚቀርበው ! ለሁነኛው ፣ ለቤተኛውስ ምን ይትረፈው ብላችሁ ነው ። ደግሞስ የመጣው ምግብና መጠጥ ሁሉ አውጥቶ አይጣል ! ምን እየሠራችሁ ነው ? ” ሲሉ አፋጠጡ ።

“ ተሱምኮ እያቀረብን ነው ” አለች በለጡ ።

“ እሱንማ አይቻለሁ ። እግር እንደጣላችሁ ፣ ጠላውን ተዚያ ፣ ጠጁን ተዚህ ፣ ዶሮ ወጡን ለዚያኛዉ ፣ ሥጋዉን ለዚህኛዉ — የቱ ፣ የት እንደሚቀርብ ሳታዩ ? ”

ከታንጕት ጀምሮ ሁሉም በሐሳብ እንደ ማቀርቀር አሉ ። “ ቅድም ሰው እንደ መሰሉ እንዳልኩት ነው ። እንዳይበላሽ የመጣው መበላት ፣ መጠጣት አለበት ። ግን እንደ መሰሉም ሲባል ፣ አንድ ሰው ፣ያመጣውን ምግብ መልሰሽ አታቀርቢለትም ። ይኸ ያመጣውን ለዚያ እየተደረገ ነው ። ” በጓዳ የተደረደረውን ከወዲያ ወዲህ ቃኙ ። “ ሞልቷል ። ተበልቶ ፣ ተጠጥቶም አያልቅ ። አሁን እንግዲህ አሰናዱትና አመለከታች ኋለሁ ! እሺ ? ” አዲስ እንግዳ ለማስቀመጥ ወደ አዳራሹ ተመለሱ ። ታንጕት ፣ “ ወቸው ጉድ ! ‘ ሳይደግስ አይጣላም ’ አሉ ? ” አያለች በሐሳብዋ ፣ ከሠራተኞቹ ጋር በመገረም ተያየች ።

ወደግምሻ አቅራቢያ እንግዳዉ ጥቂት ቀለል ማለት ሲጀምር ፣ ጉብርዬ ፣ ‘ እስቲ አባ ታጠቅን አይቸው ልምጣ ። በዚያው ተነ ዓለሜ ብቅ ልበል ’ ሲላት እንደ መጀመሪያው ቢሆን ኖሮ ታንጕትን ፣ ‘ እኔን ብቻየን ጥለሽኝ ’ ስትል በተጨነቀች ነበር ። አሁን ግን ‘ እንዳፈቀደህ ! ’ አለችው ።

ከግቢው ትንሽ ፈቀቅ ብሎ ጋረድና አክሊሉ እጆቻቸውን እያወዛወዙ በመከራከር ላይ ነበሩ ። ጋረድ ፣ የጉብርዬን ቤት በሩቅ ሲመለከት ድንገት ሐሳቡን ቀይሮ አልገባም ብሏል ። የሰጠው ምክንያት ባዶ እጃቸውን መምጣቱ ነውር መሆኑን ነው ። ትንሽም ይሁን ትልቅ አንዳች ነገር ያዙ ቢመጣ ደግሞ ፣ እንደ እጅ መንሻ እንደሚቈጠርበት ፣ ይህም የባሰውን ለእርሱ ውርደት መሆኑን ግን ሕሊናው ይነግረው ነበር ።

“ ኤዲያ ! እኔ ቁም ነገረኛ መሰለኸኝ ” አለ ይብተራ አክሊሉ በንዴት እነጋገር ። “ ወትሮውንስ — ወትሮውንስ ! ” ሳይጨርስ ተወው ።

“ አሃሃ ! ይች ባቄላ ያደረች እንደሆነ እትቆረጠምም ” አለ ጋረድ በሞትታ ቁጣ ። “ ወቅምህንም የረሳህ መሰለኝ ! ”

የአክሊሉ እንደበት ወዲያው ለዘብ አለ ። “ ምናረኩ ? ”

“ እንዲህም ትናገር ጀመር ? ”

“ እኔ መቸስ ላንተ ለአብሮ አደግ ወንድሚ ብዬ ነው እንጂ ፣ ያም ሰው ተወንድሙ ጋር ሲጫወት እንደ ባዳ አፉን አይቆጥብ ! ”

ገብርዬ ከአጠገባቸው ሲያርስ ንግግራቸውን አቆሙ ።

“ ምነው በዛሬው ቀን ብቻችሁን ጕዳና ላይ ቁማችኋል ልጅ ጋረድ ? ኧኸ ፊታውራሪ ልበልህ እንጂ ! ” አለ ገብርዬ የእግዚአብሔር ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ።

“ እኛማ ወደርስዎ ቤት መምጣታችን ነበር ” ሲል ደብተራ አክሊሉ ቀድሞ መለሰ ። ጋረድ በክፉ ዐይን ገረፍ ቢያደርገውም ሊያስተባብል አልከጀለም ።

“ ኑዋ ግቡ ! ” ገብርዬ እጁን በመዘርጋት መራቸውና የሚተዋወቁበትን ጊዜና ሥፍራ ለማስታወስ የሚሞክር ይመስል አክሊሉን ትኩር ብሎ ተመለከተው ። “ መሪጌታ አክሊሉ አባታችን ቤት ፣ ተኔም ተካ ሣም ጋራ አብሮ አደጋችን ነው ። አሁን ተኛ ተለይቶ የሎዛ ማርያም አለቃ ሆኗል ” ሲል ጋረድ አስተዋወቀው ። ‘ ቴዎድሮስ ብሎ መጥራትም ይቀፈዋል ማለት ነው ? ’ አለ ገብርዬ በሆዱ ። ቴዎድሮስና ጋረድ የሥጋ ወንድማማቾች ቢሆኑም ፣ የደጃች ክንፉ ልጅ በመሆኑ ብቻ ጋረድ ምኞት እንዳለው ፣ በዚህም ምኞቱ ምክንያት ከርሱ ልቀው በሚያያቸው ላይ ሁሉ ምቀኝነት እንደሚያድርበት ሰምቷል ።

ቴዎድሮስ ራሳቸው የጋረድ ነገር ሲነግባቸው ፣ ‘ ምን ኢዲያ ! አይረባም ። እጉል መንጠራራት ብቻ ነው ። አሁን እሱ የክንፉ ልጅ ነው ? ተምናቸውም የለ ። እበት ትል ይወልዳል ነው ፤ ለነገሩማ ተርሱ የቀረበ ወንድም መች ነበረኝ ! ’ ይላሉ ። ወገራንም የሾሙት እስቲ ተሞክሮ ይታይ በሚል ሐሳብ ይመስላል ። ገብርዬ ስሜቱን በፊቱ ላይ አላሳየም ።

የቴዎድሮስ ዘመድ በመሆኑም ይሁን ወይም የኩራት ስሜቱን ስለሚያውቁ ፣ በገብርዬ ቤት የነበሩት ሰዎች ሁሉ ለጋረድ የአክብሮት ሰላምታ አቀረቡለት ። ገብርዬ ታንጉትን ጠርቶ አስተዋወቃት ። “ ልጅ — እህ ? ፊታውራሪ ጋረድ ማለት እሱ ነው ። መቸም ወሬውን ሰምተኻል ። ” ታንጉት ስለ መልክ መልካምነቱ ሰምታ ነበር ። ረጅም ፣ ቀይ ፣ ጸጉረ ዞማ ፣ ከአፍንጫው ፣ ከከንፈሩ ከወይኑ ይህ ጕደለው የሚባል የጕንደር ወይዛዝርት ሁሉ የሚፈዝበት ነው እየተባለ ይነገርለት ነበር ። ግን አሁን ስታየው ብዙም አላስደነቃትም ። ባትጠላውም አልወደደችውም ። ይህ ነው ብላ የማትጠቁመው አንዳች ነገር የሚጕድለው መስሎ ተሰማት ። ምናልባት ከፈገግታው ይሆናል ። ጥርሶቹ ውብ ቢሆኑም ከንፈሩን ገለጥ ሲያደርግ የሚያሽሟጥጥ ያስመስለዋል ። ደብተራ አክሊሉን ግን ከነአካቴውም በሚገባ አልተመለከተችውም ።

“ እንደምን ሰነበቱ ወይዘሮ ደብሪቱ ? ” አላቸው ጋረድ ።

“ እንዴት ከረምሽ በለኝ እንጂ ! ኧረ የት ጠፋህ ? ! አላደርስህ አለ ማዳረሱ ? ” አሉት በቀልድ አሽሙር ።

“ በቀደም መጥቶ አጣሁዎት ። ”

“ እኔን ልትጠይቅ ? ወይስ ያችን ሞለፈጥ ? ኧረ ባባጃሌው ! ” አሉ ወይዘሮ ደብሪቱ ፣ የሚግጠኑ ይመስል በቤት ያለውን ሰው እየቃኙ ። “ እኔስ ዲቃላ ማሳደጉ ሰለቸኝ ። እሷ ተቤት ቋጥራ ስትቆየኝ እሱ ተጉረቤት ይዞ ሲመጣ ፣ በመኻል ቤት እኔ . . . ብቻ ግዴለም ጸጋ ነው ” ። እንድ ወንድና እንዲት ሴት ልጆቻቸውን ማለታቸው ነበር ። ሰዉ ሁሉ ሣቀ ። ታንጉት እብራ ከት አለች ። ‘ ስለ ልጆቻቸው በሰው ፊት እንዲህ ሲናገሩ እያፍሩም ? ወቸው ጉድ ! ’ እያለች በሆድዋ ።

በመካከሉ ገብርዬ ፣ “ በሉ ተጫወቱ ” በማለት እንደ ዘበት ወጣ ።

“ ወይዘሮ ታንጉት ፣ አባቴን ያውቁታል ? ” ሲል ጋረድ ድንገት ጠየቃት ፣ ገብርዬ አለመኖሩን ከአረጋገጠ በኋላ ።

ለምን እንደ ጠየቃት ምክንያቱ ለጊዜው ሊገባት አልቻለም ። ‘ ስለኔ የሚያውቀው ነገር ይኖር ይሆን ? ታወቀስ በእሽሙር መንካቱ ነው ? ወይስ አባቴን ድፍን አገር የሚያውቃቸው መሆኑን ለማስረገጥ ? ወይስ እኔን ለማነጋገር የሚያወራው ሲጠፋው ? ’ ከሐሳብ ጥያቄዋ ተመልሳ ፣ “ ኧረ የታባቴን ዐውቂያቸው ? ” አለች ።

“ እጅግ ታላቅ ሰው ነበሩ ። በዛ ሲባል ” አለ ጋረድ ደረቱን እንደ መንፋት እያደረገ ። “ ካሣን እንደዚያ አርገው ያሳደጉትና ለዚህ እንዲበቃ ያደረጉት የኔ አባት ናቸው ። ” ደረቱን በእጁ መታ መታ አደረገ ። “ የኔ አባት ባይኖሩ ኖሮ ካሣ ይኸኔ ፣ ገብርዬም ቢሆን . . . ”

አክሊሉ ጉንተል አደረገው ። ጋረድ ከዚህም ከመጣ በኋላ ያከለው ጠጅ የቆየ ሞቅታውን አብሶበት በከፊል ከራሱ ጋር የሚያወጋ መስሎት ነበር ። “ እህ ? ” ብሎ እንደ መባነን ሲል ፣ አክሊሉ ከወይዘሮ ደብሪቱ ጋር ሌላ ጭውውት ለጠቅ አደረገ ።

“ ወይዘሮ ደብሬ ፣ ምነው ሎዛ ማርያምን ረሱዋት ? ”

“ ኧረ ባባጃሌው !! አምና ሁለት ማድጋ መገበሪያ ስንዴ አላመጣ ሁም መምሬ ? ”

“ መገበሪያ መች አጣና ! ባላገር ሁሉ የሚያመጣው ነው ። ሲሆን ድባብ ፣ ታሰበለዚያ የባሕር ማዶውን የሐር ጥላ ነው እንጂ ! ”

“ እዬ መምሬ ! ደንቢያን የምገዛ መሰልኩዎት ! ”

“ ማሩ ቀመስ ደንቢያን ይዞ ያባቴ ግዛት ነበር ! ” አለ ጋረድ በመ ካከል ገብቶ ።

ብዙዎቹ ሰዎች ሞቅታውን ስላወቁ በትዝብት ፈገግታ ይመለከቱታል ። አንዳንዶቹም በጥርጣሬ ያስተውሉታል ። የቴዎድሮስን የፍቅር ልብ ለማግኘት ሲል በማስመሰል ነገር ሊያወጣጣቸው እንደሆነስ ? ቴዎድሮስ ራሳቸው አልባሌ ሰው መስለው ከሥፍራ ሥፍራ በመገኘት ስለ

አስተዳደራቸው ሕዝብ የሚለውን ያጻምጣሉ የሚል ሐሜት አለ ። መቸም ቢሆን ሥጋቸው ነው ። ማን ያውቃል ? ማን ይሞኛል ?

የጋረድ ስሜት ግን ፣ ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል ዐይነት ነበር ። ከቴዎድሮስ ጋር ከአሁኑ ተፈት ለፈት ድፍረቱን ለመፈታተን ፈልጎ ሳይ ሆን ፣ የማመዛዘን ችሎታውን ደብዘዝ ያደረገበት ሞቅታ እንደ ፈለገ ብቻ ያናግረዋል ። “ አንቺ ፣ ታላጣው ሹመት እንቺንስ ለምን አልሾ መሽም እንደኔ ? ” አለ ጋረድ እጁን ወደ ታንጉት እያጣቀሰ ።

“ አሆሆ ! ” ብላ ታንጉት ወደ ጓዳ በር ገብታ ተጋረደች ።

“ አረ ባባጃሌው ! ሴት ደሞ ልትሾም ? አንተስ ጉደኛ እየሆንክ ሔደሃል ። አባትህ ይህን ጉድ አላዩ ” አሉ ወይዘሮ ደብሬ ለመጀመሪያ ጊዜ ከልብ የተኰሳተሩ መስለው ። ግን ይህም በሙሉ አልተዋጣላቸ ውም ። ቁጣቸው ከልባቸው አለመሆኑን የሚያሳጣባቸው ከዐይን አገላ ለጣቸው ፣ ከከንፈር መሥመራቸው እንድ ልዩ ምልክት ያለ ይመስላል ።

“ ለምን አትሾምም ፣ ይኸው ተዋበች ተሹማ የለ ? ” አለ ጋረድ በመጠጡ ኃይል ርግጥ አድርጎ ፣ “ ያውም የመጨረሻውን ! ”

“ አረ ባባጃሌው ፣ ያ ሌላ ፣ ይኼ ሌላ ” አሉ ወይዘሮ ደብሬ ነገሩን በማቃለል ።

ብዙ ሰው ግን ግራ ተጋብቶ ፣ ተገርሞ ዝም አለ ። የጋረድ አሽሙር ታንጉትንም እንደ መርፌ ጠቅ አደረጋት ። አዎ ፣ እርዷም በአደባባይ ክብርና ማዕረግ ማግኘቱን ትወደው ነበር ። ግና አላገኘችውም ። እርግጥ ፣ አባ ታጠቅ እንደልጅ አሳድጎ ፣ ከዚያ ባላነሰ ፍቅር እንደሚመለከታት ይታወቃታል ። ከዚህ በተረፈ ግን የፍቅሩ መሠረት ለሰው በግልጽ አይ ታወቅም ። እንዳሳደጋት የቤት ውልድ ፣ ወይም እንደ ቤት እንስሳ ዐይ ነት ነው ። ስጦታዉና ሽልማቱም በቤት ፣ በምሥጢር ነው ። ዛዲያ ፣ ፀሐይ ካላየው ፣ ወዳጅና ጠላት ካላወቀው ምን ርባና አለው ? ተዋበች ግን ከርሷ በኋላ መጥታ እንሆ ጋረድ እንዳለው በአደባባይ የመጨረሻ ውን ቀሚስ ለብሳለች ። ታንጉት ከዚህ ሐሳብ ላይ ስትደርስ ፣ ራሷን ይዛ እግዚኦ ማለት ታጣት ፣ እንደ ትልት እጎት ትወዳታለች ። ለካሣ መንገር የማትደፍረውን ፣ ግን እንዲሆንላት የምትፈልገውን የምታማከረው ለተ ዋበች ነበር ። ካሣን ፣ የአሁኑን ቴዎድሮስ ከራስዋ ይልቅ ተዋበች እንደሚ ረግፍ አበባ ተንከባክባ እንደምትይዘው ታውቃለች ። ‘ ታዲያ እኔ በተዋ በች ማዕረግ ልቅና ? ’ ስትል ራሷን ጠየቀችና ራሷን በምሬት ለመውቀስ ሞከረች ። ወዲያው መልሳ ፣ ‘ግና ደግሞስ እኔስ ብሆን’ የሚለው ጥያቄ ከጋ ረድ አንጋገር ጋር አስማማት ። ሐሳብዋ ሁሉ ሲማታባት ፣ ወደ ጓዳ ገብታ በተደረደረው ምግብና መጠጥ መካከል ዘፍ አለችና ፣ አገጭዋን በመ ሮጀ አስደግፉ ዝም ብላ ተቀመጠች ። በአካልም ፣ በሐሳብም ደክማት ፣ ከአዳራሹ የሰው ንግግር ይሰማታል ።

ጥቂት ቆይቶ ቅልል ሲላት ፣ በእንዳች ዐይነት ምሥጢር ያወቁ ይመስል ወይዘሮ ደብሬ መጡና ፣ “ አረ ባባጃሌው ! ነይ እንጂ እንግዳሽን ሸኝ ! ” አሏት ። የድካም ፈገግታ እያሳየች ተከተለቻቸው ።

ጋረድ ፣ ቀደም ሲል በአክሊሉ ተገፋፍቶ ወጥቶ ስለ ነበር አላገኘች ውም ። “ ያ ቋረኛስ እንደሆነ እየቀባጠረ ሔዷል ” አሏት ወይዘሮ ደብሬ ሐሳቧን የተረዱ ይመስል ። ሌሎችም እንዳንዱ ፣ ከእንግዱ ቀልበስ ፣ ሌላዉ ከትከሻው ሰበር ፣ ወይም ከወገቡ እጥፍ እያለ ተሰናብቶ አለቀ ።

“ በይ እንግዲህ እንዳሻሽ ! ” አሉና በመጨረሻው ወይዘሮ ደብሬ ተሰናበቷት ።

“ መሔድዎ ነው ! ”

“ አረ ባባጃሌው ! ዛዲያ ተዚህ ላድርልሽ ነው ? ”

እንግዶች ሁሉ ሔደው ፣ ሠራተኞቹ ሁሉ ተሰናብተው ፣ ታንጉት ከበ ለው ጋር ብቻቸውን ከቀሩ በኋላ ፣ “ ጉድ አይደለም ? ” አለቻት ።

“ አረ ! እሜቴ ደስ የሚል ዓለም ነው ! ” አለች በለጡ በመቅበ ጥበጥ ። ከዚህም ከዚያም ስታሚላና ስታገላብጥ ቀማምሳ ነበር ።

“ ዝብርቅርት አልሆነብሽም በለጡ ? ” አለች ታንጉት በአብዛኛው ከራሷ ጋር ። የወይዘሮ ደብሬን ከጋረድ ጋር ፣ ብዙ ከማይናገረው የሎዛ አለቃ ከተባለው ጋር ፣ ሁለት ሦስት ብርሌ ጠጅ ጠጥቶ — የገብርዬ አሽ ከር ሲል እየፎከረ ለያዥ ለገላጋይ አስቸግሮ ከተሸኘው አንድ ደጂ ጠኝ መሳይ ጋር ሁሉንም አነጻጸረችው ።

“አረ ቢሆንም ውብ ዓለም ነው ” አለች በለጡ በድጋሚ ። “ ምንም አልቀመሱም እኮ እትዬ ! ” ስትል ብርሌ ጠጅ አመጣችላት ።

በእውነትም ጉሮሮዋ ደርቆ ነበር ። በአብዛኛው በሐሳብ ጉንጨት አደረገችና ፣ “ ምኑን እናውቃለን ብለሽ ። እስቲ መጨረሻውን ያሳም ረው ” አለች ።

Meysor Bro
t.me/BooksandYou

ምዕራፍ ሁለት

ከዐዋጁና ከሹም ሽሩ በኋላ ፣ የጉንደር ማኅበራዊ ሕይወት ረጋ ብሎ ቀጠለ ። እርጋታው ግን ውሽንፍር ከመነሣቱ በፊት እንደሚሰፍን የንፋስ ጸጥታ አሳሳች ነበር ።

‘ ሹመት ቀርቶብናል ፣ ግዛት ተወስዶብናል ’ ብለው የተከፉት ፣ ከመ ከፋትም ፀልፎ በንዴት የተቃጠሉት ጥርሳቸውን መንከስ እንጂ መሣ ሪያ ከመወልወል ገና አልደረሱም ። ቁጭታቸውን ፣ በሆዳቸው አላም ጠው አላምጠው ለፍልሚያ እስኪነሡ ጊዜ ይወስድባቸዋል ። ሠርተው እንዲበሉ የተወሰነባቸው ምድረ ካህናትና ጠምጣሚ ሁሉ እንደ አጋጣሚ አዝመራው ሠምሮ ፣ ቀማኛና ወንበዴ በመቀነሱ ንግድና ገበያ ደግ ሞቆ ፣ በየቤቱ በየመንደሩ ፣ ድግስ ፣ ማኅበርና ዝክር ሞልቶ ስለ ነበር ፣ ጉዳቱ ገና አልተሰማቸውም ። ቅሬታቸው በዋንጫ አፍ ላይ ከማጉረ ምረም አላለፈም ነበር ። በዚህ ላይ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ ስለ ዘመቱ የጉንደር ከተማ የሠራዊት ግርግር ተለይቷት ነበር ።

የቅሬተኛው ቅሬታ በአብዛኛው የሚገለጸው በቴዎድሮስ የሸዋ ዘመቻ ወሬ ነው ። ስለ ቴዎድሮስ የሸዋ ዘመቻ በየቤቱ ፣ በየመሸታ ቤቱ ፣ በየማኅበሩና ዝክሩ የሚወራው በከፊል ምኞት ፣ በከፊሉ አስተያየት ፣ በጣም በጥቂቱ ተባባሪ እውነትና በአብዛኛው ሟርት ነበር ።

‘ ያን ቂረኛ ፣ የተከዜ በረሃ እስከነሠራዊቱ በላውኮ ተባለ ! ’ ይላል እንዱ ።

‘ አላንዳች ነገር መቼ እንዲያ አንከወከወው ! መቃብሩ ቢጠራው እንጂ ’ ሲል ሌላዉ ይለጥቃል ።

‘ ያችን ሚሽቱን ምን ቀጣት ? ’

‘ የታደለ የሸዋ መኳንንት ስለቀጣታ ! ’

‘ ተወልዳ ካደገችበት ቤተ መንግሥት አውጥቶ ሲያንከራትታት ! ’

‘ እናንተ ፣ ሸዋ ዋዛ መስሎ ጉድ ሆነ አሉኮ ’ ሲል እንዱ ነገር ይለኩሳል ።

‘ ምን ሆና ? ’ ይላል ለወሬ የጀመጠ አድማጭ እየተቅበጠበጠ ።

‘ ውል የያዘ ነገር እንኳን አላገኘሁም ። ብቻ ፣ ብቻ ግን — ’ አንጠልጥሎ ይተወዋል ።

‘ እኔ ደሞ የሰማሁት ተዚያ አንኮበር ላይ ተማርኳል ነው ’ ሲል ሌላዉ ተካ ያደርጋል ።

‘ ትልልቁን ሰው ሁሉ ሲያስር እንደኖረ የጁን አገኘ በለኛ ! ’ ይላል ሌላዉ በደስታ መንፈስ ተውጠ ።

ከዚያም የሚርቱም ፣ የመገረሙም ፣ የማፌዙም ቃለ ኢጋና ከየአ ገጣጫው ይሰነዘራል ።

ወንበዴ የጠፋለት ፣ እንዳሻው የሚያስር ፣ የሚዘርፍ የሚነዳ የዘመነ መሳፍንት ሹም የተነሣለት ፣ ብዙኃኑ ሕዝብ ደግሞ በበኩሉ ይህንን ሁሉ ወረና ሐሜት የሚያስተናግደው በቁጭት ነበር ። ቴዎድሮስ ተመልሶ የግይደርስለት የሚመስለው ከንፈሩን በሆዱ ነክሶ በዝምታ ብቻ ይታ ዘባል ። እንዳንዱ ፣ ‘ ጀግና የማይወድለት የመንደር አውደልዳይ የፈ ጠረው ነው ! ’ ሲል ደፍሮ ይሟገታል ። እረኛ ፣ ውሃ ቀጅ ፣ ሚርቱን ለማ ስተባባል ይመስል ለአባ ታጠቅ ሙገሳ በየዕለቱ አዳዲስ ዘፈን ያወጣሉ ።

በዚሁ ሁሉ መካከል ፣ ታንጉት ዝርዝሩን የመንደር ሚርት ሁሉ ሳይ ሆን ፣ እንዳንዱን መጥፎ ወሬ ስትሰማ ፣ ስለ ገብርዬና ፣ ስለ ቴዎድሮስ ፣ ስለ ተዋበችና ስለ ሌሎችም በደኅና መመለስ ሐሳብ ቢገባትም የጉንደርን ኑሮ እየተላመደችው ሒደች ። ከእንዳንዶቹ በስተቀር አብዛኞቹ የቴዎ ድሮስ የጦር አበጋዞች ሚስቶች እንደ ርቧው ጉንደር ቀርተው ነበር ። ‘ እስተዛሬ ተኛ ጋር ሲንከራተቱ ኖሩ ። እስቲ አሁንስ ትንሽ ዐረፍ ይበሉ እንጂ ። ደሞም ከተማውንም ይጠብቁልን ። ለዚህ መንደር አውደልዳይ መቸም አያንሱ ’ ሲሉ እንዲቀሩ ያደረጉት ቴዎድሮስ ነበሩ ። ተዋበች ግን ተለይቼ አልቀርም ብለው አብረው ሒደዋል ። እነርሱ ወደ ቤትዋ እየመጡ ፣ ታንጉት ወደ እነርሱ እየሒደች ፣ በጭውውት በፈትል ፣ በስፈ ትና በሌላም የሴት ሙያ ፣ ከጥንት ዕውቂያዎቿ ጋር ብዙ ጊዜ የምታ ሳልፍ ቢሆንም ፣ ከወይዘሮ ደብሪቱ ጋር ያላት ቅርበት ከቀን ወደ ቀን እያ ደገ በመሔድ ላይ ነው ። እርግጥ ሌሎችም የጉንደር ወይዛዝርት ሊጠይ ቋት ይመጣሉ ። ከብዙዎቹም ጋር እስከ መወዳጀት ደርሳለች ። አንዳን ዶቹ እቃቂራቸው አይጥግትም ። ሌሎችም አጉል ሲቅበጠበጡላት እንድ ውለታ እንድትሠራላቸው የሚፈልጉ መሆናቸው ይሰማታል ። ወይዘሮ ደብሪቱ ግን ከሁለቱም አይደሉም ። አነጋገራቸው ለዛ ያለው ቢሆንም በእቃቂር ያልተቀባባ ቀና ነው ። እንደ ፊታቸው ፈገግታ ነገራ ቸው ግልጽ ነው ። አንዳንድ ጊዜ ቀልዳቸው ቆጣጣ ያስሮጣል ። ከነገራ ቸው ሁሉ በሌለበት ሰው ማማት አይወድላቸውም ። ከተናገሩ ራት ለፈት ነው ።

ታንጉት ፣ የወይዘሮ ደብሪን ጨዋታ ስትሰማ ውላ ብታድር የማት ጠግበው እየሆነች ሒደች ። ግማሽ ቀን ሙሉ ከቤቷ ቆይተው ለመሔድ

የተነሡ እንደሆነ ፣ ‘ ይቆዩ እንጅ ምን አማደፍዎት ’ ትላቸዋለች ። እንድ ሁለት ቀን ሳይመጡ የዋሉ እንደሆነ ፣ ‘ ምነው ጠፉ ? በደኅና አይደሉም ወይ ? ’ ስትል በለሙን ትልክባቸዋለች ። ወይም ራስዋ ሔዳ ከዚያው ስትጫወት ትውላለች ።

የሁለቱ ወዳጅነት ገብርዬን ስንኳ አስገርሞት ፣ ‘ አንቺ እኒህ ቤትዮ ምን አትምሰውሻል ? ’ ሲል ወደ ሸዋ ከመዝመቱ በፊት እንደ ቀልድ ጠይቋት ነበር ።

“ ደሞ ምን ሊያቀምሱኝ ኑሮዋል ። ተመልካም ሰው ጋር መወዳጀት ነውር ነው እንዴ ? ” አለችው ።

“ በዚህ አጭር ጊዜ ፣ ከአብሮ አደግ የባሰ ሆናችሁብኝ ብዬ ነዋ ! ’

“ ታጉል አብሮ አደግነት ፣ አንድ ቀን ልብስ አጠባ ላይ የተዋወቁት ወዳጅ የሚበልጥበት ጊዜ አለ ። ‘ ዕውቂያና ልደት አንድ ቀን ’ ተብሏል ። አንተስ ቢሆን አባ ታጠቅን የተዋወቅከው አንድ ቀን አይደለም ? ብታውታቸው እንዲህ ያሉ ሰው አይምሰሉህ ! ” አለች ራስዋን በአድናቆት ነቅንቅ እያደረገች ።

“ አሆሆ ! እንደበትም እያስተማሩሽ መሰለኝ ። በሉ ያዝልቅላ ችኋ ! ” አለና ነገሩን ተወው ። ታንጉት ደስ እስካላትና ጥሩ ሰው ሆነው እስከ አገኘቻቸው ድረስ የሁለቱ ወዳጅነት የሚያስከፋ መስሎ አልታ የውም ። እርግጥ እንደ አሁኑ ዕድሜ ሳይገታቸው ከአንድ ወንድ አይረ ጉም ነበር ይባላል ። እንዲያውም ፣ ግና ኮረዳ ሳሉ ፣ በመጀመሪያ ያስቀመ ጡዋቸው ደጃች ተድላ ስለ ነበሩ በአፍላቸው ጊዜ ፣ ‘ የተድላ አፋጀሽኝ ’ የሚል ቅጽል ወጥቶላቸው ነበር ። አሁን ግን ምሥጢሩን በትክክል የሚያውቅ ባይኖርም በግልጽ ስማቸው በዚህ አይነሣም ” ። ‘ ቢሆንስ ፣ እርሷ ሴት ፣ እሳቸውም ሴት ፣ ምን እንዳያደርጓት ? ’ አለ በሆዱ ። ሌላ ሐሳብ ግን አልመጣበትም ።

ታንጉት ፣ ወይዘሮ ደብሬን ከወዳጅ ዐልፎ እንደ እናት ያም ሳይሆን እንደምትታመን አክስት እንድትመለከታቸው የሚያደርግ ሁናቴ የደረ ሰው ደግሞ ገብርዬ ወደ ሸዋ ከዘመተ በኋላ ነበር ።

አንድ ቀን ፣ የራስ እንግዳ ፣ የደጃች ዓለሜ ፣ የደጃች ቢተው ፣ የደ ጃች ቢሠውር ሚስቶች ከታንጉት ቤት ተሰባስበው እህል ውሃ እየቀማ መሱ ይጨዋወታሉ ። ወይዘሮ ደብሬም አሉ ። ግን በምን እንዳንነሣው ሳይታወቅ ጨዋታዉ ወደ ባሎቻቸው ጀግንነትና ግዕረግ ያመራል ።

“ ታውቁ የለ ? ዓለሜ ጉራምባ ላይ የወንዲራድን ጦር እንዴት እንዳ ተራመሰው ። ሲመለሱ እኮ የሸጉጡ መጋል እጅ ያታጥል ነበር ” አለች የዓለሜ ሚስት ።

“ ታልሽስ የቢተው ጦር ሊዶለዱም ምንም አልቀረው ነበር ” በማለት ተኩራራች የቢተውም ሚስት በበኩሏ ።

“ ቢሠውርማ ስሜን ላይ የገደለውን የደጃች ውቤ ሰው ቁጥሩንም አያውቀው ” ስትል የራቧን አሞጋገሰች የቢሠውር ሚስትም ።

“ ለሁሉም ጦርነቱን ሁላ ባራኪው እንግዳ አይደል ? ” አለች የእንግዳ ሚስት ፣ ‘ ደግሞ የእኔስ ለምን ይቅር ’ በማለት ።

“ ግና ወንዲራድንም ፣ መነንንም ፣ ደጃች ውቤንም የማረካቸው ገብርዬ ነው ። ”

“ ቢሆንስ ተንግዳ ሊስተካከል ? ” አለች ጉንደራዋ የራስ እንግዳ ሚስት ።

“ ተራስ አሊ ስንዋጋ ገብርዬ ቆስሎ አልነበር ? ያን ጊዜ አባ ታወቅ ሊጠይቀው ድንኳናችን መጥቶ ፣ ገብርዬ ቀኝ እጇን ላጣ ነበር ነው ያለው ። ቀኝ እጇን ላጣ ነበር ! ” ስትል ታንጉት በማስረገጥ ደገመችው። እርሷም የባሏን ጀብዱ ሳታወላለት ላልማለፍ ቁርጣ በመነሣት ።

“ እንግዳ ቢበልጥ አይደለ ራስ የተባለው ? የሁሉም በላይ መሆኑ እኮ ነው ” አለች የእንግዳ ሚስት አነጋገሩዋን ፍርጥም አድርጋ ።

“ ፊታውራሪ እኮ ተሁሉ በፊት ማለት ነው ። ደሞ የጦሩ ሁላ እዝ ማች ሆኗል ” ስትል መለሰች ታንጉት ላለመረታት ።

ወይዘሮ ደብሬ ፣ ነገራቸው አስገርሞዋቸው ዝም ብለው በፈገግታ ሲመለከቱዋቸው ቆዩና ፣ “ አሁን ምን እከራከራችሁ ? ሁሉም ጥሩ ጉበ ዞች ናቸው ማለቱ አይበቃም ? ” አሉ በማስማማት መልክ ።

አንድ ሁለት ብርሌ ጠጅ የጨረሰችው የእንግዳ ሚስት ፡ “ ዛዲያ ራስና ፊታውራሪ እኩል ናቸው ለምን ትላለች ? ” ስትል ዐይንዋን አጉ ረጠረጠች ።

ታንጉት ፣ በጀግንነት እንግዳ ከገብርዬ እንደማይስተካከል ስለም ታውቅ ንድድ አላት ። “ ራስ ማለት ምን መሰለሽ ? የራስ ሚዜ ፡ የግር ሚዜ እንደሚባለው ማለት እኮ ነው ። አጃቢ ነው እንጂ ሙያው ተሌላ ። ”

ሌሎቹ ሲሥቁ ፣ የእንግዳ ሚስት አሽሙሩ ተሰምታት ከውስዋ በገ ነች ። “ የራስ ሚዜምኮ ይሠራል ” አለች እንዳይታወትባት በበኩልዋ በቀልድ ለመሸፈን ።

“ በሉ በቃችሁ ። ሌላ ጨዋታ አምጡ ! ኧረ ባባጃሌው ” አሉ አዝ ማሚያው ያልጣማቸውና የእንግዳ ሚስትን ሁናቴ የተገነዘቡት ወይዘሮ ደብሬ ።

የእንግዳ ሚስት ግን ፣ ሌላ ጨዋታ ከያዙ በኋላም ቢሆን ነገሩ ከሆ ድዋ አልጠፋም ነበር ። ሲከነክናት እንደ ቆዩ ለመሔድ ሲነሡ ፣ “ ተሣሪ ነገ እጠይቅሻለሁ እያልኩ ፣ ኧረ ለመሆኑ ፡ ገልሞ ዘመድሽ ነው ፣ ታንጉት ? ” ስትል ጠየቀቻት ። ሌሎቹ ሴቶች በቆሙበት ድርቅ አሉ ። ታንጉት መልስ ሳትሰጥ ፣ በጥፊ እንደ ተመታ ሰው ዝም ብላ ተመለከተ ቻት ። “ ያንዳገር ሰዎች ስለሆናችሁ ፣ ድንገት እንደሆን ብዬ ነው ” አለችና ምንም ክፉ ነገር እንዳልተናገረች ተሰነባብታ ወጣች ።

ታንጉት ፣ እንደ ታከተው ሰው ፣ ከጠፍር ወንበሩ ዘፍ አለችና ፈዝዛ በወለሉ ላይ ዐይንዋን ተከለች ። ስሜቷ ጎዝን ይሁን ንዴት በሚገባ አለ የላትም ። የመገረምም ዐይነት ነው ። ‘ ምን ማለቷ ነው ’ ሲል ሐሳቧ ደጋ ግሞ ይጠይቃል ። የእንግዳ ሚስት ምን ማለቷ እንደሆነ ግን ተሰምቷ ታል ። ስለ ተሰማትም ታውቋታል ። የእንግዳ ሚስት ፣ ረስታው እንደ ቆየችው ነገር ድንገት ትሰንዝረው እንጂ እሽሙሩ ግልጽ ነበር ። የምታ ስበው ጠፍታት ፣ ሐሳብዋ ባዶ ሆኖባት ፣ ‘ ወቸው ጉድ ! ’ አለች ከራ ስዋ ጋር ። ግን ሳይታወቃት ንግግርዋ ከራስዋ ዐልፎ በአዳራሹ ላለ ሰው የሚሰማ ነበር ።

‘ አንቺ ! ’ አሉ ወይዘሮ ደብሬ ልጃን እንደሚቀጣ እናት ፣ እሷን በእጅዋ ስበው አስነሥተው ራሳቸው ዘርፈጥ ብለው እየተቀመጡና ፣ ለቁጣ አይሉት ለቀልድ ፣ የሚያሻሙ ዐይኖቻቸውን እያቁለጨለጩ ፣ ‘ ቅማንት ነሽ ? ’ አሏት ። እነጋገራቸው ያለማወቅ ጥያቄ ፣ ወይም እንደ እንግዳ ሚሽት የሚያውቁትን ነገር በእሽሙር መልክ ማቅረብም አልነበረም ። በፍልሰታ ፡ ጾም ውሎ ፣ ቆርቦ ወደ ቤቱ ሲመለስ መንገድ ላይ የሚያገኙትን ሕፃን ፣ ‘ ቆርበህ ነው ? ’ ብሎ እንደ ማበረታታትም እንደ ማድነቅም ዐይነት ነበር ።

ከደበዘዘባት ሐሳብ መለስ አለች ። “ ለምን ጠየቁኝ ? ”

“ ኧረ ባባጃሌው ! መሰሌን ዐውቀዋለኋ ! ”

“ ቅማንት ነዎት ? ” ስትል ጠየቀች ፣ ስሜቷን ቅልል እያለው ።

“ ኧረ ባባጃሌው ! እንቺን ነው የጠየኩሽ ! ይልቅስ ቁጭ በይ ተፈቴ አትገተረብኝ ! ” ሲሉ አዘዙዋት ።

ስትቀመጥ እንደገና ጠየቋት ። “ እኔ እንጃ ! ” ስትል መለሰች የመደፋፈር ሣቅ በተቀላቀለበት ሙሉ ድምፅ ።

“ ዛዲያ ምን አስደነገጠሽ ? ”

“ ነገሩ ገርሞኝ ነዋ ! ”

“ ግና ገልሞ ቅማንት እንደሆነ ታውቂያለሽ ? ”

“ ሲባል እሰማለሁ ። ”

“ እገር ያወቀው ነው እንጂ ! ያስደነገጠሽስ እሱ አይደለ ? እኔም እንዳንቺ ሳለሁ እንዳንችው ሆኛለሁ ! ”

“ ትግንት ነዎት ግለት ነዋ !! ”

“ ኧረ ባባጃሌው ! ነኝ አልኩሽ ? የተባልኩትን ነው የምልሽ ። ”

ግንባርዋን እያሻሸች ዝም አለች ።

“ የሆንኩትን መስማት እትፈልጊም ? ” አሉ ቅር የተሰኙ በመ ምስል ።

“ እየሰማውዎት እኮ ነው ! ”

“ይሽውልሽ እንግዲህ ፣ ገና ጡቴ እንደዚህ ሎሚ እንደ መሰለ ሳለ ነው ” በማሳየት ጡታቸውን ነካ ነካ አደረጉት ። “ እስቲ ጠጅ ስጭኝ ፣አልጠግሁም እኮ ” አሉና ቀድታ እስክትሰጣቸው ጠበቁት ። “ አለፋ ጣቁሳ ነው እገሬ ። ዛሂያ እንዳልኩሽ ፣ ጉበዝ ሁሉ ፣ ላግባት ላግባት እያለ ሰው በሚልክበት ፣ ውሃ ልቀዳ ወንዝ ስወርድ ይሽ ጎረምሳው ሁሉ ‘ እንቺ ! ’እያለ ዐይኑን ተኔ ላይ ጣል በሚያደርግበት ጊዜ ፣ ‘ሽፍታ ተነሣ’ተባለና ደጃማች ተድላ ተነመላ ሠራዊታቸው ዘመቱ ብን ። ተዚያ ፣ ሠፈሩ ሁሉ ፣ ሲዘረፍ ሲቃጠል ፣ እንዱ ሲገደል ፣ ሌላዉ ሲማረክ ተኛ መንደር ደረሱ ። እባቴ ቀደም ሲል ፣ እንደ ወጣ የት እንደ ደረሰ ፣ ተማርኮ ይሁን ሞቶ ፣ አላውቅም ። በመንደሩ በአብዛኛዉ የቀ ረንው ሴቶቹ ነበርን ። ዛዲያ ደጃች ተድላ ተፈት ሆነው እኛ ሴቶቹ እንደ ከብት እየተነዳን ስንሔድ ፣ ደኅና ደኅና ሴቶቹን በእጃቸው እያመለከቱ ወደ እንድ በኩል እከማቹን ። ተወስድን ተሰፈራቸው ። ኧረ ባባጃሌው ! አሁን ሳስበው ይገርመኛል ። ስለ ሌሎቹ አላውቅም ። እኔን አንድ ቀን እስ ጠሩኝ ፣ እልፍኛቸው ! ” ለማስታወስ የሚሞክሩ ይመስል ዐይኖቻቸውን ሰለምለም አደረጉ ። “ ተዚያ በፊት ወንድ አልነካኝም ነበር ። ምን ልበ ልሽ ! ወደዱኝ ! ሰው እይይብኝ አሉ ። ዛዲያ እኔ ምን ቸገረኝ ፣ ገና ጣሙ አልገባኝም ፣ እሳቸውም ሸምግለው ነበር ። ዝም ብዬ መፈት ለቀቅኋ ! ዛዲያ የነሱም አለቆች እኔን መፈለግ ! እኔ እምቢ ማለት ! አንድ ቀን እንዱ ፣ አለቃ ይሆናል ፣ ‘ አንቺ ደብሬ ቅማንት የሚባሉት እንዴት ያሉ ናቸው ?’ ሲል ቢጠይቀኝ ክው አልኩኝ ፣ እኔን መስሎኝ ። ኧረ ባባጃሌው! ተመልሶ ሲያስቡት ያሥቃል እኮ ! ተዚያም እያለታቀስኩ ተደጃዝማች አልፍኝ ስገባ ምህኖቱን ጠየቁኝ ፣ ነገር፡ኩዋቸው ፣ የመከሩኝን አልረሳ ውም ። ‘ መቸስ ፣ እኛማ የአፍ ልማድ ሆኖኮ ነው እንጂ አንቺን ይሽው ወድጂ አቅፈሽ የለም ፣ ተሌሎች አብልጬ ? አይዞሽ ወደፊትም እንደዚህ ያለ ነገር ስትሰሚ ፣ ይሽው ተኔ ሞን ጋር ተሻሽተሽ የለም ! በዚህ ስሜት እያቸዋ ! ’ አሉኝ ። መቸም የሞናቸውን ነገር ልተ[illegible]ና — ኧረ ባባጃሌው ! ይህን ደሞ ምን አስታወሰኝ አሁን እባካችሁ ! ተዚያ ሰውየውን የት እንዳደረሱት አላውቅም ፣ ጠፉ ። እኔም የልብ ልብ በታኛ !

ተሳቸው ተለይቼ ጉንደር ስናርም ፣ እንደዚያ መኳንንቱ ይረባረብብኛል እንጂ እንድም ሰው ፊት ለፊት እንዲህ ነሽ ብሎኝ አያውቅም። ይፈራሳ ! አኔም ብሆን ልክ ልኩን እነግረዋለኋ ! እኔ ምን ቸገረኝ አገር ምድሩ በየቤቱ ቢንሾካሾክብኝ ! አሁን አሁንማ ሲታክታቸው ጨርሰው ትተ ውት ይሆናል ። እና ይኸው ነው አልሻለሁ ልጂ ! ” አሉና ብርሌያቸ ውን ዶቅዶቅ አድርገው አስቀመጡት ። ከባድ ቁም ነገር ፡ መራራ ትዝታ ስንኳ ሕይወትን በቀልድ የያዘ የሚመስለውን የፊታቸውን ፈገግታ የሚለውጠው አይመስልም ።

ታንጕት ፣ አፍዋን ከፍታ ስታዳምጣቸው እንደ ቆየች ፣ “ እንግዲ ያው ቅማንት ነዎት ግለት ነዋ ! ” አለች ድንገት በንነፈለ የስሜት እነ ጋገር ።

“ መባሌን ነው ያልኩሽ ፣ መባልሽን ነው ያልኩሽ ፣ የቀረው ፍሬ ከርስኪ ነው ። ሁለስ ሰው አይደለ በቁመናውማ ? ቱምድሮስን የወደድኩለት ፣ ይህን ዘር ማንዘር ተጪኝ ማለቱን ነው ። ”

‘ታዲያ ፣ የኔንስ ነገር ለምን ግልጥ አድርጎ አያወጣውም ’ ስትል በሆ ድዋ የቅፌታ ጥያቄ አቀረበች ።

“ ዛዲያ እንዲህ ነሽ ፣ እንዲህ ነህ ! ማለትን ምን ያመጣዋል መስ ለሽ ? ” ሲሉ ራሳቸው ጠይቀው መልሱን ቀጠሉ ። “ ዐቅም ማጣት ነው ፣ ሌላ አይምሰልሽ ። ደጃች ተድላን ስለ ፈሩ ፣ እኔን ጠየቁኝ እንጂ ‘ ነሽ ’ ብለው አልስደቡኝ ። እንቺንም የእንግዳ ሚስት አሁን ፣ ‘ ገልሞ ዘመድሽ ነው ወይ ? ’ ብላ በተዘዋዋሪ ነካችሽ እንጂ ፣ ፊት ለፊት ‘ ቅማንት ነሽ ’ ብላ ለመስደብ አልደፈረች ። ጉብርዬን ትፈራለቻ ! ገልሞንማ እን ደዚህም አይጠይቁትም ። እና ፣ አየሽ ልጂ ዐቅም ታለው ሰው ፣ ይሽ ደብ ተሮቹ ፣ ጨዋ ነን የሚሉት ሁሉ የሚያወሩት ዋጋ የለውም ፣ አይቸዋ ለሁ ። ለመሆኑ ጉብርዬ ያውቃል ? ” ሲሉ ጠየቋት በመጨረሻ ።

“ ምኑን ? ” ስትል መልሳ ጠየቀች ። ልቧ ቢያውቅም በእንደበትዋ ማረጋገጡ አሁንም አልሆንላት ብሎ ።

“ ኤሎ ኧረ ባባጃሌው ! ‘ ተኛ በላይ ጉራሽ እህል እበላሽ አሉ ’ ! የአባጃሌውን ልጠላሽ ነው ” ለመሔድ የቃጡ መስሉ ።

“ ይወት ዐይወት ፣ እኔ ምን አባቴን ዐውቁ ብለውኝ ? እኔ አልነገር ኩትም ፣ ምንስ ብዬ ልንገረው ! እሱም እንሥቶብኝ አያውቅም ። ”

“ ቱምድሮስስ ? እሱም አይደለ ያሳደገሽ ? ”

“ እሱማ ሳያውቅ እንዴት ይቀራል ? ” መጀመሪያ ቱምድሮስ ከእ ናቷ ዘንድ ሲመጣ እንዳየችው ፣ እናትዋ ከሞተች በኋላ ከእርሱ ዘንድ እንደ መሰዳት በአሞሩ አወጋቻቸው ።

“ በይ እንግዲህ አሁን መንፈስሽን ላታስጨንቂ ወረፍ በይ ” አሉና በግባበል መልክ ፡ ጸጉሩዋን ከምከም ከምከም አደረጉላት ።

— 2 —

ታንጉት ፡ ከሆድዋ ተቀብሮ የቆየውን ነገር የምታካፍለው ምሥጢረኛ በማግኘቷ አንድ ሸክም እንደ ወረደላት ያህል ቀለል ቢላትም ፡ ከሰዎች ጋር ያላት ግንኙነት ደግሞ በመጠኑ መለወጡ አልቀረም ። እርሷ ላይታ ወቃት በመቀየም ወደእነርሱ መሔድዋን ስለ ቀነሰች ይሁን ወይም እነርሱ በማፈር ወደ እርሷ መምጣታቸውን ስለ ቆጠቡ ፡ ማፈግፈጉ ከየትኛው በኩል እንደ ተጀመረ በትክክል ሳይለይ እንዲያው በያፈናው ፡ ከድሮ ጓደኛቷ ጋር የነበራት ግንኙነትና የምታደርገው ጥያቄሽ እየተቀነሰ ሔደ ። እርግጥ ፡ በማኅበር ፡ በዝክር ፡ በሰንበቱ ፡ ‘ እገሊትን አመጣ አር ጓታል ’ ሲባልና በሌላም ምክንያት ይገናኛሉ ፡ ይጠያየቃሉ ፡ በቤተ ክርስቲያን ፡ በአደባባይ ሲገናኙም ጥቂት ሳይጨዋወቱ አይለያዩም ። ከዚህ በተረፈ ግን ፡ ‘ ውይ ! ሳላይሽ ስንት ቀን ሆነኝ ! ’ ብሎ ወደ እንዳቸው ቤት ጉራ ማለቱ ፡ ወይም “ ምነው ጠፋሽ ? ” ብሎ ልጅ መላኩ ያለፈ ታሪክ እየመሰለ ሔደ ። ጭውውታቸው ስንኳ ወይነቱንና ታናውን ቀይሮ ነበር ። እንደ ዱሮው ተዝናንተው አይቀላለዱም ። ወይም የዱሮ ትዝታቸውን እንሥተው በስሜት አያወጉም ። ስለ ጤንነታቸው ይጠያየቃሉ ። ስለ ዘመቻው ወሬ ይወያያሉ ። ከልባቸው ቢጨዋወቱ ቁስል እንዳይነካኩ የሚጠነቀቁ ይመስላል ።

ምናልባት የቀሩት ግንኙነታቸውን እንደ ዱሮው ቀጥለው ይሆናል ። ታንጉት አታውቅም ፡ ለማወቅም ግድ አልነበራትም ። ብቻ አንዳንድ ጊዜ ሳትፈልግ ፡ ስሟን ሲያነሡና ሲያሚት ፡ በሐሳብዋ ታያቸዋለች ። ይህ ሐሳብዋ ስለ ሌላውም ሰው ያላትን አስተሳሰብ አጉል ጥርጣሬ አከለበት። በመንገድ ላይ የሚያጋጥማትና የማታውቀው ሰው ስለ እርስዋ ዘር የሚያውቅ ይመስላታል ። አንድ ሰው ትኩር ብሎ ቢመለከታት በሆዱ ፡ ‘ ያቺ ቅማንት ! ’ የሚል ይመስላታል ። ልጆች በራሳቸው ጨዋታ ሲጣቁስንኳ በእርስዋ የሚያፈዙ መስሎ ይሰማታል ። ወይዘሮ ደብሬ ባይኖሩኖሮ ፡ ይህ ስሜቷ ቤቷን ዘግታ የምትውል ብቸኛ ያደርጋት ነበር ። ከሌሎች በራቀች መጠን ደግሞ ፡ ከወይዘሮ ደብሬ ጉያ ይበልጥ እየተሸጉጠች ሔደች። ገብርዬ ከሔደ ወዲህ ብዙም እንግዳ ቤቷ አይመጣም ነበር። ወይዛዝርቱ ዐልፎ ዐልፎ ብቅ ብቅ ይላሉ ። መኳንንት ግን ከስንት አንድ ነው ። አብዛኛዉ ወደየሹመቱ ወይም ወደ ዘመቻው ሔድዋል ። ከተማ የቀረውም ቢሆን አባ ወራው በሌለበት ከሰው ቤት መሔዱ ለሌላ እንዳይመስልበት ፡ እምብዛም አይደፍረውም ነበር ። ጋረድ አሁንም አክሊሉን አስከትሎ አንድ ሁለት ቀን መጥቷል ። ታንጉት የቤቷን በእንግዳ ወይም በሰው አለመዘውተር ግን አልጠላቸውም ። እንዲያውም ብቻዋን ከቤት ሥራዋ ወይም ከወይዘሮ ደብሬ ጋር መሆኑን እየመረጠችው ሔዳ ነበር ።

ይህንን ዝንባሌዋን የተገነዘቡት ወይዘሮ ደብሬ በሚያውቁበት ዋዘኛ መልክ ሊያስተዋት ጀመሩ ።

“ ለባብሽና ነይ ፡ ተነሽ እንሒድ ! ” አሏት አንድ ቀን።

“ የት ፡ ወይዘሮ ደብሬ ? ”

“ የትም ! ኧረ ባባጃሌው ! እንደ ባሕታዊ ተዘግተሽ ልትሞቺ ነው ? ነፋስ ይምታና ! መልክሽም ይገረጣል እኮ ! ”

የዕለቱ ሽርሽራቸውና የጉብኝት ጉዞዋቸው በዚህ ዐይነት ተጀመረ ። በመጀመሪያ ፡ በእግራቸው ሆነው ሁለቱ ብቻ በአቅራቢያው የሚገኙትን እየፈራረሱ የሔዱ ግንቦች ፡ አብያተ ክርስቲያናትና ሠፈሮች እያሳዩ ታሪካቸውን ሲነግሩዋት ፡ ከመጽሐፍ በቃላቸው ያጠኑት ይመስሉ ነበር ።

“ ይኸ ግምጃ ቤት ግንብ የሚባለው ነው ። አጤ ፋሲል ናቸው ያሠሩት ። ምድር ቤቱ የመጣፍ ማስቀመጫ ፡ ደርቡ ደግሞ የጣፊ ትዛዙ መቀመጫ ነበር አሉ ። አሁንማ ይኸው ወና ሆኗል ። ይህን ደሞ ዱቄት ግንብ ይሉታል ። ያጤ ፋሲል ነው ። እንጃ እንግዲህ ማቡኪያ ይሁን ወይ የተፈጨ እህል ማስቀመጫ ፡ በውል አላወኩትም ። ያንን ትልቁን የፋሲልን ግንብ መቸም አይተሽዋል ። እሳቸው ናቸው ብዙ ግንብ ያሠሩ ። እሳቸው አይደል ጉንደርንስ የቆረቆሩ ? . . . ይኸም የአንበሳ ግንብ የሚሏለው የአጼ ፋሲል ነው ። አንቶላ ነበራቸው መሰለኝ ። አሁን ቴዎድሮስ እንዳደረገው . . . ”

ከአንዱ ሠፈር ወደሌላው በሚሔዱበት ጊዜ ሁሉ አንደበታቸው አያቋርጥም ። የከተማዉ ሰው ሁሉ የሚያውቃቸው ይመስል ዐላፊ አግዳሚው ፡ “ እንዴት አደሩ ? እንዴት አረፈዱ ? እንዴት ዋሉ? ” ሳይላቸው አያልፍም ። እርሳቸውም በበኩላቸው ፡ ወንዱን ‘ አንተ ወስላታ ’ — ሴቷን ‘ አንቺ ሞልፋጣ ’ ብለው በመጥራት ፡ ሳያሣሥቁና ሳያጨዋውቱ አይለዩም ። እርሳቸው የሚሰነዝሩት የነቀፌታ ቃል ፡ ከማሣቅና ከማቀራረብ በስተቀር በሌሎች ላይ ቅሬታ እንደማይፈጥር ሁሉ ፡ ሌሎች የቀልድ ቃል ሲጥሉባቸው ፡ ከመሣቅ በቀር እያስከፋቸውም ። ከውርደት ስሜት ነጻ የወጡ ነው የሚመስሉት ። ሌላዉም ይህንን ነጻነታቸውን ያወቀላቸው ይመስል በነጻ ያጫውታቸዋል ።

እንደዚህ ግራና ቀኝ ያገኙትን ሁሉ እያጫወቱ ከሌላው የጉብኝት ሥፍራ ይደርሳሉ ። “ይኸ ደሞ የጻድቁ ዮሐንስ ግንብ ነው ። ደግሞም የፍቅር ግንብ ይሉታል ። ምህኖቱን አልደረስኩበትም ። እጤ ዮሐንስ እንደሆኑ ፡ ሰሌን ራሳቸው ሠርተው እየሸጡ ይኖሩ ስለ ነበር ስለ ፍቅር ማወቃቸውን እጠራጠራለሁ — ለዚህ አይደል ጻድቁ የተባሉትስ ? ” ብለው ጣቅ አሉ ።

“ የአድያም ሰገድ ኢያሱ ግንብ ፡ የአጽራር ሰገድ ዳዊት ግንብ — ዘፈን ይወዱ ነበር ይባላል — የመሲሕ ሰገድ በካፋ ግንብ ፡ የቋረኛ ኢያሱ

ግንብ ፣ የራስ ጒርጊስ ግንብ — ” እንዚህንና ሌሎችንም አሳይተዋት ሲጨርሱ ደግሞ በከብት ወደ ቀሃ ወንዝ አካባቢ መሰጹዋት ። ታንጉት የቀሃ ወንዝ ተጠልፎ መዋኛ የተሠራበትን የሩሲያዩስ ግንብ ፣ የዘቢልን መቃብርና ፣ የዶሮ ግንቡን ስታይ በጣም ገረማት ። ሰው ሰፈረስ እንደዚያ ያለ ሕንፃ ይገነባል ? “ የሚወጹት ፈረሳቸው ነበር አሉ ፣ ቢወጹት አይ ደስ የመቃብር ቤት የሠሩለት ! ” ሲሉ ወይዘሮ ደብሬ አስረጹዋት ። ስለ ዶር ግንቡም ቢሆን የሚናገሩት አላጡም ። “ ብልሆችማ እንደዚህ ያለ መልካም ቤት እሠርተው ዶሮዋቸውን ራሳቸው እያረቡ ይኮመኩሙ ነበር ። ከጦት ሙቴ ደጃች ውቤ ይሻላሉ ። ስንት ዉርት እንደሚሰፉበት ዐላውቅም እንጂ አንድ ጋን ሙሉ መርፌ አስቀምጠው ነበር ይባላል ፣ ቴዎድሮስ በኋላ የማረከው ። በሞቴ እስቲ አንድ ጋን ሙሉ መርፌ ያታ ብራል ሰው ? ቴዎድሮስስ እንዲህ ያለውን ሁሉ እለውጣለሁ ብሎ የሚ ለፋው ? ..... እስቲ እሱ ይሁንዋ ! ” ንግግራቸው እንዳንድ ጊዜ ካንዱ ወደ ሌላው ይዘላል ።

“ ቁስቋም ማርያምን የተከፈትና ይህንን ግንብ የሠሩትማ እቴጊ ምንትዋብ ናቸው ። ” ዳንቴን ወጥተው ከወፀደ ቤተ ክርስቲያኑ ዐረፍ ብለ ዋል ። “ መልካቸው ውብ ፣ ጠባያቸው ውብ ፣ እንዲያው እጂን ታጥቦ ታለስንካ የፈጠራቸው ነበሩ ይባላል ። እስቲ ይታይሽ ! ዛሬ እንኳን ሴቴ ወንዱስ እንዲህ አስቦ ይሠራል ? ዛሬያ ብዙ ጊዜ ሱባኤ እየገቡ ተዚህ ነበር የሚቀመጡት ይባላል ። ”

ታንጉት ለመጀመሪያ ጊዜ ጉንደር ከወደ ታች በሰሬው ተንጣልሎ ታያት ። “ ደስ እይልዎ እማማ ደብሬ ? ” አለቻቸው አጠራርዋ ፡ ከወ ይዘር ወደ እማማ ተሻግር ነበር ። ላይታወቃት ነበር የጀመረችው ።

እርሳቸውም ፡ “ አሆሆ ! አርጊት አረግሽኝ ? ኧረ አሁንም ግደባይብ እያቅተኝም ! ” ሲሉ ቢቀልዱም ወደውታል ። “ ሰው ታሳማሪ ምን ፉይዳ አለው ! ” ብለው መለሱላት ፡ ባልተለመደ የትካዜ መልክ እሻግ ረው እየተመለከቱ ።

ጉብኝታቸው ከጉንደር ከተማ ከልልም እየወጣ ሔዶ ። ሩሲል ፡ በአ ንገርብ ፡ በመጣው ወንዝ ላይ ያሠሩዋቸውን ድልድዮች ፡ ከዚያም ርቀው ግሸና አጀከር በመያዝ ፡ በጉርጉራ የሱስንዮስን ግንብ ፡ የናግራ ሥላሴን ገዳም ፡ በአንፍራዝ ባሕሪ ግንብን እንድታይ አደረጉዋት ።

ወይዘሮ ደብሬ ፡ ታንጉትን በየሥፍራው እያዘዋወሩ ብዙ አስደሳችና አስደናቂ ነገር ሲያሳዩዋት ፡ በአውነትም እንዳሰቡት ወደ ራስዋ ብቻኝነት ግጀንብልዋ እየጠሩ ከመሔዱ በላይ ፡ ስለ ቴዎድሮስ ዓላማና ምጥንዋ ጭላንጭል ይታያት ጀመር .....

... ከዜመች መልስ ፡ ከውሎ ጉዞ በኋላ ከተሰማሚ ሥፍራ መሬ ይተኩላል ። እህል ውሃ ከተባለ በኋላ አባ ታጠቅ ከባለሟሎቻቸው መከል ተቀምጠው ዉዋታ ይጀመራል ። አባ ታጠቅ ፡ አንድ ምልክት በሩቁ የሚያዩ ይመስል ፡ ወይናቸውን ከአድማስ ላይ ተክለው ጥንት ታሳቅና ገናና ስለ ነበረችው ኢትዮጵያ እንደ ሰመመን በተመሰመ ትዝታ ይተርካሉ ። አሁን ደካማ ሁና ፡ ተከፋፍላ ፡ ሕዝብዋ ተጉላቷሎ ስለሚገኝበት በሚያ ወጉበት ጊዜ ደግሞ ፡ ንግግራቸው የትካዜና የቁጭት ቃና ይይዛል ። ‘ ጉበዝ ዛሬያ አገራችን እንዲህ ሆና ትቅር ? ’ ሲሉ ባለሟሎቻቸውን በግበረታታትም በግሩጠጥም ይጠይቃሉ ። እንደገና ትልቅና ገናና መሆን አለባት ብለው ስለሚያስቧት ኢትዮጵያ ሲገልጹ ፡ ታንጉት በጊዜው ነገሩ ብዙ ባይገባትም ፡ ወደ አንድ ጥግ ሆና ስታጻምጣቸውና ሁኖቴያቸውን ስትመለከት አብሬ ትመሰጣለች ። በሕልማቸው የሚያዩ ዋትን ኢትዮጵያ ለማየት ትሞከራለች ። ግን ረቂቅ ፡ ሥውር ምስጢር ትሆንባታለች ...

አሁን ግን ፡ የደከመ ሕሳቤዋን ለማሳረፍ ከአልጋዋ ላይ ጋደም ብላ ስትጉበኛቸው የዋለቻቸውን የሚያስደንቁና ዛሬ ግንኙየረጂና እየፈረሱ የሔዱ አብያተ ክርስቲያናትና ግንቦች እንደገና በሐሳብ ስታያቸው ፡ በሕ ሊናዋ የሚነው ፡ ‘ እነዚህ ሁሉ አጸዲስ ቢሆኑ ኖሮስ ! እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች ብዙዎች ቢሠሩስ ? ’ የሚሉ ጥያቄዎች በማም ግልጽም ሳያሆን ቴዎ ድሮስ ስለሚያልሟት ኢትዮጵያ መጠነኛ ግምት ይሰጡዋት ነበር ።

በጣም ሩቅ ያልሆኑትን የጥንት ቅርሶች አስጉብኝተው ከጨረሱ በኋላ ፡ ወይዘሮ ደብሬ አንድ ቀን ፡ “ ገብርዬ ሲመጣ የማይቆጣሽ ተሆነ አሁን ደግሞ ደልጊ እንሒድ ” አሏት ።

“ እሱማ ምን ያስቆጣዋል ። ግና ፡ ደልጊ ፡ ምን አለ ? ” ስትል ጠየቀ ቻቸው ።

“ ዜመዮሮን አሳይሻለኋ ! ”

“ አልተዋል አላሉኝም ? ”

“ የተረፈ ዘር ተለለኝ እርሜንስ ባወጣ ? ”

“እስከ ዛሬ የናሩ ኑረው ? ሰውስ ምን ይሉዎታል ? ”

“ መሔድ ደስ ታላለሽማ መቸስ ! ” ብለው እንደ ቅሬታ ነገራቸ ውን አንጠልጥለው ተዉት ።

እለቅሶ ለመድረስ ፡ ወይም ጀመድ ለመጠየቅ የሰንት ቀን መንገድ መሔዱ ታንጉትን በእርግጥ ደስ አላላትም ። ግን ደሞ ፡ እርሳቸው ልክርፎ ሲሉ ምን ያህል ሲደክሙ ልታስቀይማቸው ቀርቶ ለብዙ ጊዜ መደየቱ ንም አልፈለጎትም ። “ እኔ ምን ቸገረኝ እንሒድ ! ” አለቻቸው ።

ሁለት ቀን ሙሉ ተጉዘው ነው በሞስተኛዉ ቀን ደልጊ መንደር የደ ረሱት ፡ የሳምንት ቅዳሜ ገበያ ደመቅመቅ ማለት በያዘበት ከረፋዱው

ላይ ነበር ። እህሉ ፡ ቅመማ ቅመሙ ፡ ጥጡ ፡ ሽማዉ ፡ ከመቶማ የመጣው ጨርቃ ጨርቅ ፡ እህሉ በመያዳው ተዘርግቷል ፡ የጋማና የቀንድ ከብቱ በየመኻሉ ተሰግስጓል ። ገበያተኛው ይተራመሳል ፡ ያወካል ፡ ከአንዳንዱ ቦታ ከምችት ብሎ አፍ ላፍ የሚነጋገር ይመስላል ፡ ሌላዉ ዘንድ እጁን እያወራጨ ይንጫጫል ። የሁሉም ድምፅ ባንድነት ሆኖ እንደ ውሃ ሙላት ያተምማል ። ከአሸዋ ቀመሱ መሬት የሚነሣው አቧራ አንዳንድ ጊዜ እንደ ጢስ ወይም እንደ መጋረጃ ሰውን ከቅልጥሙ በታች ሽፍን ያደርገዋል ። መልሶ ወደታች ይወርዳል ።

ወይዘሮ ደብሬ ፡ ከጉብታ መሳይ ቁመው አጠቃላዩን በዐይናቸው ኪቃኙ በኋላ ፡ “ ድንኳን ተዚያ ፡ትከሉ ” ሲሉ አሽከሮችን አዘዙ ፡ ደኅና ጥላ ወደ አለው የግራር ዛፍ በእጃቸው እያመላከቱ ። እሳቸውም ፡ አቧም አንዳንድ ድንኳን ይዘው ስለ ነበር በሁለቱ ቀን ጉዞ እየተጠቀሙባቸው መጥተው ነበር ።

ታንጉት ፡ የጉዞዋቸው መጨረሻ መሆኑን አስባ ምክንያቱ ስላልገባት፡ “ ለምና ? ገበያ ላይ ድንኳን ተመትከል ቤት ብንገባ አይሻልም ? ” ስትል ጠየቀቻቸው ።

“ የምን ቤት ? ”

“ ተዘመዶችዎ ነዋ ! ”

“ ዘመዴን ተገበያ ላይ አሳገኘውም መሰለሽ ? የተጠፋፋው ሰው የሚገናኘው እንዲያውም ተገበያ ነው ልጄ ። ”

“ ልቅሶውን ሳይደርሱ ? ” ።

“ ኧረ ባባጃሌው ! እስቲ መጀመሪያ በሕይወት ያሉትን እንያቸው ። ይልቅስ ድንኳኑን ቀልጠፍ በሉ ልጆች ! ” ሲሉ አዘዙ ።

ድንኳኖቹ ተተክለው ፡ ሁለቱ በአንዱ ድንኳን በር ጥግ በድኳ ላይ ሲቀመጡ ፡ ወይዘሮ ደብሬ ለጥቂት ጊዜ ዝም ብለው የገበያውን ትርምስ ሲያስተውሉ ቆዩ ። “ እውነትም የቴዎድሮስ ልፋቱ ሁሉ መልካም ነው ። ገበያው ቅልጥ ብሎ የለ ! የዛሬ ሦስት ዓመት የመጣሁ ጊዜ ፡ የአንድ ደብር ሰንበቱ የሚያክሉ ገበያተኞች ብቻ ነበሩበት ። አሁንማ የጉንደርን ቅዳሜ ገበያ ሊያክል ምን ቀረው ! ” አሉ በማድነቅ ።

ልጅ ልጁ ጨዋታውን ፡ ትልቅ ትልቁ ገበያውን እየተወ ፡ ለመቅረብ የፈራ ይመስል በሩቁ ነብ እየሠራ ይመለከታቸው ጀመር ። የጉንደር ሰው ለገጠሬ ብርቅ ነው ። አንዳንዱ እርስ በርሱ ይንሾካሾካል ። ሌላዉ በመገረም በትሩን ተደግፎ ያስተውላል ። ቀረብ ብሎ እጅ ለመንሣትና ለመተዋወቅ እየቃጣው ፈራ ተባ የሚልም አለ ። ቀስ በቀስ ፡ ዙሪያውን ገለባ እንደ ተቆለለበት አውድማ ተከበቡ። አሽከሮቻቸው “ ወጊዱ እንጂ”

እያሉ ለመበተን ሲሞክሩ ፡ “ ተዋቸው እንጂ ያገሬ ባላገር ሁሉ ብርቁ ድንቁ አይደለ ? ” ማለታቸው ታንጉትን የባስ አስገረማት ። እርሷ ከዚያ ሁሉ ሰው ጋር መፋጠጡ አስጠልቷት ነበር ። ወይዘሮ ደብሬ ግን ፡ ዙሪያቸውን ከቆመው ልጅና ትልቅ ሰው ጋር የዐይን ድብብቆሽ መጫወቱ አስደስቷቸዋል ።

“ ብንሔድ አይሻልም እማማ ደብሬ ? ” ስትል ታንጉት በማሳዘን ቃና ጠየቀች ።

“ የት ? ” አሏት አሁንም ።

“ ተዘመዶችዎ መንደር ነዋ ! ”

“ ዘመዶቹ እኻሁና ! ” አሉ ዙሪያ ከቆሙት ሰዎች በደፈና እያመለከቱ ።

ከወትሮውም ጨዋታና ቀልድ ከማብዛታቸው ጋር አሁን ምኑም የማይገባ ነገራቸው ፍጹም ግራ ሲያጋባት ፡ ‘ እህ ጤነኛም አይደሉ ኖሯል ? ’ ስትል ራሷን ጠየቀች ።

ወይዘሮ ደብሬ ፡ የታንጉት ሐሳብ የገባቸው ይመስል ፡ ዘወር ብለው በፈገግታ ተመለከቷትና እጃቸውን ዘርግተው በሌባ ጣታቸው እየጠቆሙ ፡ “ ነይ አንቺ ፡ ኧረ ባባጃሌው ነይ እንጂ ! ” ሲሉ እንዲን ኮረዳ ጠሯት ። ከተርታው ትንሽ ወጣ አለችና መልሳ ተቀላቀለች ። “ ኧረ ባባጃሌው ! ነይ እንጂ የወንዜ ልጅ ። ኧረ ባባጃሌው አሁን ምኑ ያስፈራል ? ” አውራ ጣትዋን በጥርሷ እየበላች አቀርቅራ ቀረበች ። “ጠጋ በይ” አሏት። አሁንም እያመነታች ከፊታቸው አጉንብሳ እንደ ቆመች ፡ “ ቅማንት ነሽ ? ” ሲሉ በድንገት ጠየቋት ።

ታንጉት ፡ ጥያቄውን ስትሰማ ክው ስትል ፡ ኮረዳዋ ግን እስከዚህም አልደነገጠችም ። ለአከብሮትም ይሁን ወይም በፍራቻ ዐይኗን ወደ መሬት እንዳቀረቀረች ዝም ብላ ቆመች ። “ ኧረ ባባጃሌው ! ቅማንት ነሽ ወይ ነው የምልሽ ! ” አሏት ወይዘሮ ደብሬ ኮስተር ብለው ። ልጅቷ በመገረም አንድ መዳፏን ከጆሮ ግንዷ ላይ አስደግፋ መልስ ሳትሰጥ ወደ ኋላ ልትመለስ ስትል ፡ ወይዘሮ ደብሬ ከተቀመጡበት ተፈናጥረው ሌላ እጂዋን ለቀም አደረጓት ። ታንጉት በሕልም ውስጥ ያለች ይመስል ከመደናገር ዐልፎ ዞረባት ። ግን ፡ በእንዳች ዐይነት ሥውር መገንጪስ እንደ ተያዘች ትኩር ብላ መመልከቷ አልቀረም ።

“ አይዞሽ አትፍሪ፡ የወንዝሽ ሰው ነኝ ። ምን አሳፈረሽ ? ‘ቅማንት ነሽ ወይስ አይደለሽም ’ ብዬ ነው የጠየቅሁሽ ? ” የከበበው ሰው አብዛኛው ንግግሩንም በሚገባ ሳይሰማ በሁኔቴው ተገርሞ እርስ በርሱ ያውካካል ።

ኮረዳዋ ፡ የአሉታ ፡ ወይም የአወንታ መልስ ሳትሰጥ ፡ ባልተያዘው እጂዋ የሚያለቅስ ዐይኗን እያሸች በኃይል ነጥቃ ማምለጡንም ፈርታ ፡ ከቆ

መችበት መቆላመሙን ቀጠለች ። ወይዘሮ ደብሬ፣ ‘‘አትነግሪኝም ? አትነግሪኝም ? ሒጅ በይ ! ’’ ሲሉ ለቀቋት ። እንደ ጦር በመወርወር የሰዉን ቀለበት ሰንጥቃ ተፈተለከች ። የሰዉ ሁካታ በእንዴ አስተጋባ ። ታንጉት ፣ አጉል ሕልም ትርዒቱ አፍዝዞ ቢይዛትም በልቧ ከልጅቷ ስሜት ጋር አብራ ተሠቃየች ። ወይዘሮ ደብሬ ሁካታው ጋብ እስኪል ጠበቁና ዙሪያውን ሰው ፈለጉ ። ጥርሱን መንቀል ከጀመረ ተራ ልጅ ላይ ዐይናቸው ዐረፈ ። ‘‘ ና እስቲ የኔ ድንቡሽ ! ’’ አሉና እንደሚታቀፍ ሁለት እጃቸውን ዘረጉለት ። በልጅ ድፍረት መጣና ከፊታቸው ቆመ ። በቁልምጫ ጉንጩን ቆንጠጥ አርገው ጠየቁት ። ‘‘ እንተስ ምንድነህ ? ’’

‘‘ የናኔ ልጅ ነኛ ! ’’ አለ ባለማመንታት ።

‘‘ ናኔስ ምንድናት ? ’’

‘‘ የኔ እናት ናታ ! ’’

‘‘ ቅማንት ናችሁ ? ’’

ልጁ በጥያቄያቸው እንደ ጅል የቈጠራቸው ይመስል ፣ በመገረም ተመልከቷቸው እየጣቀ ወደኋላ ተመለሰ ። አሁንም ሁካታው አስተጋባ ። አሁን የከበባቸው አብዛኛዉ ሰው ነገሩን እንደ ጨዋታ እየቈጠረው ሔዶ ነበር ። ወይዘሮ ደብሬ ፣ አሁንም እንደገና ዐይናቸውን ከዳር እስከ ዳር አዞሩና ፣ አፍንጫውን በነጠላው ዳርቻ ሸፍኖ ፣ በትሩን ተደግፎ ከቆመ ጉሪምሳ ላይ አተኮረ ። ‘‘ አንተ ጉበዝ ! አንተ ጉበዝ ’’ ብለው ተጣሩ ። ባጠገቡ ያሉት እርስ በርሳቸው ተያዩ ።

‘‘ እኔን ነው ? ’’

‘‘ አዎ ፣ እስቲ ና ! ’’

ነጠላውን ካፍንጫው ላይ አውርዶ ቀረበ ።

‘‘ አንተስ ምንድነህ ? ’’

በመናደድ ሳይሆን በመገረም ኮስተር ብሎ ተመለከታቸው ፣ ‘‘ እህ? ’’

‘‘ ዘር የለህም ? ’’

‘‘ እህ ! አለኝ እንጂ ! ’’

‘‘ እዛዲያስ ዘርህ ምንድነው ? ወይጦ ነው ? ’’

‘‘ ኧረ ! ’’

‘‘ ቅማንት ነህ ? ’’

‘‘ ኧረ ! ’’

‘‘ አማራ ነህ ? ’’

‘‘ አወና ! ’’ አለ እርግጥ አድርጎ ። ሰው ሁሉ ሲሥቅለት ፣ አብሮ እየሣቀ ወደ ሥፍራው ተመለሰ . . .

‘‘እየሽ እይዶል እንግዲህ ጉዳችንን ! ’’ አሉ ወይዘሮ ደብሬ ፣ በአንድ እጃቸው የሚበሉትን ምግብ እያሰናዱ ፣ አንድ እጃቸውን በማመልከት አኳኋን ወደ ገበያው አግጣጫ ዘርግተው ። ወይዘሮ ደብሬ የመጡበትን ጉዳይ ከጨረሱ በኋላ ፣ ከገበያው ትርምስ ለመራቅ ፣ ድንኳን አስነቅለው ፣ ከመንደሩ ጀርባ ሠዋራ ሥፍራ ላይ ሠፍረው ነበር ። ‘‘ እያገርም ሽም ? ! ’’ አሏት ዐይኖቻቸውን እያቁለጨለጩ ። ታንጉት መግረሙን ገርሟት ፣ አገጯን በመዳፏ አስደግፋ የሌሰ ነገር የምታይ ትመስል ነበር ። ግን የምትሰጠው መልስ አልነበራትም ።

‘‘ ኧረ ባባጃሌው ! ምን አፈዘዘሽ ? ነቃ እንድትይ ነበርኮ ያመጣሁሽ ። ’’

‘‘ ይህንን እንዳይና እንድሰማ ? ’’

‘‘ አወና ! እየሽ ፣ ቅማንቱም ፣ ወይጦውም ፣ አማራውም ሁሉም እግዜር የፈጠራቸው ሰዎች ናቸው ። መልካቸው አይለይ ! ወይ እነዚያ ጅራትና ቀንድ የላቸው ። በሥራም ፣ በሙያም የሆነ እንደሆነ ፣ አይተና ነሱ ። እኩል ሠርተው ያድራሉ ። እንዲያውም ፣ ወይጦቹና ቅማንቶቹ ይበልጣሉ በሥራ ። ዛዲያ ያች ልጅ እንዳየሻት ፣ ‘ ቅማንት ነሽ ወይ? ’ ብዬ ስጠይቃት ፣ ‘ አይደለሁም ’ እንዳትል መሆንዋን ታውቃለች ። ‘ ነኝ ’ እንዳትል ደግሞ አፈረችበት ። ዝም ብላ መቅለስለስ ! ኃፍረትነቱን ገና ያላወቀው ትንሹ ልጅ ይሻላል።ሥቆብኝ ሔዳ! ያኛው ግን፣ ‘ቅማንት ነህ ወይ?’ ብየ ስጠይቀው አስተባበለኝ ። አማራ ነህ ወይ ስለው ደግሞ ‘ አወና ! ’ አለኝ ተኩራርቶ ። ይኸን ሁላ ዛዲያ ምን አመጣው ? እነዚያ ለምን ያፍሩበታል ? እንዲያውም ለነገሩ እኔስ አንቺስ ብንሆን ለምን እናፍርበታለን ? አያስገርምም ? ’’ ውሃ እያርከፈከፉ በሶውን ማሸት ቀጠሉ ።

‘‘ ግን ምን አሳሰበዎትና ይዘውኝ መጡ ? ’’ ስትል ታንጉት ጠየቀች ። መገረሙ ሀልፎላት ፣ በወይዘሮ ደብሬ አመለካከት ነገሩን ሲታስበው እውነትም ፣ ‘ ለምን ’ የሚል ጥያቄ አሳደረባት ።

‘‘ እኔም ራሴ ታውን ቀያም መጥቸ ነበራ ! ’’

‘‘ እንዳሁኑ ለመጠየቅ ? ’’

‘‘ አወና ! ’’ አሉ ወይዘሮ ደብሬ ፣ ነገሩን ለማስታወስ ይመስል ፀይናቸውን ሰለምለም አደረጉ ። ‘‘ ‘ነግሬሽ የለም እንድ ወታደር እንደ ሰደበኝ ? በኋላ ቅጣቱን ሊያገኝ ! ዛዲያ ነገሩ ሲከነክነኝ ይኖር ነበር ። ደጃች ተድላ ይወዱኛል ። ሌላዉም ፣ መኳንንቱም ፣ ወታደሩም ዕድል ታገኝ ልጋይል ብሽ ይላል ። ‘ዘሬ ዛዲያ እንደ ነውር የሚታየው ለምንድን ነው?’ እያልኩ። ሀብትም ፣ ከበሬታም ታገኘው በኋላ ምን እንዳሳሰበኝ አላውቅም ፣ ‘ እስቲ

የተሰደብኩበትን የወገናቼን ጉድ ልይ' ብዬ ወደዚህ መጣሁ ። እንደ ዛሬዉ የገበያ ቀን ነበር ፣ የምገዛ መስዬ አንድዋን ባለቅቤ አስጠራኋት ። እንዲ ያው ውብ መልከ መልካም ናት ። ላዩን ሽተት አረኩና ፣ ' ውስጡ ሁሉ ጥሩ ነው ? ' ብዬ ጠየኳት ። ገንቦ ሙሉ ነው ። ' አወን ' አለችኝ ። ለመ ጠየቅ ሰበብ ፈልጌ ፣ 'የቅማንቶች ቅቤ ጥሩ ነው ይባላል ። የቅማንቶች ቅቤ ነው ? ' ብዬ ጠየኳት ። ' ይሆን ይሆናል ' አለችኝ ። ' ምን ይሆን ይሆናል ፣ ያንቺ ቅቤ አይደለም እንዴ?' ብዬ አፋጠጥኳት። ጥቂት አቅማማ ችና ' ነው እንጂ ' አለችኝ ። ' ዛሬያ እንቺ ቅማንት ነሽ ፣ አይደለሽም ?' ተዚያ በኋላ ዝም ። ባረጋት ብሠራት ልትመልስልኝ መሰለሽ ? ታለሳ ኋት አይቀር ብዬ ገዛኋትና ሌላዋ ዘንዳ ተጠጋሁ ። ማር በትልቅ ቅል የያዘች ናት ። ላዩን በጣቴ ጠንቆል አደረኩና ፣ 'ውስጡ በሙሉ ነጭ ነው ፣ እንደ ላዩ ?' ብዬ ጠየኳት ። ' አወና 'አለችኝ ። አሁንም ቀጠል አረኩና ፣ ' የቅማንት አገር ማር ውሃ ያነሣል ይባላል ። የቅማንት አገር ማር ነው ? ' ማለት ። ነገሩ እንደ አዲስ ሣቅ ያመጣባቸው መሰሉ ። ' ትኩር ብላ አየች ኝና ' ቅማንት ንብ ታለ ተኛ መንደርስ የለም ? ' አትለኝም መሰለሽ ! ' አማራ ነኝ ' ማለቷ ነዋ ! እንደ በገንኩ መብገን መቸስ ምን ብዬ ልን ገርሽ ። ተዚያ ምን እንዳሳሰበኝ አላውቅም ብቻዬን ወደ አንድ ሠዋራ ሥፍራ ሔድኩና መዓት ጊዜ ይሆናል ፣ ለራሴ በራሴ ፣ ' እኔ ቅማንት ነኝ! እኔ ቅማንት ነኝ ! ' እያልኩ ጮህኩ ። እውነትም ወጣልኝ ፣ ቀለለኝ ፣ ተዚያ በኋላማ ፣ ሰው ቢያማኝ ፣ በአሽሙር ቢነካኝ ተመጨፍ የማይሰማኝ እየሆነ ሔደልኛ ! ''

'' እና ፣ ' አንቺም አሁን ጫካ ሔደሽ ተራስሽ ጋር ጨረሺ ነው ' የሚሉኝ እማማ ደብሬ '' አለች ከት ብላ እየሣቀች ። አንዳች ሸክም የወረደላት የሚመስል ስሜት ድንገት ሠርጾባት ነበር ።

'' ታሰኝሽ ምናለበታ ! ግና ቁም ነገሩ '' አሉ ወይዘሮ ደብሬ ንግግ ራቸውን ለማስረገጥ ራሳቸውን ነቅነቅ እያደረጉ ፣ '' ችግሩ ያለው ተራ ሳችን መሆኑ ነው ። የዘር ውርደታችን በኛው በራሳችን ውስጥ ተተሰግን ፣ እሣር ቅጠሉ ሁላ ፣ የሚዘባበትብን ፣ የሚሰድበን ፣ የሚያሽሟጠጠን፣ የሚ ያማን ይመስለናል ። ቅማንትም ሆንኑ ወይጦ ፣ እኛው ራሳችን ተውስጣ ችን ብንሆንሳ ምንተዳየ ! ብለን ታመንበት ፣ ሲሆንም ተኮራንበት ግና ፣ ውጭ ሰው የሚለን አያስጨንቀንም ። አያሠቃየንም ። እንዲያውም ፋይዳ አንሰጠውም ። ዐቅም ፣ ማለቴ ፣ ሀብትም ፣ ከበሬታም ታለን ደሞ ፊት ለፊት ደፍሮ ' እንዲህ ነህ ፣ እንዲህ ነሽ ' የሚለን የለም ። በሆዱ የሚለንንም እየቆየ ሲታክተው ይረሳዋል ። አሁን ገልሞን ተፊቱ ማን የሚናገረው አለ ? ራሱ ውስጥ ውስጡን የሚያመው ታልሆነ በቀር ። አንቺንም ቢሆን ፣ ገብርዬ አስታለልሽ ፣ አባ ታጠቅ አስታለልሽ ደፍሮ ፊት ለፊት የሚናገርሽ የለም ። ቢበዛ ፣ እንደዚያች የእንግዳ ሚሽት በሥ ውር ዘዬ ነው ። ያን ጊዜ ' አወ ! ' ብትያት ኖሮስ ? ራስዋ ነበር የምታፍ

ረው ። እና አሁንም የሆነ እንደሆነ ፣ ተዚህ ድረስ አምጥቸሽ ጉድ ያሳ የሁሽ ለዚህ ብዬ ነው ። እንግዲህ ራስሽ ለራስሽ ዕወቂበት ። ለመሆኑ ፣ በነገር ነዘነዝኩሽ አይደል ? ''

'' ለኔ ብለው ነዋ ! '' አለች ታንጉት ዐቅፋ መሳም እየከጀላት ።

'' እንግዲህ ይብቃን ። ' የሰማነውን በልቦናችን ያሳድርብን ' ነው የሚሉት ቄሶቹ ? አሁንስ እህል እንቅመስ ። ''

ወይዘሮ ደብሬ ፣ ከስንት ዓመት በፊት እንደሆኑት ሁሉ ታንጉት የሐ ላብ መቅለል ይሁን የመንፈስ ነጻነት ፣ ከውስጥ አንዳች ለውጥ ተሰም ቷት ወደ ጐንደር ተመለሰች ።

— 3 —

ገብርዬ ፣ ከሸዋ ዘመቻ እንደ ተመለሰ በታንጉት ላይ የደረሰውን አን ዳች ዐይነት ለውጥ የተገነዘበው ወዲያውኑ ነበር ።

እግሩን ክፉኛ ቆስሎ ፣ ቁስሉም አመርቅዞበት ጐንደር ድረስ የመጣው በቃሬዛ ቢሆንም ፣ ብዙዎቹ የጦር አዝማች በዚያው ሲቀሩ እርሱ በሕይ ወት በመመለሱ ከተሰማት ደስታ ጋር ፣ ሳያስፈልግ አንዴ ትራሱን ፣ ሌላ ጊዜ የመኝታ ጋቢውን እያስተካከለች ፣ ከዚያ በፊት አይቶት በማያውቀው ሁናቴ ስታቆላምጠውና ፣ የባጥ የቆጡን ስታጫውተው በመገረም ተመ ለከታት ። ወትሮም ቢሆን እንደበተ ዝግ አልነበረችም ። ነገር ግን ፣ ምና ልባት ከሴት ጓደኞቿ ጋር ካልሆነ በስተቀር ፣ ከእርሱም ሆነ ከሌሎች ሰዎች ጋር ስትጨዋወት ፣ በማፈርም ይሁን ልማድ ሆኖባት ፣ አንገቷን ቀልበስ ፣ ዐይኗን ሰበር ታደርግ ነበር ። ብዙውን ጊዜም ከጨዋታ እፍ ላቂ ይልቅ ተቀባይና ሲያስፈልግም በዚያው ላይ አክታታይ ናት ። ቃላት የምትቆጥብ ይመስል ነገርዋ የተመጠነ ነው ። አሁን ፣ በአስተያየቷም በአንደበቷም ተዝናንታ ጨዋታዋ እንደ ምንጭ ውሃ ኩለል ብሎ ይወርዳል ።

'' ታንጉት አዲስ ሰው መሰልሽኝ ! እነኝህ ጐንደሮች ለወጡብኝ መሰለኝ '' አላት ገብርዬ ጨዋታዋን ሲያዳምጥ ቆይቶ ። አመለካከቱ ግን የፍቅር ነበር ።

'' መጥፎ ነገር አየህብኝ ? ''

'' ደስ ደስ የሚል ነገር እንጂ ! ''

'' ጐንደሮች አሠለጠኑኛ ! ''

'' ዋ ! አባ ታጠቅ እንዳስጠነቀቁሽ እንዳያሴጥኑሽ ኋላ ! '' የቀልድ ማስጠንቀቅ ነበር ።

“ ላንተ ደስ ደስ ታሰኘሁህ ምን ቸገረህ ! ስቀልድህ ነው ባክህ ” አለች መለስ አድርጋ ። “ አንተ ተሔድክ ተብዙም ሰው ጋር አልተገናኘሁ ። አዲስም ወዳጅ የለኝ ! ወይዘሮ ደብሬ ብቻ አልተለዩኝም ። ”

“ እሳቸውን ሴትዮ ሙጥኝ ብለሽ ይዘሻቸዋል ? ”

“ ብቻዬን ስሆን እሳቸው ናቸው ያኳረሙኝ ልጄ ! ” አለችና ፣ ጊዜ ውን እንዴት በጉብኝት ያሳልፉት እንደ ነበር በዝርዝር አሜወተችው ። የደልጌውን ግን አልነገረችውም ። ምክንያቱን መግለጽ ነበረባት ። ለዚህ ደግሞ ገብርዬ ምን እንደሚሰማው አላወቀችም ። ጋይንቶች በዘር ጉዳይ ጥብቅ እንደሆኑ ሰምታለች ። ከፈለገ ቴዎድሮስ ራሱ ይንገረውና መላ ይፈልግለት ብላ ወሰና ነበር ።

“ እሺ በጄ ! ” አለና ገብርዬ በእጅዋ ወደ አልጋው ሳብ አረጋት ።

“ ዋ ! እኔ ኋላ የለሁበትም ቁስልህን ! ” አለች ፣ እጅዋን ለማስለቀቅ ወይም ለመራቅ ሳትሞክር ።

“ ለምን ተቆርጦ አይወድቅም ! ”

“ አሆ ! አንተስ ጉደኛ ነህ ! ባንድ እግር ልትዋጋ ? ”

“ ፈረሰኛ እሆናለኋ ! ” አለና ደረቷ ትከሻውን እስኪነካ ድረስ ጐትቶ አስጠጋት ።

“ ዛዲያ ቆይ እንጂ የእልፍኙን በር ልዝጋው ። ” ተመልሳ ከጐኑ እንደ ተጋደመች ፣ “ አሁን ማ — ይሙት ድፍን ሸዋን ስታዳርስ ፣ እኔነኝ እንጂ ተዚህ ተኩራምቼ የከረምኩ ! ” አለች በውሸት ቅፌታ ።

“ እንቺማ እንዲያውም ፣ የኩተማው አውደልዳይ ማር ቅጠል በሆነ በት . . . ”

“ እኔ ታንጉት ! ”

“ እኔ ገብርዬ ! ”

“ እስቲ እንማማል ! ” ገብርዬ ዝም ብሎ ሲደባብሳት ፣ “ ፈራህ አይደል ? ” ስትል ጠየቀችው ።

“ ምን አስፈራኝ ! ”

ክርክሩዋን አልቀጠለችም ። ሁለቱም ወዲያው ረሱት ።

በኋላ ሁለቱም በረካ መንፈስ ከንድ ለከንድ በመንተራረስ ተጋድ መው እንዳሉ ፣ ገብርዬ ዐይኖቹን ስልምልም በማድረግ የተመሰጠ የሚ መው እንዳሉ ፣ ገብርዬ ዐይኖቹን ስልምልም በማድረግ የተመሰጠ የሚ መስል ፊቱን ተመለከተችና ፣ “ ምን እያሰብክ ነው ? ” ስትል ጠየቀችው።

“ ዕድሌን ነዋ ! ”

“ የምን ዕድል ? ”

“ አንቺን ለሚሸትነት ፣ አባ ታጠቅን ለመሪነት የሰጠኝን መልካም ዕድሌን ነዋ ! ” ሲል መለሰላት ። ይህ አባባሉ የልቡ እውነት ቢሆንም ፣ እርሷን በሐሳብ ላይ ላለመጣል ብሎ ነው እንጂ አእምሮው ሌላም ዕድል እያሰላሰለ ነበር ፣ የልጅ ዕድል ።

ታንጉት መንፈሷን ቅልል ብሎት እንደ ቆየ ሁሉ ፣ ከሸዋው ዘመቻ መልስ የዕለት ተዕለት ኑሮዋ ፣ ከወትሮ ሞት ደመት ባለ መልክ ቀጠለ ። ከበነጋው ጧት ጀምሮ ጠያቂው ይጉርፍ ጀመር ። የሚመጣው ምግብና መጠየ ንዳ ጠበበው ። ከብቱ ግቢውን በረት አስመሰለው ። ገብርዬ ፣ በአዳራሹ ለቁስለኛ በሚያመች ድንክ አልጋ ላይ ዐረፍ ብሎ ፣ ጠያቂዎ ቹን እያመሰገነ ሲቀበል ፣ ታንጉት እንደ ፈተኛው ማስተናገዱ አላደና ገራትም ። አሁን የገብርዬን የወዳጅነት ቡራኬ ያገኙት ወይዘሮ ደብሬም በቤቱ አድራጊ ፈጣሪ ሆኑበት ። ‘ የቴዎድሮስን ጦር የመንዝ ገደል በላው ’ እያለ ሲያሟርት የነበረው ሁሉ ለምን ጊዜው ተለውጦ ውርንፃ ተቀባይ መምሰሉ ቢያስገርማትም ፣ በራሷ ደስታ ተውጣ ስለ ነበር ግራሚዋን ዋጋ አልሰጠችውም ። ሌላው ቀርቶ በእንግዳ ሚሽት ላይ የነበራት ቅሬታ ለጊዜው ከሐሳብዋ ጠፍቶ ነበር ። አዲስ ሁናቴዋን የተገነዘቡት የዱሮ ጓደኞቿም ፣ በመገረም እንደ መጠቃቀስ እያሉ ወሥር ጊዜ እርስ በርሳቸው ተያይተዋል . . .

ማምሻውን ቴዎድሮስ ፣ ገብርዬን ሊጠይቁ መጡ ። ተከታትሎ ፣ መሐድ ያቃታቸው ሽሀር ላሞች ፣ እየተንዱ ገቡ ።

ገብርዬ ተነሥቶ ለመቆም ሲሞክር ፣ “ ኧረ ኤዲያ ! ምን እያልክ ነው ? በርፈህ ተቀመጥ ይልቅስ ! ” አሉት በጓደኛ ግሣጼ ። “ ለመሆኑ እንዴት ነህ አሁን ? ”

“ ደኅና ነኝ ፣ በጣም ደኅና ነኝ አባ ታጠቅ ። ”

መምጣታቸውን ቀደም ብሎ መልክተኛ ሲነግር ፣ ብዙዉ ራሱ በውቆ ፣ ሌላዉም ፣ ወይዘሮ ደብሬ ፣ “ ደክመህ እኮ ፈታውራሪ ፣ ሕመም ተኛ ቁስለኛ ነህ ፣ ግባና ጋደም በል ” ሲሉ ባለቤት ከሌለበት ቤት እንግዳ እይቀመጥምና ነገሩ እየገባው ተነሥቶ ስለ ሔደ ፣ ቤቱ ሞር ባይልም ቀለል ብሎ ነበር ። ቴዎድሮስም የመጡት ጥቂት ራሳቸውን ነው ።

“ ይቆይል እንጂ እሱማ መዳኑ የት ይቀራል ! ነገ ወጌሻው ጨርቁን ይፍታና አጥቦ አዲስ መድኃኒት እንዲያደርግልህ ። ቆይቷል ። እንቺ ደሞ ” አሉ ቴዎድሮስ ወደ ታንጉት እያመለከቱ ፣ “ ተሥጋው ጋር ሽኮ ናውንም ቅልጥሙንም እየቀቀልሽ ጠግኝው ። ማብሰሉ ታቃተሽማ ለጉድ ነው ። ወዮ ነግሬሻለሁ ! ”

“ እሱ እሺ ብሎ ተበላ መሥራቱ መች ይገዳል አባ ታጠቅ ? ” አለች ታንጉት ፣ ውሸትነቱና ቀልድነቱ በሚያሳውቅ ማሳጣት ።

“ እኔ ምን ችገረኝ ። ተቤት ተወዝፎ ይናራታላ ! ” አሉ ቴዎድሮስ በተመሳሳይ ዛቻ ። “ ታውኑ ዘመቻ የሚቀረውም ቦት ዋይ ቢሆን ነው ! ”

“ የምን ዘመቻ አባ ታጠቅ ! ” ገብርዬ እንደ መሬናጠር ታጣው ።

“ ዘመቻችን ተጀመረ እንጂ መቸ አለቀ ብለህ ገብርዬ ? አውን ግና ያች ’ ፣ ፀርቂት ፀሱን ይዛ እንደገና ሽፍታለች ’ የሚልወሬ መጣታል ። ያንን ያህል ምላ ተገዝታ ፣ በሱዋው አልፈን በሸዋ ዙረን እግራችን ሳያገባ ከዎንጊዘው ? ” ቴዎድሮስ አንድ ነገር ትዝ ያላቸው ይመስል ፈገግ አሉ ። ወርቂት በጦር የሚያሸንፋትን በሌላ እንደምትገራው የሚነገር ላት ቆንጆ ነበረች ። “እውነስ አይግረኝ አልዎርዎ ። ያገኘዋል ተጂ ። ” ቅጣቱ የታያቸው ይመስል ኩስተር አሉ ።

“ መቸ ልትሔድ ነው ? እኔም ኮ እንደ ምንም መሔድ እችላለሁ ” አለ ገብርዬ እግሩን እያሳየ ።

“ እንኳን አንተ ቁስለኛው ጪነኛው ሠራዊትም ጥቂት ጊዜ ወረፍ ብሎ ነው የሚነሣው ። እስቲ መጀመሪያ ድነህ ቆየኝ ። ለሌላው ትደርሰዐ ታለህ ” ብለው ቴዎድሮስ ግራና ቀኝ በቤት ያሉትን ሰዎች እንደ መገም ገም ካደረጉ በኋላ ፣ “ ለመሆኑ እንዴት እንደ ቆሰለ ነግሮሻል ? ” አሏት ታንጉትን ።

“ እረቴ ! ”

“ አፍሮ ነዋ ! ” አሉ ከገብርዬ ጋር ቁልጭልጮ የሚጫወቱ መስ ለው እየሣቁ ። “ ጀግናው ገብርዬ ፣ ጅሌው ሆዬ ፣ በነፍጥ ፣ በጦር ፣ በጉ ራዴ የመጣውን ፊት ለፊት ፣ ግንባር ለግንባር እየተጋፈጠ መሬት አይ በቃኝ ሲል ብልጥ መንዜ ሆዬ ከቁጥቋጦ ሥር ተሸጉጦ መርግ መልቀቅ ። ቅልጥም አደረገዋ ! እንዲያውም ዝንጀሮ ሳይሆን ይቀራል መርጉን የለ ቀቀው ? አገሩ ሁሉ ዝንጀሮ ብቻ ነው ! ” አሉና ቴዎድሮስ እንደ ወንድም በፍቅር እየተመለከቱት ከት ብለው ሲሥቁ ሌላውም ለቀቀው ። ታንጉት ከልብ አንፈራፈራት ። ወይዘሮ ደብሬም አፋቸውን በእጃቸው ከድነው በቆሙበት እንደ ቅጠል ተንዘፈዘፉ ።

“ ሲሮጥ አይቸዋለኋ ! ሰው መሆን አለበት ! ” አለ ገብርዬ አብሮ እየተንከተከተ ።

“ አዬ ገብርዬ ! ሰዉ ፣ በጨርቅ ፈንታ ፣ ያን ባናውንና ደበሎውን ለብሶ ፣ በሩቁ ከዝንጀሮ አይለይ ! ዝንጀሮምኮ ይሮጣል ። እንዲያውም ተሰው አብልጦ ! ” ሲሉ ቴዎድሮስ ፣ ሣቁ እንደገና ቀለጠ ።

“ አንጓች ! ” አሉ ቴዎድሮስ ለመሔድ ሲነሡ ። ቀረብ አለች ። “ ነ ብቅ በደና ተዋቡን ጠየቂያት እንጂ ! ” አሏት ። አነጋገራቸው ማሳሰ ወይም መለመን ይምሰል እንጂ ፣ ውስጠ ትእዛዝ ጭምር መሆኑን ታወ ቃለች ። ቴዎድሮስ ፣ ‘ እባክህ ፣ እባክሽ ’ ያሉትም ጉዳይ መፈጸም አለበት፣

ራሳቸው ያሰቡትን ከመፈጸም እንደማያመልጡ ሁሉ ፣ ከሌላውም እንደዚሁ ይጠብቃሉ ።

“ እሺ አባ ታጠቅ ! ” ቦትል መለሰች ፣ ለምን ይሆን የሚል ፊደል ግን እየመጣባት ። ምክንያቱም ፣ ትናንትናውኑ ገብርዬን ከአልጋ ላይ እንዳለረፈች ፣ ወዲያውኑ ወደ ቤተ መንግሥት ሔዳ ከሁሉም ጋር ተገናኝታ ተመልሳለች ። ስለዘህም ተዋበችን የመጠየቅ ብቻ ሊሆን አይችልም ። አንዳንድ ጊዜ ግን ፣ ቴዎድሮስም ቢሆኑ ሊያያዋት ሲፈልጉ ያለ ምክንያት የሚያስጠሩዋት ጊዜ አለ ። በአንዳች ወይነት ሐሳብ ፈት ፈታን አይተው ፣ ደኅንነቷን ያግመው ይጋግመው ጠያቂዉ ያሰናብታታል ። ከጠርባቸው ጋር ያላት ግንኙነት ይበልጥ የሚያውቅታትና ግራ የሚያጋባት በእንደዚህ ያለ ጊዜ ነው ። እንደሚወዱዋት ፣ እንደሚያስቡላት በጣም ይሰማታል ። “ነገ ሲደርስ ለማየው አውን ምን አሳሰበኝ ’ ስትል ለጊዜው ከአእምሮዋ ሩቀችው ።

ታንጉት ፡ ቴዎድሮስን እስከ ግቢው በር ሸኝታ ስትመለስ ፣ ግቋን ለቀቀችው ። ወይዘሮ ደብሬ ቴዎድሮስን እጅ ነሥተው ከተሰናበቱበት እንደ ቆሙ ነበሩ ።

“ እረ ባባጃሌው ! ምነካሽ ልጄ ! ” አሉ ፡ እንደ ቀድሞው የቀልድና የወዛ መልክ ሳይታይባቸው እንደ ተኩሳተሩ ።

“ እርስዎ ነዎታ እማማ ደብሬ ! ” ታንጉት ግቋን መግታት አቃታት ።

“ እረ ባባጃሌው ! ምን ሆንኩ እኔ ? ”

“ ዛሬ ምነው እንደዚህ ዝግት አደረገዎት ። አይተህልኛል ገብርዬ ? ተዚያ ተበሩ ጥግ ተደግፈው ነው እኮ የዋሉት ። እጃቸውን አጣፍተው ። ”

“ ዛዲያ ምንላርግ ? ”

“ አይናገሩም ? አያንቀሳቅሱም ? ”

“ እረ ባባጃሌው ! ልቅለብለብ ነው የምትይኝ ? ”

“ እንደ ወትሮው ማለቴ ነው ! ”

“ አይ ! ቦታ ቦታ አለው ። ተማንም ጋር አፈን የተካፈትኩ እንደሆነ ፣ ተትልቅ ሰው ጋር እንደዚያ መሆን አለብኝ ? ቴዎድሮስ ትልቅ ሐሳብ ያለው ትልቅ ሰዉ ነው ። አክብሮት አደርግለታለሁ ። አይገባም ፈታ ውራሪ ? ” ሲሉ ገብርዬን ጠየቁት ።

በክፍተኛ አድናቆት እየተመለከታቸው ራሱን ብቻ በአወንታ እወ ዛወዘ ። እንደ ታንጉት እየማረኩት ሔደዋል ።

“ በሉ እናንተም ዕረፉ እንጂ ! እረ ባባጃሌው ! ወይስ አልተንፋፈ ቃችውም ልበል ? ” አሉ ወይዘሮ ደብሬ ተሰናብተዋቸው ሲወጡ ፣ ፊታ ችው በተለመደ ፈገግታቸው ፈክቶ ። የሁለቱ ማቅ ተከተላቸው ።

ታንጉት ፣ ከተዋበች ጋር ስለ ሸዋው ዘመቻ ፣ ስለ ጉንደሩ ኑሮ ፣ በሁለቱም በኩል ያጋጠማቸውን ነገር ፣ ሴላ ሌላውንም በቀላሉ እንደ ዋሣ ሰ ጨዋወቱ ቆይተው ፣ ያሁኑ ቴዎድሮስ የዚያን ጊዘዉ ካሣ ፣ ከተዋበች ጋር ሲያገናኝዋት ‘ ተኔ ቀጥላ እናትሽም ፣ እኅትሽም ናት ፤ እታለም በያት ’ ካሏት ጀምሮ በምትጠሪት ፣ “ እታለም ልሒድ እንግዲህ ” ብላ ስትነሣ ተዋበች ፣ “ ታጠቅም ሊያይሽ ይፈልጋል መሰለኝ ፤ ግን ተልፍኝ አይደለም ። ታዲሱ ቤት ነው ” አሏት ።

ቴዎድሮስ ፣ በጉንደር ቤተ መንግሥት ውስጥ ካመጡት አዲስ ነገር ለራሳቸው የተለየ የሥራ ክፍል መመደባቸው ነበር ።

ከርሳቸው በፊት የነበሩት መሳፍንት ፣ ከእነዚያም በፊት የነበሩት ነገሥታት ፣ በአደባባይ ችሎት ይቀመጣሉ ። በሰፊ አዳራሽ ይሾማሉ ፣ ይሽራሉ ፤ ግብር ያበላሉ ፤ ጥብቅ ምሥጢር የሌለበት ጉዳይ በዚሁ አዳራሽ ይመክራሉ ። ያከናውናሉ ። ራሳቸውን ወይም የቅርብ ታማኞች ባለሟልቻቸውን ብቻ የሚመለከተው ምሥጢር ቀመስ ውሳኔና ፣ ወይም በዘመነ መሳፍንት ሳያቋርጥ እንደ ተደረገው ሁሉ ፣ ሚራውና ቢላውም ተግባር በእልፍኝ ውስጥ ይካሔዳል ። ቀላጤ ወይም ደብዳቤ የሚያስፈልገው ጉዳይ ሲሆን ፣ ጸሐፈ ትእዛዙ በቃል የተቀበለውን ትእዛዝ በራሱ ክፍል ወይም ጽሕፈት ቤት ውስጥ አዘጋጅቶ ያፈጽማል ፤ ያስፈጽማል ፤ ቴዎድሮስ ግን ከዚህ በተጨማሪ የራሳቸው የሥራ ክፍል እንዲደራጅ አደረጉ ።

ሐሳቡን ያነጉት በኋላ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ከተባለው ከጀን ቤል ነበር ። ጀን ቤል ፣ የቴዎድሮስን ትልቅ ሐሳብ ፣ የቴዎድሮስን ትልቅ ዓላማ ከተረዱት ጥቂት ሰዎች አንዱ ነው ። እንዲያውም ፣ ከሠለጠነው አውሮፓ ከመምጣቱ ጋር ፣ በቅን አስተሳሰቡ ከሁሉም የበለጠ ተረድቶላቸዋል ። ከደጃች ውቤ ዘንድ ረዘም ላለ ጊዜ የጌታ አድሮ ፣ ደጃች ውቤ ሲሸነፉ ግርከው ካሰሩት ከቴዎድሮስ ጋር በመተሳሰብ ፍቅር ያቀራረበውም ይኸው ነበር ።

ስለ ሥልጣኔ ፣ ስለ ዕውቀት ፣ ስለ አስተዳደር ፣ በተለይም እንድ ሕዝብን ሀብታምና ኃያል ስለሚያደርገው የሙያ ሥራ በሰፊው ሲያስረዳቸው በመመሰጥ እንደሚከታተሉት ሁሉ ፣ በበኩሉ ሥራቸው እንዲቃና ብዙ መንገድ ሲፈልግ ፣ የሠለጠኑ አገሮች መረዎች ከተለመደው እንደ አዳራሽ ፣ እንደ ችሎት ፣ ከመሳሰለው ይፋ የሥርዓት ባሕል መድረክ ሌላ ፣ የዕለት ሥራቸውን በተሞና የሚያከናውኑበት ልዩ ክፍል እንዳላቸው አንድ ቀን ነገራቸው ። ቴዎድሮስ የአዳራሹ ጋጋታ ፣ እርሳቸው እንደሚሉት የቅምጥል ጫጉላ የመሰለው እልፍኝ ሽብርቃት አስጠልቷቸው ነበርና ሐሳቡ ወዲያው ማረካቸው ። ሊቀ መኳስ ዮሐንስ አስተያየት እየሰጠ ፣ ከሚሲዮኖችና በጊዘው ከነበሩት የውጭ አገር ሰዎች ችሎታ ያላቸው ፣ የሚያስፈልገውን ዕቃ ሥራ አጣደ

ፈውት በእጭር ጊዜ ውስጥ ተሰናዳ ። ከዚህ በኋላ ቴዎድሮስ ፣ ከችሎት ሲነሡ ወይም በእልፍኝ የሚቀበሉት እንግዳ ከሌላቸው ፣ የሥራ ጊዜ ያቸውን የሚያሳልፉት ወይም ብቻቸውን ፣ ወይ ፣ ከሊቀ መኳስ ዮሐንስ ጋር ዐልፎ ዐልፎም ከቅርብ ባለሟሎቻቸው ጋር በዚህ ክፍል ነበር ። ገብርዬ ስለዚህ የቴዎድሮስ አዲስ ጓዳ ብዙ ጊዜ ነግሮዋታል ። ራስዋ ግን ካውን ቀደም አላየችውም ነበር ።

በመቃብር ሥፍራ እንደማይሠረግ ሁሉ ፣ በሠርግ ዳስ ውስጥ እን ደማይለቀስ ሁሉ ፣ ከለመደችው ከአዳራሹና ከእልፍኝ ውጭ ለመጀመሪያ ጊዜ ቴዎድሮስ በዚህ አዲስ ክፍል ለምን እንደ ጠበቃት ታንጉት ግራ ገብቷት ፣ ‘ ለጥሩ ነው ፣ ለመጥፎ ? ’ እያለ ልብዋ በፈራ ተባ ጸንኪራ መታ ባት ። ሳንቃውን ፊርቀቅ ስታደርግ “ ማነው ? ” አሉና ቀና ብለው በመ መልከት ፣ “ አንጓች አንቺ ነሽ ? ግቢ ” አሏት ።

ስትገባ የባስ ተደናገራት ። ያሠሩት አዲስ ክፍል ከእልፍኝ ያማረ የተንቆጠቆጠ መሆን አለበት ስትል በሐሳብዋ ገምታ ነበር ። ዘወርወር ብላ የተመለከተችው ግን ፣ ቴዎድሮስ ከኋላው ቁጢጥ ብለው የተቀመጡበት አንድ ትልቅ ሰደቃ ፣ የጠፍርና የዕንጨት ወንበር ፣ በየሥፍራው ሽጉጥ ፣ ጠመንጃ ፣ ጉራዴ ፣ መጽሐፍ የሚመስሉ ነገሮች ፣ ሌሎችም የማታውቃቸው ዕቃዎች ናቸው ። ከእንዱ ግድግዳ ላይም የሸረሪት ድር የሚመስል መሥመር የተሞጫጨረበት ብራና ነገር ተለጥፏል ። ታንጉት በጊዘው አላወቀችውም እንጂ ቆንስል ፕላውዴን የሰጣቸው የጊዘው የአፍሪካ ካርታ ነበር ።

“ ቁጭ በይ እንጓች ! ” አሏት ። ተቀምጣም ወይንዋ በመገረም ዙሪያውን ሲንከራተት አደተው ፣ “ ምነው እንጓች ? ” ሲሉ ጠየቋት ። ስሚቷ ግን ገብቷቸዋል ።

ወዲያው ነገራቸውን ለወጥ አደረጉና ፣ “ ለመሆኑ እንቺ ደኅና ነሽ ፣ ጤንነትሽ ? ” ሲሉ ጠየቋት ።

“ በጣም ደኅና ነኝ ። ”

“ ሐሳብም የለብሽም ? ”

“ ምን ሐሳብ አለብኝ አባ ታጠቅ ? ”

“ ምናውቃለሁ ብለሽኝ ? የሰው ሐሳብ ብዙ ነው ። እኔ እንደሆነ እንግዲህ ፣ ባራቱ ማዕዘን ሳስብ ብዙ አላጫውትሽ ፣ አላዋይሽ ! እንዲያው ድንገት ብዬ ነዋ ! ” ራሳቸው ጥቂት ያሰቡ መስሉና ፣ “ ገብርዬም አያስከፋሽም ? ” ሲሉ ጠየቋት ።

“ እሪ ጭራሽ ! የእግዚአብሔሩን ሰው ! ” አለች ታንጉት ደመቅ ባለ አነጋገር ፣ ከገብርዬ ጋር የትናንቱ ሁናቴያቸው ታውሷት ።

''እንደማያስከፋሽስ ዐውቃለሁ። እንዲያው ለንገሩ ብዬ ነው እንጂ። እንደምወድሽ ታውቂያለሽ ፤ እም ባልወልድሽም ልጂ ነሽ።''

ታንጉት የምትመልሰው ጠፍቷት ዝም አለች።

''እም ፤ ታንጊና ተተዋበች የሚቀርበኝ የለም።''

'ለምን ነገሩን ለደተህ ፣ ግልጽ እርገህ አትናገርም ፤' የሚል ሐሳብ ታንጉት ድንገት መጣባትና ፣ የአፍቅሮት ፈታቸውን ስታይ ወዲያው ከአእምሮዋ ተሰረዘ።

''እና ጉንደር ፣ ሲያወራብኝ ፣ ስያሜርትብኝ ፣ ሲሸርብብኝ ፣ ክር ሜል ግለትን አሰግለሁ። ለምን አልነገርሽኝም አገኝች ፤ ወደስ አልስ ግሽም ፤'' ትዝብትም ፣ ግማዴም ሳያሆን የመግጠን ዐይነት ነበር።

''ምንን ልንገርህ አባ ታጠት ፤ ወሬ ብቻ እኮ ነው ፤'' አለች ታንጉት አነጋገርዋ የሞገቱት ጥሪ ነበረበት።

''ተወሬ ፣ ተሜራ እኮ ነው ሁሉም ነገር የሚጀምረው። እታው ቂም ፤' ዘመቻ ተፈታው ወሬ የፈታው' ሲባል አልሰማሽም ፤ ተዚያ ደሞ ሌላው ይመጣል። ያለፈው ዐዕሏል። እሁን ለወደፊቱ ልስምንሽ እሺ ትደኛለሽ ፤''

''እህ ፤ ላንተ እምቢ የምልህ ነገር አለ ፤'' ታንጉት ሳይታወቃት በመጨነቅ ተወራጨች። የተናገረችው ከልብዋ ነበር። ቴዎድሮስ በናቅሩም ፣ በፈታዱም ፣ በቁጣውም ስቦ የሚይዝ አንዳች የተፈጥሮ ኃይል እንዳለው አብራ በኖረችበት ዘመን ሁሉ ተሰምቷታል። ያሆንን ኃይልም ኑሯዋለች። ገና ልጅ ሆና ክፉኛ በቀጣት ጊዜ ሰንኳ እንዳቆላመጣትና በሰመታ እንዳባበላት ያህል ጥምጥም ትልበት ነበር ፣ እንደ ዛሬው ሌላው ሐሳብ ሳያመጣባት።

''እም ዐውቃለሁ። እንቺም ታወቅሽኝ እምቢ እንደማትይኝ ዐውቃለሁ ፣ እሺ እንግዳያው ዐደንሽንም ፣ ጆሮሽንም ነቃ አድርጎሽ ፣ የምታደውን፣ የምትሰሚውን እንዳያው አርቲ ቡርቲውን ሳያሆን፣ እህ ፤ የምትደውን ባውቀው መልካም ነው። አሁን እኛ ዘመቻ ሒደን ሲወራ ፣ ስዶለት እንደ ከረመው ዐደነት።''

ታንጉት የነገሩ ዳርዳርታ በመጠኑ ገባት። ነገር ግን ያልገመተችው አዲስ ነገር ስለሆነባት በትክክል ለማረጋገጥ ዝም ብላ ጠበቀች።

''ቀፈፈሽ ፤ እስጠላሽ እያደለ እገባች ፤'' በቅሬታ መኩሳተር ትክ ብለው ተመለከቷት። ''ነገሩ መሰለል ነው። እም በመሳፍንቱ ዘመን እንዲ መስፍን በሌላው ላይ ሰ ያሜርና ሲዶት ፣ እገሌ የእገሌ ሰላይ ነው ሲባል ከማስጠላት ዐልፎ ፣ ምን ልበልሽ ተሰውነት ወጥቶ ተውሽ ፣ ተልክ ስክስ ውሻ መባስ ነው። ግን ደሞ እንድ ሰው እዝመራውንም ይሰል

ላል ፣ ደኅና እምርስት እንደሆነ። ከብቱንም ይሰልላል ፣ አውሬ ወደም ሴባ እንዳይነተትበት። እርሱ ክፉ ሳያስብ በክፉ የሚንጣበትን ጠላት ሁናቴም ይሰልላል። ዛሲያ ይሽ ሁላ ምን መጥፎ ነገር አለበት ፤ ለበጎ ነዋ ሐሳቡ። ዛሲያ እገራችን እዝመራችን እያደለችም ፤ ናት እንጂ ፤ አብትላ ፣ አፍርታ የምትግበን። ዛሲያ ፣ ጠላት ፣ አውሬ ጠላት አድክሟት ናረ። አውን ደሞ እኛ እንደነና እንደ ጥንቷ ሀብታም ፣ ጠንካራ እንድትሆን ስንፈልግ ፣ ቱርክም ፣ ፈረንጅም ሊያደክሟት ፣ እድክመውም ጨርሰው ሊወስድዋት ውስጥ ውስጡን እየሰለሉ የሚሥሩትን ይሠራሉ። ይሽ ተንኰል ያልገባው የእኛው ሰውም ተነሱ ጋር አብሮ ለማፍረስ ይቶ ፍሪታል። ሌላው ደግሞ ፣ ይሽ የዘመነ መሳፍንት ሠምላቃ ኑሮውን እንደ ትልቅ ነገር ቆጥሮት ያ ለምን ተነካብኝ ብሎ በዚህም በዚያም ይዶል ታል። ዛሲያ ፣ ይህ እንዳይደርስ ፣ ተዚህም ዐልፎ በጠላቶቿ ላይ መሰለል ምን ክፉት አለበት ፤ በጎ ነገር ነው እንጂ ፤ የጽድቅ ሥራ ነው እንጂ ፤ ተሆነልኝ ፣ እኔ ላገሬ ታገር አገር ፣ ታጥናፍ አጥናፍ እየተንከራተትኩ እስልልላት ነበር። ለኔዉ ለራሴማ ምን ፈልጌ ፤ የምበላው አንድ እንጀራ ፣ የምለብሰው አንድ ሠርት ፤ ለእስ ላንቺስ ፣ ለተዋበችስ ባባታችን አገር አርሺ ፣ አድኜ ሳንጉርስ ፣ ላንበላ ፣ ላንለብስ ግደር ያቅተናል ፤ እንዳያውም ሐሳብ የለለበት የሰላም እንቅልፍ እያተኛን ፤ መቀለብ ፣ በምችት መድለብ በያምረኝ ናርስ የእግቺ የራስ አሊ አዳራሽ ተከናቶልኝ አልነበረም ፤ ያገርሽ ፣ ያገሬ ዕዳ ሆናብኝ ነው እንጂ ፤ ሰው ላገሩ . . .''

ታንጉት ፣ የቴዎድሮስ የግላግ ሽክም ተጫናት። ወደዘር ይብሬ እያዩሩ ባሳይዋት የጥንታዊት የኢትዮጵያ ፍርስራሽ ሕልማቸው እንደነገ ተደቀንባት። ''እሺ አባ ታጠት ፤ ምን እርጎ ነው የምትሰኝ ፤ እሺ አልኩህ ንግረኝ ፤'' አለች የሚታያት ሕልማቸውን መሸነም ያታታት ያመስል ንግግራቸውን እያቋረጠቻቸው።

ቴዎድሮስ፣ ከአስሠናቲ የሕልም ግለም ተንዘው ድንገት እንደተመለሱ ያህል በሰፈው ተነፈሱ። ''እንዳዩኩሽ ግላግዩን ለማሠናገፍ ብዙ ሰዎች እየዶለቱ መሆናቸውን ሰምቻለሁ። በተለያም ካህን ነን ባይ ወምጣሚዎች። ለመሆኑ ብዙ ሰው ዐውቀሻል ጉንደር ፤'' ሰሉ በመካከሉ ጠየቋት።

''ኧረ እቲ ፤ አንድ ጥሩ ወዳጅ ብቻ አፍርቻለሁ። ወደዘር ይብሬ የሚባሉ።'' ቴዎድሮስ ጥቂት እንደ ማሰብ አሉና ራሳቸውን ነቀነቁ። ''እላውቃትም።''

''ኧረ ድፍን ጉንደር ያውቃቸዋል።''

''እኧ፣'' አሉ ቴዎድሮስ በማስታወስ ነቃ ብለው። ''ይች የይጃች ተድላ የነበረች ው ፤''

''ኧረ በዕድሜ ጠና ያሉ ትልቅ ሴትዮ ናቸው ፤'' አለች ታንጉት 'እንች' በመባላቸው የተዋረዱባት ይመስል።

“ ጉንደር ሳለሁ ሲወራላት እሰማ ነበር እንጂ እኔ የት ወሎቃት ብለሽ ! ግን ምን ኢጋጠማችሁ ልጂ ? ” አሉ ቴዎድሮስ እንደ ዋዛ ።

ታንጉት ግንነንጉ እንደ መርፌ ጠቅ አደረጋት። ‘ እሱም እንደ ሌሎቹ በነገር መንካቱ ነው ? ’ አለች በሆድዋ ። የቴዎድሮስ አስተያየት ግን እንዳችም የእሽሙር ምልክት አልነበረበትም ።

“ እንዱ ዋና የዱለታው ጉንጓኝ እኒያ ግብጻዊ የቱርክ አሽከር ናቸው ይባላል ” አሉ ቴዎድሮስ ወደ ጉዳያቸው ተመልሰው ። ታንጉት በጥየቃ ዐይነት ትኩር ብላ ተመለከተቻቸው ። “ አዎ ! አቡን ተብየው ! ” ሲሉ መለሱላት ። “ ተዋውቀሻቸዋል ? ”

“ እንድ ጊዜ ቤታችን መጥተዋል ። ቤተ ክስያንም ዐልፎ ዐልፎ መስቀል ያሳልሙኛል ። ”

“ እስቲ እሳቸውንም ቀረብ በያቸው ። እና ፣ ለሁሉም የሚሆነውን እያደርማመጥሽ ንግሪኝ ። ”

ጉዳያቸው ያለቀ መስሏት ታንጉት ለመሔድ ስትነሣ ፣ “ ኧኸ ! ልረሳው ነበር ” አሉ ቴዎድሮስ ከተቀመጡበት እየተነሡ ። ከዚያም ከአንድ ጥግ ዝተት የመሰለ ነገር አመጡና ሰጧት ። “ ተሸዋ ያመጣሁልሽ ነው ፣ መንዙች የሚለብሱት ። ባና ይሉታል ። ገብርዬ ብቻሽን ጥሉሽ በዘመቻ ሲንከራተት ያሞቅሻል ! ” በቀልድ ሣቅ ፈገግ አሉ ።

ታንጉት ፣ በተሰጣት አዲስ ተግባር ብዙ ሳትጨነቅ ፣ ከአቡኑ ጋርእንዴት እንደምትቀራረብ እያሰላሰለች ወደ ቤቷ ተመለሰች ።

— 5 —

ጋረድ ፣ ከጉንደር እደባባይ ተሰውሮ ሰንብቶ ፣ ገብርዬን ሊጠይቀው የመጣው ቴዎድሮስ እንደገና ወደ ወሎ ዘመቻ ከሔዱ በኋላ ነበር።አሁንም የመጣው ከደብተራ አክሊሉ ጋር ነው ።

“ ይሀንን ያህል ምን አስቸገረህ ልጅ ጋረድ ? ” አለው ገብርዬ ከም ስጋናው ጋር በመገረም ። በእርግጥም በጣም ገርሞት ነበር ። በደርቡ በር በኩል እንዳያቸው ፣ ጋረድ አንዲት ምን የመሰለች ሽሀር ፣ አንድ ዐሥር የሚሆኑ በጎች አስከትሏል ። “ ግቢውስ የት ይቢታል ! ” አለ በቀልድ መልክ ።

“እህ ! እንደ ካሣም ባልሆን ይኸ ይብዛብኝ ? ” ሲል ጋረድ እንደ ዋዛ መለሰ ። የማወዳደሩ አሽሙር ገብርዬ ቢገባውም ሊጠይቅ የመጣን ሰው ማስከፋት ነውር ስለ መሰለው ቅሬታውን አላሳየም ። ወዲያው ሌላ ሌላው ጭውውት ቀጠለና ረሳው ።

ታንጉት ፣ በበኩልዋ በጋረድ ላይ ከፊተኛው የተለየ ሁናቴ ያየችበት መስላት ። ጉራው ተቀንሷል ። የንቀት አመለካከቱ መለስ ብሏል ። ከመ

ጠሙም ተቆጥቧል ። ‘ ያን ለት ሞቅ ስላለው ነው ወይስ ዐይኔ ነበር? ’ አለች በሆድዋ ።

ከዚህ ቀን ጀምሮ አዘውትረው መምጣት ያዙ ። ሲመጡም ፣ ሲሔዱ ሁለቱ ተለያይተው አያውቁም ። ታንጉትን የሚያስገርማት ይህ ነበር ። ‘ምን ዐይነት ፍቅር ነው ? ’ ትላለች ለራስዋ ። እንዳንድ ጊዜም ከእርስዋና ከወይዘሮ ደብሬ ወዳጅነት ጋር ታመሳስለዋለች ።

ገብርዬ መጀመሪያ ላይ ፣ ‘ ተመቸ ወዲህ ነው ? ’ የሚል ጥርጣሬ ቢያድርበትም እያደር ጉብኝታቸውን እየለመደው ሔደ ። የቅርብ ጓደኞቹ ሁሉ ዘምተው ፣ ሌላው ጠያቂም እየቀዘቀዘ ሔዶ ስለ ነበር ፣ እየመጡ ማጫወታቸውን አልጠላውም ። እንደ ማንኛውም መቀራረብ ፣ ገበጣ እየተጫወቱ፣ ከእደጋና ከዘመቻ እስከ ዋዛ ፈዛዛ ጨዋታ ብዙ ጊዜ አብረው ሲያሳልፉ ፣ መተራረብ ፣ መቀላለድና ከሚሸት የሚደበቅ የፍቅር ምሥጢር መለዋወጥ ጀመሩ ። ይበልጥ እየተላመዱ ሔዱ ።

ነገሩ የከነከናቸው ወይዘሮ ደብሬ ነበሩ ። “ እኔ አላማረኝም ” አሏት አንድ ቀን ታንጉትን ለብቻ ። ጋረድና አክሊሉ ጪት ገደማ የመጡ ሲጫወቱ ውለው መሔዳቸው ነበር ።

“ ምኑ ? ” ስትል ጠየቀቻቸው ።

“እግር እበዙብኝ እነዚህ ሰዎች ። ኤዲያ ፣ ዝምድናም ተሁነኛ ሰው ጋር ሲሆን ነው” አሉ ወይዘሮ ደብሬ እነጋገራቸውን ፍርጥም አድርገው።

“ ወይ እማማ ደብሬ ! ስለ ሰው ክፉ ሲናገሩ ዛሬ ገና ሰማሁዎት ! ! ”

“ እኔ ምን ክፉ እናገረኝ ። እንዲያው ውቃቢዬም እንደሆነ እያዘወተሩ መምጣታቸው ቢያስገርመኝ ነው እንጂ ! ”

“ ጋረድም እንደሆነ የአባ ታጠቅ ወንድም ማለት ነው። ዛዲያ ተወንድሙ የጦር አለቃ ጋር ወዳጅነት ቢፈልግ ምን አለበት ? ”

“ ያስገረመኝስ እሱ አይደለ ? ደግሞ ጋረድ ፣ የደጃች ክንፉ ልጅ ቢሆን በአባቱ አልወጣ ! ቴዎድሮስንም እንደ ወንድሙ አያየው ! ”

“እረ እንደዚህ አያስቡ ! ” አለች ታንጉት ነገራቸውን በማጣጣል ።

“ እንኳን ተመሰለሽማ ” አሉና ወይዘሮ ደብሬም ነገሩን ችላ እደረጉት ። ከእርሳቸው ሌላ ወዳጅ በማፍራታቸው ምቀኝነት እንዳይመስልባቸው ።

ታንጉት ፣ በበኩልዋ የእነልጅ ጋረድ ዝምድና ከልብ ባያስጨንቃትም ጉብኝታቸውን የምትፈልግበት ሌላ ምክንያት ነበራት ።

ገብርዬ ከወትሮውም ልጅ በጣም ይወዳል ። ከመንገድ ላይ ልጅ ካጋጠመው ይወቀውም አይወቀውም ዝም ብሎት አያልፍም ። እንደ ቤተ ክርስቲያን ጉንበስ ብሎ ግንባሩን ይስመዋል ። ወይም ደግሞ ብድግ

አድርጎ በማቀፍ ፣ ‘ ስምህ ማነው ? የማን ልጅ ነህ ? ትበዝ ነህ ፈሪ ? ’ እያለ ላንዳፍታ ያጫውተዋል ። ዘመቻ ወይም እደን ሔዶ ፣ ሥራዬን ብሎ ለመንደር ልጆች የዱር ፍሬ በጨርቅ ቋጥሮ የሚመጣዉ ብዙ ጊዜ ነበር ። ልጆችም የሚወዱት የዚያኑ ያህል ነው ። ታንጉት እንደምታውቀው ፣ ጉንደር እስከ መጡ ድረስ በየቆዩበት የሠፈር ፣ ልጆች ከወላጆቻቸው ቀጥሎ የሚቀርቡትና የሚያቀርባቸው ገብርዬ ነበር ። እንደ ዕድል ሆኖ ፣ እርሷም ፣ እንደ ተዋበች እስከ አሁን ልጅ አልወለደችም ። ልጅ የሚያፈቅሩትና የሚያፈቅራቸው ገብርዬና ቴዎድሮስም የሚያጫውቱት የራሳቸው ልጅ አላገኙም ። እርሷና ገብርዬ ከተጋቡ ሰባት ዓመት ወልዷቸዋል ።

ምናልባት ጊዜው እየገፋ ሲሔድ ፣ ያለመውለድዋ ሐሳብ አመለካከቷን አጉልቶባት ሊሆን ይችላል ። ገብርዬ ከሸዋ ዘመቻ ከተመለሰ ወዲህ ደግሞ ስለ ልጅ ያለው ስሜት ከበፊቱ እጅግ የበረታ እየሆነ ታያት ፣ ተሰማት ፣ የሚያንጋግረው ወንድ እንግዳ ከሌለ ድንክ አልጋውን ከደርቡበር ደረጃ ላይ እንዲያወጡለት ያስደርግና በአቅራቢያው የሚዘዋወሩትን ወይም የሚጫወቱትን ልጆች በተመለመ ያስተውላል ። ከእንቅስቃሴ ያቸው ጋር ወይኑ ይንከራተታል ። አመለካከቱ የፍቅር ብቻ ሳይሆን የስስት ዐይነት ጭምር ነው ። የሐሳብ እጁን ዘርግቶ የሚያቅፋቸው ፣ የሚደባብሳቸው ይመስላል ። በፊቱ ላይም አንዳች ትካዜ ጥላ ይደረብበታል ። ታንጉት ፍላጐቱ እየገባት ፣ ስሜቱ እየተሰማት ፣ ትሠቀታለች ። ትጨነቃለች ። እያደርም ሰቀቀን እየሆነባት ሔደ ። እነጋሪድ እየመጡ ገብርዬን ማጫወታቸውን የወደደችውም ፣ የውስጥ ሐሳቡንም ባያሆን ፣ ወይኑ ከልጆች ጋር መንከራተቱን በመጠኑ ይቀንስለታል በማለት ነበር ። በዚያውም የእርሷንም ሠቀቀን ።

በኋላም ፣ ‘እሾህን በእሾህ ’ እንዲሉ ቴዎድሮስ ለሰጣት ሥራ ፣ እክሊሉ ከአቡነ ሰላማ ጋር የበለጠ አቀራርቧት ፣ እህል ውሃ እያያዘች መንበራቸው ዘንድ ብዙ ጊዜ በመሔድ፣ እምብዛም የተጨበጠ ነገር አላገኘችም እንጂ ታንጉት አንዳንድ ነገሮች ለመታዘብ ችላለች ። ብዙ ካህናት በአቡኑ አዳራሽ እየተሰበሰቡ ሲወያዩ ሲከራከሩ ይውላሉ ። ታንጉት ብዙውን ነገራቸው አይገባትም ። ስለ ምሥጢረ ሥላሴ ፣ ስለ ሥርዓተ ቅዳሴ ፣ ስለ ክርስቶስ ባሕርይ ነው ። በመካከሉ አዲሱ የቴዎድሮስ ውሳኔ በሀገሪቱ አብያተ ክርስቲያናት ላይ ስለ አስከተለው ጉዳት ይነግና የብዙው ካህናት ስሜት በንዴት ይግላል ። ‘ እኮ አባታችን ፣ ቢተ ክርስቲያን ጨርሳ እስከ ትዘጋ ዝም ብለን እንይ ? ’ እስከ ማለት የሚደርሱ ነበሩ ። የገብርዬ ሚስት መሆንዋን የሚያውቁ ቢኖሩም ፣ በነገራቸው የሚፈሩበት አይመስሉም ። ‘ አሁን ተፈቱ እንደዚህ ደፍረው ይናገሩ ይሆን ? ’ የሚል ሐሳብ ይመጣባታል ፣ ታንጉት ። አክሊሉ የሉዛ ማርያም አለቃ ብቻ ቢሆንም ፣ በካህናቱ ዘንድ ከፍተኛ ተሰሚነት ያለው ይመስላል ። ግን ፣ የቴዎድሮስን ውሳኔ በግልጽ ተቃውሞ ሲናገር ሰምታው አታውቅም ። ነገሩን እንደ ዋዛ አንሥቶ ለሌሎቹ ይተወዋል ።

ባልንጀርነታቸው በጣም የሠመረ በመሰለበት ፣ ገብርዬ ተሽሎት በምርኩዝ በግቢው ውስጥ መረማመድ በጀመረበት ወቅት ፣ እነጋሪድ ድንገት መምጣታቸውን አቆሙ ፣ ብዙ ቀናት ዐለፉ ፣ ሳምንት ሞላ ። ገብርዬ በመቅረታቸው ቅር የተሰኘ ወይም የተገረመ ሳይመስል ፣ ከግቢው ወጣ እያለ ከመንደሩ ልጆች ጋር በመጫወት ጊዜውን ያሳልፍ ጀመር ። እንዲያውም አንድ ሐሳብ የወረደለት መሰለ ። ታንጉት ግን ከነከናት ። ከልጆች ጋር የሚያሳልፈው ጊዜም ሠቀቀንዋን እንደገና እየቀሰቀሰባት ሔደ ። ሁለተኛዉ ሳምንት እንደ ተገባደደ ፣ አላስችል አላትና ጠየቀችው ።

“ ምን ሁነው ነው ኧሪ የጠፉት ? ”

“ ወረታቸው ቢያልቅ ነ ዋ ! ” ሲል በማታለል መለሰላት ።

“ እንድ ነገር ቢሆኑ ነው ? ”

“ ቢሆኑ እንሰማ ነበር ። ”

“ ተቀያይማችኋል ? ”

“ ምን እቀያየመን ? ”

“ ማለቴ እንድ ነገር ተናግረውህ ፣ ወይም ተናግረሃቸው እንደሆነ ብዬ ነዋ ! ”

“ እንቺ ምን አስጨነቀሽ ? ”

“ ባይጨንቀኝም መቸስ ይከነክናል ! ”

ደግማ ደጋግማ ካነሣችበትና ‘ እኔ እንሱንም ቢሆን እጠይቃቸዋለሁ እንጂ ! . . . ’ ካለችው በኋላ ነበር ምክንያቱን የነገራት ።

የምሳ ገበታ ተነሥቶ ሁለቱ ብቻቸውን ቡና እየጠጡ ነበር ። “ እይው እንግዲህ ፣ የነሱ ነገር ተሆድሽ አልጠፋ ታለ ” ሲል ጀመረና የሆነውን በአጭሩ ተረከላት ። አንዳች ምሥጢር የሚፈልግበት ይመስል ፣ የጠጣበትን ፍንጃል ከእጁ ላይ እያገላበጠ ፣ አእምሮው ግን ዝርዝር ሁናቴውን እንደገና እንደ ፈትል ያጠነጥን ነበር . . .

ገብርዬ ምርኩዝ ይዞ ትንሽ መንቀሳቀስ እንደ ጀመረ አንድ ቀን ምሽት ፣ ሥስቱ ወደ ጓሮ ወጥተው ራት እስኪደርስ ከየድንጋይ ላይ ዐረፍ ብለው ነበር ። ሙሉ ጨረቃ ወጥታለች ፣ የሚበርድ ሳይሆን ቀለልና ቀዝቀዝ ያለ አየር ይነፍሳል ፣ እንቁራሪቶች ቋ ! ቋ ! ቋ! !ይላሉ ። ዐልፎ ዐልፎ የሰዎች ጥሪና የከብቶች ጩኸት ይሰማል ። ከማዶ በቁስቋምና በአባ እንጦንዮስ ፣ እሳት ብልጭ ብልጭ ሲል ይታያል ። ጉንደር ከተማ ከናካቴው ጭር ባትልም የሚያስደስት ጸጥታ ሰፍኖባታል ። የዜማ ተማሪ

ቀስ ብሎ ድምፁን የሚያሽበት ፣ ከብቶቹን ያስገባ እረኛ ዋሽንት የሚጫወ
ትበት ፣ ጉልማሳ ለእጮኛው ወይም ለወዳጁ የፍቅር ዜማ የሚያንጐራጉ
ርበት ምሽት ዐይነት ነበር ።

በአካባቢው ላይ የሰፈነው ጸጥታ ፣ በእነርሱም መንፈስ ውስጥ የሠረጸ
ይመስል ሦስቱም ጭውውቱን ትተው፣ በየራሳቸው ሐሳብ ተውጠው ዝም
ብለው ቆዩ ። ገብርዬ የሚያስበው ፣ ድንገት ባላሰበው ሁናቴ መቁሰሉ ፣
‘ለካንስ ድንገት መሞትም አለ ለካ?’ የሚል ሥጋት ከአሳደረበት ወዲህ
ዐልፎ ዐልፎ በአእምሮው የሚመጣበትን ጉዳይ ነበር ። ልጅ አለመው
ለዱ ። ኪታንጉት ጋር እስከ ዛሬ ሁለት ሦስት ልጅ የሚያደርሱበት ጊዜ
ነበር ። ግን የአንዱም እርግዝና አልሞከራት ። ‘እኔ ነኝ መኻን እርሷ?’
ሲል በሐሳቡ ይጠይቅና በታንጉት እንዳያመካኝ ከጋብቻው በፊትም ሆነ
በኋላ ፣ ዐልፎ ዐልፎ ከሌያባቸው ሴቶች የልጅ ወይም የርግዝና ነገር ከላ
ጋጠመው የወንድ ልጅን መኻንነት ማመን እያዳገተው ግራ ይገባዋል ።
ዛዲያ መቸም ሰው ቁሞ አይኖርምና ስሙ የሚጠራበት ፣ ዘር ሳያስተርፍ
ሊያልፍ ነው? ጉዳዩን ከታንጉት ጋር አንሥቶት ባያውቅም ከቅርብ ጊዜ
ወዲህ እየከነከነ አስቸግሮታል ።

‘‘በእንደዚህ ያለ ጊዜ ወንድ ልጅ ይሸፍታል!’’ አለ አክሊሉ ፣ እንደ
መጣላቸው በድንገት የሚናገሩትን በመስማት የሚያስቡትን ለማወቅ ።

‘‘ የሴት ልጅ ደግሞ ተኝቶ ያንኮራፋል ’’ ሲል ጋረድ ሰጠቅ አደ
ረገ ።

‘‘ ስለ ሽፈታና ስለ ሕልም ስትናገሩ የትናንት ሴሊቱ ሕልሜ ትዝ
አለኝ ’’ አለ ገብርዬ ድንገት ከእንቅልፉ እንደ ባነነ ሰው ።

‘‘ አንተም ታልማለህ ? ’’

‘‘ እኔ ምንድነኛ ? ’’ ጥያቄው አድናቆት ይሁን አሽሙር ስላልገባው ፣
ገብርዬ ግንባሩን ቋጠርጠር አደረገ ።

‘‘ አየህ ሰው በእንቅልፉ ሕልም የሚያልምበት ፣ በውኑ ብዙ የሚ
ጨነቅ ፣ የሚያንሣው ፣ ብዙ ሐሳብ የሚያዘውና በሕይወቱ ብዙ የሚመኝ
ሲሆን ነው ይባላል ’’ አለ አክሊሉ አሰላሰሶ ።

ገብርዬ ፣ አሁንም የነገሩ ትርጓሜ በትክክል አልገባውም ። ‘‘ እዛዲ
ያስ ? ’’

‘‘ ዛዲያማ አንተ የምትመስለኝ ሞት እንኳን ዐይኑን አፍጦ ቢመ
ጣብህ ፉንክች የማትል ፣ ለማንም የማትበገር ቆራጥ! በዚህ ላይ የቴዎድ
ሮስ ጦር አዛዥ ሆነህ የምትመኘውን አግኝተህ ተሆነ ፣ ምን ሕልም ይታ
ይሃል ብዬ ነዋ! ’’

‘‘እቢት — እቢት! ‘ ያሮን ሲደልሉዋት በመጫኛ ጣሉዋት ’ አሉ ።
እንተምኮ በውዳሴ ንገርህ እንተቴን ገዘገዝከው ። ተዚህ ውሳ ፣ ጉባኤ ቃና

ነው ዘ — ሥላሴ የምትሉትን ቅኔ ብትዘርፍልኝ አይሻልም ’’ አለና ገብ
ርዬ በነገሩ ክት ክት ብሎ ሣቀ ። ግን በቆራጥነት መወደሱን አልጠላውም ።

‘‘ ሙት — ሙት ! ጸድቁን አልሃለሁ እውነቴን ነው ። ’’

‘‘ እውነትህን መሆኑን መቼ አጣሁት ? ’’

‘‘ ዛዲያ ሕልሙን ንገረና ! ’’

‘‘ አታልምም ብለኸኝ ። ’’

‘‘ ታለምክስ ? ’’

‘‘ ተውኩታ ! ’’

‘‘ ሕልምህን ለመንገር ፈራሃ ! ’’

‘‘ ምን አስፈራኝ ። ’’

‘‘ ዛዲያ ንገረና ! ’’

‘‘ ግም ሕልምኮ ነው ’’ አለ ገብርዬ በግጥላላት ትከሻውን ነትነት
እያደረገ ።

‘‘ ሕልም ‘እንደ ፈችው ነው’ ተብሏል ። መጥፎም ደግ የለውም ’’
አለ ጋረድ ።

‘‘ እይ — እንደሱስ አትበል ። እንደ ገሃዱ የሚቈጠር እውነተኛ
ራዕይ ደሞ አለ ’’ ሲል አክሊሉ አረመው ።

‘ እሺ ሕልምም ሆነ ራዕይ ለሁሉም እንስማው ’ በማለት ገብር
ዬን በውትወታ አስጨነቁት ።

ገብርዬ ነገሩን በማንጣቱ ትንሽ ጸጸተው ። ‘‘ የሸፈትን ይመስለ
ኛል ’’ አለ ነገሩን ያታለለ በመምሰል ትከሻውን ሰበቅ አድርጎ ።

‘‘ እንግን ? ’’ ሲል ጋረድ ጠየቀ ።

‘‘ በግን ላይ ? ’’ ሲል አክሊሉ ለጠቀ ።

በገብርዬ የታግኝነት ስሜት በሕልም እንኳን መሸፈት ራሱ እንደ
ክህደት የሚቈጠር ነበር ። ይህንን ክህደት እንደ ደኅና ነገር ለሰው ማው
ራት ደግሞ ከትዝብት ያለፈ ዓመፅ መስሎ ተሰማው ። ሰው በሚጠላው
ላይ ይሸፍታል ። የተበደለ ሰውም ቢያምፅ አይፈረድበትም ። በሚወዱ
ትና በሚታመኑት ላይ እንዴት ሲደረግ ይታሰባል ? ገብርዬ መልስ የሚያ
ገኝበት ይመስል ቀና ብሎ ሰማዩን ተመለከተ ። ጸጥ ያለ ፣ የረጋ ነው ።
ዘለዓለማዊ ሥርዓት የሰፈነበት ይመስላል ። ገብርዬ ተራቅቆ ባያፈላሰ
ፍም ግንም ሰው እንደ ጠቅላላ ሥርዓት መከተል እንደሚገባው ይሰማ
ዋል ። በወር ሚዳ ደረቱን አስጥቶ ፣ ልቡን ሰጥቶ የሚዋጋውን ያህል አገር
ለመበጥበጥ ፣ መንደር ለማመስ ፣ ለመዝረፍ ወይም ለመፈራትና ለመታ
ወቅ የሚደረግ ሽፍትነትን በጣም ይጠላል ፣ ይጠየፋል ፣ ቴዎድሮስን

ያመነበትና በቲዎድሮስ የታመነበት ዋናው ምክንያት ይኸው ነበር ። ቲዎድሮስ፡ ስለ ኢትዮጵያ አንድነትና አዲስ ዐይነት አስተዳደር ባላቸው ከፍተኛ ዓለማ ፣ ያገሩ ሥርዓትና ዕድገት አርአያ ሆነው ይታዩታል ። ዛጲያ የመሸፈቴን ሕልም ምን አመጣው ? አርግጥ ወዳያው የቆሰለ ሰውን ከትኩሳቱ ጋር ብዙ አታኸፍቶት ነበር ። የዚህ ዐይነቱ ሕልም ግን ለአንጉት ልፍ ዓለሙ እንግዳ ነበር ። አልመዋለሁ ብሎ የማያገ'ተው ስለሆነ ሕሊናውን ሠቅቆት ነበር ። አውን ለሰው መንገሩ ደግሞ የሐፍረት ሠቀ ቱን አሳደረበት ።

" እስተዚህም'ኮ አይደለ ! " አለ ንብርዱ ከጠራው ሰግይ ላይ ዐይኑን እንደ ተከለ ። " ዝርዝሩንም በትክክለኛ አላስታውሰውም ። ዝብርቅርቅ ያለ ነበር ። " ከዚህ ላይ እውነቱን ነበር የተናገረው ። ጠቅላላው ትርጒት ጉልቶ ቢታየውም ፣ የጊዜ ፣ የቦታና የሰዎች መታወቂያ ከእውነተኛው ሕይወት ጋር የተመሳሰለ አልነበረም ። ጊዜው ፣ ቀንና ሴሌት ፣ ሥፍራው ቆላና ደጋ ፣ ተራራና ሸለቆ እንዳንዶቹ ሰዎች ዊራት የመሳሰሉ ፣ መላ ቅው የጠፉ ነበር ። " እንዳልኩት በትክክል አላስታውሰውም ። ደንብር ብሩ የወጣ ዐይነት ነው " አለ ንብርዱ ችላ ብለው እንዲተዉት ነገሩን በማቃለል አውንም ወደ ጠራው ሰግይ እንዳንጋጠጠ ።

" ይሁና ዛጲያ ፣ ምናለ !"

" ሕልም የተዘበራረቀውን ያህል ምሥጢሩ በዚያው ልክ ነው ረቂቅ መጢቅ የሚሆነው ፣ ስለይህ ንገረን " ሲል አክሊሉ አፋተወ ያዘው ።

መንገር እንዳልቀረለት ሲረዳ ፣ እምጠየሚያወጣው ይመስል ንብርዱ በሰሬው ተነፈሰ ። " ለነገሩማ ቢረቅቅ ቢጉላ እኔ ምንተዳዬ ! ዐይነቱ ግን አስገርሞኛል " በጉጉት እየጠበቁት ላንዳፍታ ዝም ብሎ ቆየና ቀጠለላ ቸው ። " በንድ ትልቅ መስክ ሕዝብ ተሰብስቦ ፡ የጋማና የቀንድ ከብት ላይለይ እየታረደ የሚበላ ይመስለኛል ። የጥብሱ ጢስ እንደ ሐምሌ ጻመና እየሩን አፍናታል ፣ አጠይሞታል ፣ ከአንዳንድ ሥፍራ ሰው እርስ በርሱ ይብላላል ። " ንብርዱ የሁናቴው ቀፋፊነት ያሳከከው ይመስል ግኩሉዉን አውጥቶ ጆሮውን በየተራ ሰቀሰቀ ። " በሌላ ሥፍራ በአንድ ትልቅ ዋርካ ዙሪያ ከወገባቸው በላይ ራቁታቸውን የሆኑ ሴቶች እየተንጋለሱና እየተ ደፋ ምሕላ የሚያደርሱ ይመስለኛል ። መዶሰ ቁርባንም ይመስለኛል ። በዚህ መካከል አምስት የምንሆን ሰዎች እንደ ሽፍታ በገመድ ተጠፍረን ከንጉሥ ፊት እንቀርባለን ። "

"እነማን ንጉሡ ማነው ?" አለ አክሊሉ ፡ በዚህ ሕልም በኩል የንብ ርዱን ጥላቻና ፍቅር የያረሰበት መሰለው ። ቅዠትም ይሁን ትንቢት የሰው ሐሳብ ፍላጉትና ምኞት በሕልሙ ይመጣበታል ። በይሉኝታ በማብዝነት ፣ በፍርሃት የተጻፈን ስሚት በሕልም አማካይነት እየገነፈለ ፡ የሥውር ሕሊናን ጓዳ እየበረገደ ይወጣል ። ስለ ሰው ስሚትና ዝንባሌ

ከሰውን ሕይወት ይልቅ የሕልም ዓለም የተሻለ ግልጥ ሳያለሆን ይረቀቅ ! አክሊሉ በዎሽቱ ዉለማ ዐይኖቹን ብልጣጥ አድርጉ የንብርዱን ገጽታ ለማንበብ ሞከረ ።

" ተኔ ጋር የተያዙት እንማን እንደሆኑ አያለዩኝም ። ጠም የለውም ፣ ሹርባ አልተሠራም እንጂ ንጉሡ ቲዎድሮስ ይመስለኛል ። "

" እሺ ተዚያ በኋላስ ? " በማለት ጋረድ እንደ መቅበጥበጥ ታጣው ።

" ተዚያ ንጉሡ እኛን ሲመለከት ራቱ በርበሬ ይመስል ና ወደ ፍም እያተለወጠ ሔዶ የሚንቀለቀል እሳት ይሆናል ። ወላፈኑ ሲገርፈን ጊዜ የኃሊት እንደ መሸሽ ስንል ወታደሮች ወደፊት ይገፈትሩናል ። እንዲህ ሲል — በንበል ባሉ መካከል የንጉሡ ቁመና እንደገና ቅርጽ ያወጣና በቅሪ መንግሥቱን ቀና አድርጎ ወደኔ እየጠቆመ ፡ ' አንተም ደሞ ንብርዱ ! አን ተም ! ' ሲል እንደ ነጉደጓጅ ይሙህብኛል ። ' ኧረ እኔ ምንም አላጠፋሁ ' ለማለት እሞክርና ድምፄ ሰልሎ ያቅተኛል ። "

" የሚገርም ነው ። የደብረ ሲናው ቁጣጽዮ ። አንተ እንደ ሙሴ ፡ እሱ እንደ ኤሎሂ ! "

" እክሊሉ አንተ ትቀልድብኛለህ ልበል ? "

" ሙት የምሬን ነው ። የነበልባሉ ፎናቴና ከነበልባሉ ድምፅ መው ጣቱ እደመሳሰልም ነው የምትት ? ይልቅስ ጨርስልን ። "

" ይኸው ነው ። ' ደሞ ይከጻል ! ' በሚል የቁጣ ድምጥ በበትረ መንግሥቱ ዐይኔን ሲሸነቁረኝ ሲቃጣ ብንን ብዬ ነቃሁ ፡ ሳብ አጣም ቆኝ ። "

" በቃ ይኸው ነው እንደዚህ የዘገነነህ ? "

" ከዚህ የባሰ ምን ሊመጣ ኑርዋል ? " አለ ንብርዱ ስቅጥጥ በማ ለት አኳኋን ራሱን እየነቀነቀ ።

" ሕልምኮ ነው ! " አለው ጋረድ ።

" ሕልም መሆኑ ብቻ በጀ ! ለዚህ አይደለ ደፍሬስ ያወራውላችሁ ! "

" እውነት ቢሆን ኑርሳ ? "

" ምኑ ? " ሲል ንብርዱ በመገረም ጠየቀ ።

" ሕልሙ ነዋ ! "

" እንዴት አርጎ ሕልም እውነት ይሆናል ! "

" ማለቴ — ማለቴ " ሲል አክሊሉ ድንገት ዘባርቆ ነገሩ እንዳይ በላሸበት ላፍታ ገታ ብሎ ከአፉ የሚወጡትን ቃላት መዘናቸው ። ንመገ ማቸው ። ደፈር አለና ሐሳቡን ተፋው ። " መሸፈትህ ሕልም ላይሆን እውነት ቢሆንስ ? ምን ትሆናለህ ! ጨርቅህን ጥለህ ልታብድ ! "

ገብርዬ አውንም ነገሩን ትክክል አልተረዳውም ። “ እንዴት አርጎ ሕልም እውነት ይሆናል ? ምናልባት በጊዜው እንደ ትርጓሜው ይደርስ ይሆናል እንጂ ። ”

አክሊሉ፣የመናገር ድፍረቱን ጨምቆ የሚያወጣ ይመስል በጨለማው ፊቱን ጭፍግግ አድርጎ ምንጋጋውን አጣበቀ ። “ እኔኮ ያልኩት በሕልም መሸፈት እንዲህ ያረገህ ፣ በውንህ ብትሸፍት ማለቱ ነው ። ”

“ መሸፈት ? እህ መሸፈትማ ማንስ ይሸፍት የለ ! ዋናው ነገር መሸፈቱ ሳይሆን በማን ላይ መሸፈቱ ይመስለኛል ። ”

አክሊሉና ጋረድ ፣ በጨለማው በዐይን ተፈላለጉ ፣ ሳይነጋገሩ ሐሳብ ለሐሳብ ተገናኙ ። ነገሩ የሚታወቀው ፣ የሚለየው አውን ነው የሚል ስሜት በሁለቱም ላይ አደረ ፣ ፍንጭ ተገኝቷል ፣ ገርበብ ያለውን የአእምሮ በር በርግደው ገብተው አስተሳሰቡን ማወቅ አለባቸው ። አክሊሉ እጁን ነጠቅ አድርጎ በመመለስ ምልክት አሳየው ። ጋረድ ጭንቅላቱን ወደ ኋላ ቀልበስ አድርጎ መስማማቱን ገለጸለት ።ጥቅቅሳቸውን እንደ ዋዛ ቢያያም ለጊዜው ምሥጢሩ አልገባውም ነበር ።

አክሊሉ ፣ ነገሩን ለማለስለስ ጉሮሮውን በትንፋሹ ደግሞ ደጋግሞ ጠራረገ ። “ የምልህ ፣ የምትሸፍተው አንተ ፣ የምትሸፍትበትም በሕልም ያየኸው ቢሆንስ ? ” አለ አክሊሉ ፣ ጥያቄውን በተቻለ መጠን እንደ ቀላል ነገር ጣል ያደረገው ይምሰል እንጂ ፣ አካሉ ከተቀመጠበት እየተናጠ፣ ስሜቱ እየተናወጠ ነበር ።

“ ምን ? እኔ በቴዎድሮስ ላይ ልሸፍት ? ” ጥያቄው ሳይሆን ቁጣው አይሎ ገብርዬ ከተቀመጠበት ተወርውሮ ተነሣ ።

“እህ ? መቸስ . . . መቸስ ” በማለት አክሊሉ ጥቂት እንደ ማቅ ማግት አለ ። “ ለጊዜው ከቴዎድሮስ በቀር ሌላ ንጉሥ የለን ። ”

“ ሳሊለን ቅድስት - ሳሊለን ቅድስት ! ” ሲል ገብርዬ እገደ መሐይም አማተበና በሁለት እጁ ጭንቅላቱን ያዘ ። “ ምነዋ ! ምነው ወንድሜ ነውርም አይደለ? ”

“ ምኑ ነው ነውር ? ” ሲል ጠየቀው ።

“ ምንስ ቢሆን እንዲህ ታስብልኛለህ ? ”

“ ተከፋህ እንዴ ? ” ሲል ጋረድ በማባበል መልክ ጠየቀው ።

“ ክፉኛ እንጂ !” አውንም ገብርዬ በመገረም ራሱን ነቀነቀ ።

“ ምነው አዲስ ነገር አረክው ? ”

“ እሪ ከአዲስም አዲስ ትንግርት ነው እንጂ ! ”

“ እንተ ራስህ በራስ አሊ ላይ አልሸፈትክም ? እሱስ በሚሸቱ አያትና አባቷ ላይ አልሸፈተም ? ”

“ ‘ያ - ሴላ ይሽ ሴላ ’ ይላል ሸማኔ ! ምን አገናኝቶት ? ”

“ ምን ለያይቶት ?”

ገብርዬ፣ ንዴትና ቁጣ ቢተናነቀውም ራሱን ለመግታት ሞከረ ። “ እኔ በደል ፣ ጥቃት ቢደርስብኝ ሜካ ገባሁ ። ቴዎድሮስም የሆነ እንደሆነ ለእማቱ ከመታመን ላገሩ አንድነት ፣ ላገሩ ትልቅነት ያለው ዓላማ ቢበ ልጥበት ነው የሸፈተው ። የሱ ሽፍትነት አይባልም ። ፈጥሞ ! አገሩን በጉዱ ወንበዴዎች ላይ ነው የተነሣው ። ልፋቱና ጥረቱ ሁላ እኔንም ይሰ ማኛል ። በዚህ ላይ ከልብ የሚያምነኝ ፣ ከልብ የምታመነው የልብ ወዳጄ ነው ። ለነገሩ ይህንን ሁሉ አውን ምን አስለፈለፈኝ ? ” አለና ተወው ።

“ ጨርሰው እንጂ ! ” ሲል የአክሊሉ አንጋገር የውትወታ ቃና ነበረበት ። “ ወዳጅህ ሆኖ ምን አደረገልህ ?”

“ አሆሆ ! ምን ያላደረገልኝ አለና ?”

“ እንግዲያውስ በራስ አሊ ላይ የሸፈትከው ምንም ስላላደረጉልህ ተመቅኝተህ ነዋ ?”

“ ቢመረኝ ዝም ብዬ ነው በረሃ ገብቸ የተቀመጥኩት ። ”

“ በኋላ ግና ከካሣ ጋር ሆነህ ወግተሃቸዋል ። ”

“ በሀገራችን ምህኖት ጠላቶች ከሆንን በኋላ ነዋ ! ”

“ ዛሬያ ከቴዎድሮስ ጋርስ አንድ ቀን ጠላቶች የማትሆኑበት ምን ምህኖት አለ ? ”

“ ያለ ምህኖት ? ” ሲል ገብርዬ በመገረም ጠየቀ ። “ ከመሬት ተነሥቶ እንደዚሁ ጠላት መኳኳን የለም ። ምህኖት ያሻዋል ። እስቲ ቴዎ ድሮስን በምን ልጥላው ? በምን ልመቅኘው ? አልበደለኝ ! በጥቅም ፣ በምቾት ፣ በሀብት አልበለጠኝ ! ተቀምጦ ፣ በዚህ ውጡ በዚህ ውረዱ ብሎ አያዝ ! ከኛው ጋር ይዘምታል ። እንደኛው ይዋጋል ። እንዲያውም ከኛ ቀድሞ ! ያለውን አብረን እንበላለን ! አብረን እንጠጣለን ! ሐሳ ቡን ፣ ዓላማውን አብረን እንማከራለን ! መሪ ተመሆኑ በቀር እሱ ተኛ የተለየ ምን ነገር ያለው መሰላችሁ ?! ” አንጋገሩ ጥያቄ ሳይሆን የማረጋ ገጥ ዐይነት ነበር ።

“ እኛንስ የገረመን ይኸው አይደል ! ከኛ የተለየ ሳይኖረው በዚያ መከረኛ ዙፋን ላይ . . . ” በማለት አክሊሉ ንግግሩን አንጠልጥሎ ተወው ፣ እንዴት እንደሚጨርስ የተቸገረ ይመስል ።

አክሊሉ ንግግሩን ባይጨርስም ፣ ገብርዬ የሰማው በቅቶት ነበር ። ሁለቱንም ተራ በተራ በዚያ ጨለማ ሊያያቸው ፣ ሊያፈጥባቸው ሞከረ ። ወዳጅነቱን ስለ መፈለጋቸው ሕሊናውን ሲከነክነው ለቆየው እንቆቅልሽ አውን ፍንጭ አገኘ ። ‘ አዎ ! እንደዚያ መሆን አለበት ’ አለ በሐሳቡ ።



“ እረ ይኸ ሁላ የነገር ዳርዳርታ ምን ብታስቡ ነው ? ከኔስ የምት ፈልጉት ጉዳይ ምንድን ነው ? ” ሲል ጠየቃቸው ፡ በንዴት ይብገን እንጂ፣ የገብርዬ አነጋገር ፍርጥም ያለ ሆኖ የለዘብታ ነበር ።

“ እረ አንዳችም ! ” አለ አክሊሉ ።

“ ወዳጅነትክን እንጂ ! ” ሲል ቀጠለ ጋረድም ፡ ፋታ ሳይሰጡት የተማከሩ ይመስል መልሳቸውን በጥድፊያ ተቀባበሉት ።

“ ዛዲያ እንደዚህ ያለ ነገር ለምን ታነሣላችሁ ?” አሁንም አጠያየቁ ለዘብ ያለ ነበር ።

“ ጨዋታ በጨዋታ ይነሣል — እንዳመጣጡ ። ምን ክፋት አለ በት ? ”

“ ከሆነማ እሺ ። እንዳፋችሁ ያርገዋ ! ” አለ ገብርዬ ። የጥርጣሬ አሽሙሩን ጣል ያደረገው እንደ ዘበት ነበር ። ነገር ግን፡ ለዐይን ያዝ ባደ ረገው ምሽት ፡ በኃፍረትም ይሁን በሐሳብ ላመል ያህል አንገታቸውን ሰበር ሰበር ሲያደርጉ እንደ ጠረጠራቸው መገንዘባቸውን ዐወቀ ።

ራት ሲበላ እንደ ሰሞኑ ተዝናንተው አልተጨዋወቱም ። ለራትም ቢሆን የቆዩት ፡ ነገሩን ያዘናጉ ስለ መሰላቸው ወይም ለምንተፍረት መሆኑ ለገብርዬ ተሰምቶታል ። የተሰነባበቱት በሙሉ ዐይን ለዐይን ሳይታያዩ ነበር . . . . . .

“ ዛዲያ ምን አሰብክ ? ” ስትል ታንጉት ጠየቀችው ፡ ከተረከላት በኋላ ።

“ ደሞ ምን አስባለሁ ብለሽ ! እንደዚህ ያሉትን ያው በሩቁ ነው እንጂ ! ”

“ ማለቴ ለአባ ታጠቅ ትነግረዋለህ ? ” ታንጉት ቴዎድሮስ የጣ ሉባት አደራ ድንገት ትውስ አላት ።

“ ምን ብዬ? ጥርጣሬ እንጂ የጨበጥኩት ነገር የለ ! ‘ሽፍት’ ብለው አልመከሩኝ ። ወይ ‘አብረን እንሽፍት’ ብለው አልጠየቁኝ ። ‘ቢሆን’ ብሎ ነገር ይዞ እንዴት ተሰው ይቀረባል ? ደሞስ የራሴን ሕፅ ምስ ቢሆን እንዴት ብዬ አወራለታለሁ ? እሠሠሠ ! ” አለ ገብርዬ በመገረም እንደ መሣቅ እየሞከረው ።

“ እና ፣ ለጊዜው መተሩፈር ይሆን? ወይንስ ተናካቱው ቁርጥ ያለ አለመደራረስ መሆኑ ነው? ” የታንጉት ጥያቄ ለራስዋ ጭምር ነበር ።

“ ወደፊት እናያለና ! ”

“ የወደፊት ሕይወታቸው እንደገና መጋጨት ግን በሰላምና በበጎ ላይሆን ነው ።

ምዕራፍ ሦስት

ገብርዬ ፡ ምናልባት ከተፈጥሮውም ባይሆን ፡ በኋላ ከእናኗሩ ወርሶ እንደ ተዋሐደው ሰውን በቀላሉ የማይቀርብ ነው ። ጋይንት ዙራምባ ማር ያም ፡ የአባቱን መሬት ደብረ ታቦር ላይ እየተንሰራፋ የሔዱት የራስ አሊ ዘመዶች ነጥቀው ፡ ጉልት አድርገውበት በረሃ ከገባ በኋላ ፡ አዳኝ እንደሚሠጋ የዱር አውሬ ሰው በሩቁ ሰ ያስተውል ፡ ሲገመግም ነበር የኖረው ። በመጀመሪያ የሚያውቀው ልቡን ከፍቶ እንደ ልቡ የሆነበት ፡ አባቱ ‘የራስ አሊ ዘመዶች ናቸው’ በሚባሉ ሰዎች ከመገደላቸው በፊት ከሠፈሩ ልጆች ጋር የፍቅር ፡ የጨዋታ ወዳጅነት የመሠረተበት የልጅ ነት ዘመኑ ነበር ። ከዚያም ጦር ለመወርወር ፡ ጋሻ ለመመከት ሲችል አንድ ቀን ወደ ቆላው ወርዶ ከመሰሎቹ ጋር ተቀላቀለ ። ግን ገብርዬ እየ ቆየ እንደ ተረዳው ፡ በጅምላ በረሃ የገባው ሁሉ ተመሳሳይ ሐሳብ ፡ ተመ ሳሳይ ፍላጐት ፡ ተመሳሳይ ጠባይና ተግባር አልነበረውም ። በየትም እየ ዘረፈና እየቀማ መኖር የሚፈልግ አለ ። እንደ መነነ ባሕታዊ ነገር ዓለ ሙን ትቶ ከዱር ፍሬ ፡ ከእውደማ እንደተገኘ ጥሬጥሬ ያገኘውን እየ ቀማመሰ ሕይወቱን የሚገፋ አለ ። እርሶም ፡ ነግዶም ከራሱ የተደላደለና የተሻለ ነሮ ያለውን ሁሉ አኗኗሩንም ፡ ሕይወቱንም ያለ ምክንያት የሚ ያጠፋው ደግሞ አለ ። በበደል ምሬት ከኅብረተሰብ ሽሽቶ ምክንያ ቱን እስኪያውቅ ፡ መፍትሔውን እስኪያገኝ የሚንከራተተው እንደ ገብርዬ ያለው ደግሞ አለ ። ሁሉም አምሳያውን እየተመራመረ ያሰባስ ባል ። እምነት ፡ ፍቅር በጥቂቶች መካከል እየጠበበ ይሔዳል ። ይህ በስ ንት ፍለጋ የሚገኝ ፍቅርና መተማመን ግን ከብረት የጠነከረ ነው ። ሲበ ጠስም የዚያኑ ያህል በቀላሉ አይቀጠልም ። እንዲያውም ብዙ ጊዜ ከነ አካቴው ሊቀጠል አይችልም ። እንደ ልጅ ልብ ሲከፈት በሙሉ ይቀ በላል ፡ ሲዘጋ ጨርሶ ያርቃል ፡ መሐል መንገድ ፡ ግማሽ ስሜት የለ ውም ፡ ገብርዬ በዚህ ዐይነት መንፈስ ያደገና የኖረ ሰው ነው ።

ገብርዬ ፡ ከመጀመሪያውም እያመነታ ከነጋረድ ጋር የሞከረው ጓደ ኝነት እምነቱን ካቆሰለበት በኋላ ደግሞ ፡ የዕድሜ እኩዮቹ በሞሉበት በጉንደር ከተማ ቅርበቱንና ውስውን ከነአካቴው ከልጆች ጋር አደ ረገ ። ጧት ቁርሱን እንደ ቀመሰ ሥራዬን ብሎ እያዘገመ ይወጣና ለምሳ የሚመለስበት ፡ ከዚያም እንደገና ሔዶ ምሽት የሚገባበት ጊዜ አለ ። እንደ አካንዱራ ፡ ገበጣ የመሰሰለውን ፡ እንቅስቃሴ የማይጠይቀውን ከልጆች ጋር አብሮ ይጫወታል ።

ታንጉት፣ የገብርዬ ፍቅር እንዳልተቀነሰባት ብታውቅም ፣ በበኩልዋ ወይዘሮ ደብሬ ስላሉላት ከእርሷ ጋር የበለጠ ጊዜ እንዲያሳልፍ አስረ ሳጊ መስሉ ባይታያትም ፣ ሁናቴው ሐሳብ እያሳደረባትሔደ ። ' ሕይወቴን ሙሉ መንቀሳቀስ ለምዶ አውን ከቤት ሲውል መንፈሱ አልረጋ ለት እያለ ነው፣ ወይንስ ባለመውለዳቸው የልጅ ፍላጐት እየበረታበት መጥቶ ? ' ከግቢ መውጣት ሳይጀምር እርሱ ያደርገው እንደ ነበረ ሁሉ ፣ ኋላ ፣ ታንጉት ከደርቡ በራፍ ላይ ሆና ፣ ከመንደሩ ልጆች ጋር ሲጫወት ዝም ብላ ትመለከተውና እንዳች ወይነት የሐሳብ ትካዜ ይጫናታል ።

" አረ አንተ ሰው ልጅ መሆንህ ነው ? " ስትል ጠየቀችው ። " እንድ ቀን እግርህን እንፈራጥጠህ ቁሊዋን ስትሊጋ ማቂ ሙጥቶ ነበር ። " አንጋገርዋን ቀልድ ታስመስለው እንጂ ሐሳብዋ ከቀልድ የራቀ ነበር ።

" ተገኝቶ ነው ! " አለ ገብርዬ በእንድ ጉጂ የማታ ልብሳቸውን ሲደራርብላት ፣ በሌላ እጁ ታፋዋን እንደ መቆንጠጥ እያደረገ ።

" ልጅ ነው፣ ልጅነት ? "

" ሁለቱም ። "

" ባለመውለዳችን እያዘንክ ነው መሰለኝ ? "

" ምን አሳዘነኝ ። እሱ ባለው ጊዜ ይሆናል ። " አንጋገሩ ግን የቂ ዘመ ቃና ነበረበት ።

" ልጅ ግን በጣም ትፈልጋለህ ? "

አልመለሰላትም ። ሐሳብ እንዳይገባት ብሎ መሆኑ ተሰማት ።

"መቸስ እኔ እምቢ ታለኝ ለምን ተሌላ አትወልድም ገብርዬ፣ አን ተን ደስ ታለህ እኔ እንደሆነ አይክሩኝም ። " ከውስጥ ሐሳብዋ ግን የተ ናገረችውን በማስተባበል ሮጧባት ። እርሱ ልጅ ቢፈልግ ኑርሷ ካል ወለደችለት ፣ የሁለቱ የፍቅር ውጤት ፣ የሁለቱ የፀደን ማረፊያ ካልሆነ ምን ዋጋ አለው ! እንዲያውም ከሌላ ሴት ተወለደ ፣ የሁለቱ ፍቅር ፣ የሁለቱ ግንኙነት አነሰም በዛ መለወጡ ይቀራል ! መቸም ሰው ነውና ወይንም ልቡም ወደ ውጭ ወደ ልጁ ፣ ወደ ልጅ እናቱ ሊከፈልበት ይች ላል ። በዚያው ልክ በሁለቱ መካከል የነበረው ሰሚት ተቀነሰ ፣ ሳንክ ገባበት ማለት ነው ። ' ካላንቺ ከሌላስ አላደርገውም ! በል ገብርዬ ' ስትል በሐሳብዋ ተግጠነችው ።

ገብርዬም ሐሳብዋን የደረሰበት ይመስል ፣ " የሁለታችን ልጅ ቢሆን ነበር እንጂ " አለ በቅሬታ መልክ ። ግን ሴላውንም በእርግጠኝነት ፣ የተ ቃወመ አልመሰለም ።

ታንጉትን ሠቀቀን እንደ ወሰፈ ወጋት ። " በተለይ ደሞ ተሸዋ ተተመለስክ ወዲህ ነው ዐይንህ ተልጅ ጋር በጣም የሚንከራተት የሆ ነው ! " ከመልሱ እንዳች ዐይነት መጽናኛ መፈለጉዋ ነበር ።

" ይሆናል ! " አለ ገብርዬ በደፈናው ።

" ያጋጠመህ ነገር ነበር ? "

ገብርዬ ፣ በድንገት ከእንቅልፉ እንደ ተቀሰቀሰ ዐይነት ' እእ ? ' የሚል ድምፅ አሰማ ።

" አንድ ነገር ደርሶብሃል ! " አለች ፣ እንድ ነገር እንደ ተሰማው እየተሰማት ።

" ለምን ተአእምሮዬ አይጠፋም ልጂ ! " አነጋገሩ ከራሱ ጋር ይመስል ነበር ።

"ምንድነው እሱ ንገረኝ እስቲ ! ወይስ ተኔ የሚሸሸግ ነው ? " ታን ጉት ላንዳፍታ ተመልሳ አጽናኝ ሆነች ።

" ምን የሚሸሸግ ጉዳይ አለበት ፣ የእንድ ልጅ ሁናቴ እኮ ነው ! " ሲል ገብርዬ ጀመረ ። የትዝታውን ትርዒት አጥርቶ ለማየት ይመስል በእጁ ፊቱን ጠረግ አደረገ ። " ተመቁሰሉ በፊት ነው ። እንኮበር ተሚ ሉት የእነሱ ከተማ አጠገብ ትልቅ ጦርነት ገጠሙንና ተጪት ጀምረን ስንከሳከስ ጀምበር ዘቅዝቅ ግለት ሰትጀምር እጠቃናችው ። ፈታቸውን መልሰው ሲበታተኑ ተኩተልናችው ። ሰምቼ የዋሣ ሰዎች አያይሉም ፣ ጨርሶ የተሸነፉ መስለው ያበተኑና እንደገና እድፍጠው መየተው አያጋ ይጥላሉ ። መጠጊያና እህል ውሃ እንድናጣ መንያሩን ፣ ጉተራ ውን ፣ ክምሩን ሁሉ ያቃጥሉታል ። ተዚያ በፊት ብዙ ጊዜ እንደዚህ ሠርተውን ነበርና እባ ታጠት እንዳያሞኝዋቸው ብሎናል ። ዛሬያ እኔም የእነሱ የመር አለታ የሚመስለውን ተኩተልኩት ፣ ልግርከው ። እለ ቶቻቸውን 'አቤቶ ገሌ ወይም የአቤቶ ገሌ ልጅ' እያሉ ነው የሚጠሩ ዋቸው ። እንዲህ አይምሰልሽ ሁሪያውን ሰብሰብ ብለው ነው የሚይዙ ዋቸው ።

" ዛሬያ ለያቸ አያቺው ነበር ። አንጣጥሬ ሞር ስወረውር ትክ ኛው ላይ ወጋሁት ። ግን ተፈረሱ አልወደቀም ። እንዴ ነጠት እንደ ግለት አረገውና ተኩርቻው ላይ ተደናቶ ግልቢያውን ቀጠለ ። እኔም አለቅም ብዬ ተኩተልኩት ። የኛ ከብቶች በመንገድ ብዛት ተዳክመው ነበርና እንደ ፈለኩት አልያረሰኩበትም ። ብቻ ትንሽ ነው የረቀኝ ። ተዚያም ተመንደር ያርሰን ተተልቱ ቤት ወርዶ ሲገባ በሩቁ ታየኝ ። በመንደሩ

ሰው አይታይም ። ይደበቃሏ! ተከብቴ ላይ ወረድኩና ባንድ እጄ ጦሬን ሰብቴ ይዤ፣ ባንድ እጄ ሽጉጤን ደግኜ በመጠንቀቅ ቀስ ብዬ ገባሁ ። ዛዲያ ምን አየሁ መሰለሽ ? ሰውየው ተመደቡ ላይ ተጋድሞ ደሙ በደረቱ ይወርዳል ። ዕድሜው ታሥር ዓመት የማይበልጥ አንድ ልጅ ታጠገቡ ተንበርክኩ ደሙን በጨርቅ እየጠረገለት፣ ' አይዞህ አባባ! አይዞህ እኔ አለሁልህ ! ' ይለዋል ፣ ልጁ መሆኑ ነው ። እንደ ልጅ ፈርቶ፣ ደንግጦ ማልቀስ የጨግ ነው ። ፍጡም ! የተገላቢጦሽ የቆሰለ አባቱን ያበረታታል ። ገርሞኝ ገብቼ ቆም ስል ጥላዬ ከበደው መሰል ዞር ሲል አየኝ። ተዚያ ለምን ጊዜው ተእንድ ጥግ እሙር ዱላ መዘገ አደረገና አባቱን በመከለል ፣ ' እኔ ኦያለሁ እስቲ አባቴን ትነካዋለህ ! ' ብሎ አያፈጥ ብኝም መሰለሽ ? እንዳልሥቅ የልጁ ተልቡ እንዳያ መሆን በጣም አስገረመኝ ፣ ልቤን ነካው ፣ አብሮ ወዲያ ወዲህ በማለት ተፈቴ እየተጋረጠ ሊያሳልፈኝ ነው ? አይነኩት ነገር ገና ተሬ ሕጻን ! ቢቸግረኝ ' እሺ አል ነካብህም የምጠጣው ውሃ ስጠኝ ' አልኩት ። ምኑ ሞኝ ሆነና! ላባቴ ዘብ እንደ ቆመ ፣ ' ተንሥራው አለሉዎት ' አለኛ ! ገንቦውን እንሥራ ነው የሚሉት ። አንቱታው ደግሞ እንጂ ! ውሃዬን ጠጥቼ ዝም ብዬ ወጣሁና ተመለስኳ ! በፊት አቤቶውን ስከታተለው አባ ታጠቅ አይቶኝ ኖሮ ፣ በግዳዬ ጥሎሽ ጊዜ ፣ ' ገብርዬ ፣ ምነው ዛሬስ ባዶ እጅህን መጣህ ? ' ሲል ጠየቀኝ ። ' ገደል ገባ መሰለኝ ጠፋብኝ ' አልኩት ። አገሩ ገደልማ ነው ። ዛዲያ ምን ብዬ ልንገረው ? ''

ገብርዬ ፣ ታሪኩን እንደ ጨረሰ ታንጉት ብታውቅም እርሱ በታሪኩ እንደ ተመሰጠ ሁሉ ፣ እሷም የምትናገረው ወይም የምትሰጠው መልስ ጠፍቶባት ዝም አለች ።

'' አይገርምሽም ? '' ሲል ገብርዬ ጠየቃት ፣ ከጥቂት ጊዜ ዝምታ በኋላ ።

'' ምኑ ? '' በማለት መልሳ ጠየቀች ። ልጅ ካለመውለዳቸው ጋር ያለውን ግንኙነት ያቃለለች መስሏት ነው እንጂ ፣ ታሪኩ የእርሷንም ስሜት ነክቶት ነበር ።

የገብርዬ መልስ ግን የባሰውን እናወጣት ። '' እህ ! ዐሥር ዓመት የማይበልጠው ልጅ ለአባቱ እንደዚያ ዘብ መቆም ! እንደዚያ ያለ ልጅ ተተኩ ቢሞቱስ ምናለበት ! ያንን ልጅ ታየሁ በኋላ ሳይወልዱ መሞት የሞት ሞት መስሎ ነው የተሰማኝ ! ምንጊዜም ተሐላቢ አልጠፉ ነዉ ያለው ። '' የፊቷን በሠቀቀን መለዋወጥ ሲመለከት አዋርጦ ተወው ፣ የተናገረው በስሜት ተውጦ ሳይታወቀው ነበር ።

ታንጉት ፣ መላ ሰውነቷን ጭምቅ የሚያደርግ አንድ ዐይነት ምጥ የያዛት መሰላት ። ቀስ አለችና ፊቷን አዙራ ተጋደመች ። በማባበል ፊቷን ሲደባብስ እጁን እርጥበት አቀዘቀዘው ። '' ምንድን ነው ! '' አላት ፊቷን ወደ እርሱ እየመለሰ ።

'' አንተ ልጅ በጣም ትፈልጋለህ ፣ እኔ ደሞ እምቢ አለኝ ! '' አለች መላ ሰውነቷ በሠቀቀን እየተሰበቀ ።

'' ብትጠይቂኝ ታሪኩን ነገርኩሽ እንጂ አሁን ጠፍጥፈሽ አድር ሺልኝ አልኩሽ ! '' በማለት ዕንባዋን እየጠራረገ ፣ እየደባበሰ ፣ እያሻሸ ሊያጽናናት ሞከረ ። ሁናቴው በዚህ አላበቃም ። ወደሚቀጥለው ተሸጋገረ።

ታንጉት ግን ፣ ፍላጐቱን በሙሉ ፈቃድ ታስተናግድ እንጂ ፣ ስሜቷን ከስሜቱ ለማዋሐድ ትሞክር እንጂ ' . . . . እባክህ ፈጣሪዬ ለዘር ብታበቃን ! እባክህ ! ' እያለች ባልተለመደ ጊዜና ሁናቴ መካከል የሕሊና ጸሎት ይዛ ነበር ።

—2—

ወደዘሮ ደብሬ ፣ ታንጉት አዲስ ሐሳብና ትካዜ ያደረባት መሆኑን ለመገንዘብ ረጅም ጊዜ አልወሰደባቸውም ። እንደ ወትሮው ትጫወታለች ፣ ትሥቃለች ፣ የዕለት ሥራ ታከናውናለች ፣ በመካከሉ ግን ኢሊ በድንገት በራስዋ የድንጋይ ገላ ውስጥ እንደምትገባ ፣ ታንጉትም አንድ ነገር እንደ ረሳች ድንገት ቅዝዝ ፣ ፍዝዝ ስትል የአካባቢዋን የውጭ ዓለምና ሕይወት ትታ ወደ ራስዋ የውስጥ ዓለም የገባች ትመስላለች ። እንደ ልጅ አሁንም አሁንም ትኩር ብለው ለሚመለከቷት ወደዘሮ ደብሬ ፣ በተለይ የሚያሳውቁባት ወደናጅ ናቸው ። ሕይወት የሚፈነጥቁትን ያህል ፣ ተፈት ለፈት ከአንዳች ነገር ሳይ አፍጥጠው እፍ ! እንደ ተባለ መቅረዝ በድን ይሆናሉ ። ወደዘሮ ደብሬ ይህንን ብዙ ጊዜ ታዝበዋል ። የሚያውቁበት ምክንያት አልነበራቸውም እንጂ ፣ የወደናጅ ጸዳል መጥፋት እያዘወተረ የሔደው ከገብርዬ ጋር ተኝታ በሕሊናዋ ብትደልያም በውኑ ያው የተለመደው የሴቶች ፣ ' የሔዋን እርግማን ' የሚሉት ከቀጠለባት በኋላ ነበር ።

ወደዘሮ ደብሬ ፣ ' አንድ ጭንሽ ይሻክራል ፣ ሌላ ጊዜ ጣትሽ ይጐር ባል ' እያሉ የሁለታቸውን ሥራ እንደ መሰላቸው ከዕለት ዕለት ይለዋውጡታል ። አንዳንድ ቀን ' እማማ ደብሬ ዛሬ እኔ ይህን ልሥራው ' ስትላቸው ፣ ' እንቺን ሲያምርሽ ይቅራ ! ታላቅሽ እኔ ነኝ እያደለሁም ? ' ብለው በራሳቸው ውሳኔ የዕለቱ ሥራቸውን ይመድባሉ ። አንድ ቀን እንደ ተለማመደው ገብርዬ ወደ ልጆቹ ጨዋታ ሔዶ ፣ ሁለቱ ብቻ አዳራሹን ይዘው ወደዘሮ ደብሬ በዕለቱ የሥራ ምድባቸው ጥጡን ነድፈው በሰፈድ አቅርበውላት እርሷ ግን የእንገዝቱን ዛቢያ ከባቷ ላይ አሽከርክራ መኻል መንገድ ላይ ስትተው ወይም የከረረውን ፈትል ከእንገዝቱ ላይ አጠንጥና ስትጨርስ ጣቶቿ ቁጥ ሲሉ ፣ በዚህ መኻል ዐይንዋ እንደዚሁ ቦዘዘ ሲል ሲያስተውሉ ከቆዩ በኋላ ፣ '' ኤዲያ ተይው ! '' አሉና ንድፍ ጥጥ የተቆለለበትን ሰፈድ ፈቀቅ አደረጉት ። '' አንቺ ልጅ ምን አማኝ ቶሻል ? ''

''ምን ሆንኩ ? ''



‘‘ ኧረ ኤዲያልኝ ! የሰው ዐይን ውሃው ሲቀየር መቸ አጣሁትና፣ ተገብርዬ ጋር ሰላምም አይደላችሁ ? ’’

‘‘ ኧረ ደኅና ነን ! ’’

‘‘ እዛዲያስ ? ’’

ለነገሩ ከእርሳቸው የምትደብቀው ነገር የላትም ። እንዝርቱን ጣል አረገችና ፡ ‘‘ እማማ ደብሬ ልጅ እምቢ አለኝ ። ገብርዬ ደግሞ ለልጅ እጅግ እየሳሳ ሔደ ’’ አለች በምሬት ፊቷን ጭፍግግ አድርጋ ። የነገራትን ታሪክ ነገረቻቸው ።

‘‘ወይ የግዜር ነገር ! የኔዋን መንቃራ በያመቱ ያስታቅፋታል ። ተማን አባቱ እንደሆነ አውን ደሞ አምስተኛዋን ቋጥራለች ። በዚያው ሰሞን እኔ እግሬ ወጣ ሲል ፡ ልጅ ጋረድ ሲያንጎብብ አይቸዋለሁ ። ተዚህስ ምን ሆኖ ቀረ ልጄ ! ’’ ሲሉ በመካከል ጠየቋት ።

በገብርዬና በእነሱ መካከል የደረሰውን መንገር አልፈለገችም ። ‘‘ እኔ ምናባቴን ዐውቄ ? ’’ አለቻቸው ።

‘‘ወትሮውንስ የወረት አልነበረ ! ... ስለ ልጅ መውለድማ የኔዋ ጉድ እንዴት እንደሚሆንላት ትንገርሻ ! ’’

ታንጉት ከንፈርዋን መጠጠች ። ‘‘ እኔ አንጅቱ እርር ብሏል ። እርስዎ ደሞ ! ’’

‘‘እይዞሽ እንጂ ! በማዘን ብቻ የሚሆን ነገር የለ ። ’’

‘‘ ምን ላርግ ብለውኝ ! ’’

‘‘ ለመሆኑ ውርዴነት አለባችሁ ? አንቺም እሱም ? ’’

‘‘ ምናባቴን ዐውቄ ! ’’

‘‘ የሕግ ባልሽ ነው ። አንቺማ ተየት ታመጭዋለሽ ! እናትሽም የሆኑ እንደሆነ አንቺን በደኅና ወልደዋል ። ውርዴነትም ቢሆን ፡ ደም ይመ ታሽ ነበር እንጂ እንደዚሁ አይተውሽ ! ለመሆኑ ጠበሉን ዎናምነ ሞክረሻል ? ’’

‘‘ በቋራም ፡ በአዳኘ አገርም ፡ በጫቆም ሰሚ ነው የተባለውን ታቦ ትና የታወቀውን ጠበል ሞክሬ ነበር ። ማኅበረ ሥላሴም ፡ ቸንከር ተክለ ሃይማኖትም አልቀረኝ ። ’’

‘‘ የዚህን አገር ደሞ መሞከር ነዋ ! ’’

‘‘ ተሆነልኝም ለምን ኤየሩሳሌምስ አይሆንም ! ’’

‘‘ እሱንስ ቴዎድሮስ ሲዘምት ትደርሽበታለሽ ። ’’

በዚህ ዐይነት ከስሜን እስከ አቸፈር ፡ ከጋይንት እስከ አርማጭሆ ቀዝቃዛውንና ፍል ውሃውን ጠበል ፡ የታወቀውን ገዳም ፡ የበቃ የተ ባለውን ባሕታዊ ያዳርሱ ጀመር ። አውን ያለ ምርኩዝ መራመድ የቻ ለው ገብርዬም ብዙ ሥፍራ አብሯቸው ይሔድ ነበር ። ታንጉትና ወይዘሮ ደብሬ ፡ ‘ ጐንደር ከተማ ከመወዘፍ አገር ማየት አይሻልም ! ’ ከማለት በስተቀር የጉዞዋቸውን ዋና ምክንያት በግልጽ ባይነግሩትም ጠርጥ ሯል ። ሙከራቸውን አልጠላውም ።

ከሩት ጉዞ ተመልሰው ጐንደር በሚሰነብቱበት ጊዘም ፡ የወርባ አራቱን ታቦት በዓል እየቈጠሩ እምነትና ቅብዓ ቅዱስ መቀባቷን ፡ ማየ ቆረር መቅመሷን አልተወችም ።

ታንጉት ፡ በተስፋ እጅግ ከመጓጓቷ የተነሣ ቡራኬ በተቀበለች ፡ ጠበል በቀመሰች ማግሥት የእርግዝና ምልክት የሚታያት መስሎ ይሰማታል ። ምን ዐይነት ምልክት እንደሆነ ግን አታውቅም ። ‘ ሰያ ረግዙ ብዙ ነገር ያምራል አሉ ። እኔን ምን ይሆን ከቶ የሚያምረኝ ’ ትላቸዋለች ወይዘሮ ደብሬን ።

‘ሲደርስ ታገኚው የለ !’ ሲሉ ይመልሱላታል ፡ ጉጉትዋ ልባቸውን እየነካው ። ለእርሷ ሳይነግሩ ለታቦት ተሳሉላት ።

የወር አበባዋ አንድ ሁለት ቀን ያሳለፈ እንደሆነ ፡ ‘ እማማ ደብሬ አውንስ ሊቀር ነው መሰለኝ ! ’ ትላለች ፊቷ በተስፋ እየበራ ። ሲመጣ መልሳ ቅዝዝ ትላለች ።

ብዙ ወራት ዐለፈ ። ብዙ አገር አዳረሱ ። ግን አልሆነላትም ። ገብ ርዬም አብሮዋቸው ብዙ ከተዘዟረ በኋላ ፡ ባይሰለችም ከንቱ ልፋት መሆኑ እየተሰማው ሔደና ፡ ‘እህ ! እንግዲህ መቸስ ስንንከወከው አንኖር ። አባ ታጠቅም መመለሻው ሳይቃረብ አይቀርም ። ጐንደር ብቆየው ይሻ ለኛል ። ታላለው መቸስ ምን ይደረግ !’ አላቸው አንድ ቀን ለሁለተኛ ጊዜ ጐንደር ተክለ ሃይማኖት አንድ ሰባት ሲያበቁ ።

‘ ምኑዋ ! ’ ሲሉ ወይዘሮ ደብሬ ያላወቁ መስለው ጠየቁት ።

‘ አሄሄ ! ምህኛታችሁ ሳይገባኝ ቀርቶ ነው አብሬያችሁ የምንክ ራተተው ! ተሆነልንማ በማን ዕድሌ ነበር ።’

ታንጉት ፡ የቀድሞው ትካዜ እንደገና ተጫናት ። ፊቷ የውቀቀን ዋውልጋት ሰፈነበት ።

‘‘ እውነቱን ነው ገብርዬ !’’ አሏት ወይዘሮ ደብሬ ፡ ታንጉትን ለብ ቻቸዉ ። ‘‘ ይቺ ሁሉ ታቦት ታልሰማ !’’

‘‘ ምን ብበድለው ነው ፈጣሪዬ እንደዚህ የረገመኝ !’’ አለች ታን ጉት ፡ የምሬት ሲቃ እየተናነቃት ።

እንደገና ረግተው ጉንደር ሲቀመጡ ገብርዬ ተስፋ በመቁረጥ ይሁን ታንጉትን እንደሚያውቅታት በመገንዘብ ስለ ፣ ልጅ ማንሣቱን ተወው ። ከመንደር ልጆች ጋር መጫወቱንም ቀነሰ ። በተቻለ መጠንም የደስተኝነት ሁናቴ ያሳይ ነበር ። ይህ ግን ለታንጉት አልበጃትም ። ውስጥ ውስጡን እየበላው ለእርሷ ሲል ስሜቱን እንደ ደበቀ በመገመት ፣ የባሰውን እሳት ላይ እንደ ተጣለ ቋንጣ አንጀትዋ በጎዘን እርር ድብን ይል ገባ ። ሙጥኝ እንደ ማለት ያህል ወዳጅነታቸውን ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ብትፈልገውም ፣ ያ ውብ ጨዋታቸውና ቀልዳቸው ጥርሷን የሚያስገልጣት በስለት እየመሰለ ሔደ ። ዐልፎ ዐልፎ የምታሰማው የሣቅ ድምፅም ቢሆን ፣ እንደ ቅል ኳኳቴ የደስታ ሕይወት የሌለው፣ ከእንገት በላይ መሆኑ በግልጽ ይስታውቅባታል ። ወይም የትዝብት ዐይነት ነው ።

የሐሳብ በሽታዋን በምንም ዐይነት ማጽናናት ሊያቃልሉላት እንደ ማይችሉ ወይዘሮ ደብሬ ሞክረው - ሞክረው ሲገነዘቡ ፣ " ግንኮ ተግብርዬ ይሆን? ይሆናል ምክንያቱ ! " የሚል ሐሳብ አቀረቡላት ።

" ኧረ እሱ እንዳች ጉድለትም የለበት እቴ ! " አለች ታንጉት በግራሚ ማስተባበል ።

" እህ ! ምን ጉድለት አለበት ያልኩሽ መሰለሽ ። ቢሆንማ አልመነኩሽ ! መች አብረሽው ትኖሪ ነበር ። ግና ያም ሆኖ ፣ ዘሩ መካን እንደ ሆነስ ? አለው እኮ የወንድ መካን ። ስለዚህ እኮ ነው ፣ ውርደኔት አለበት ወይ ብዬ ተመጀመሪያው ጠይቂሽ የነበረ ? "

" መካንነቱ ተሱም ሆነ ተኔ ያው ነው ! " አለች በተስፋ መቁረጥ እጅዋን እያወራጨች ።

" መቸም ተሱ ተሆነ . . . . " ንግግራቸውን አንጠልጥለው ተዉት ።

" እህ ተሱ ተሆነሳ ? " የጉጉት ሲታ ያዛት ።

" አይ ! ተይው የማያሆን ነው ። ሞንቶትሽ ቢያስጨንቀኝ ነው እንጂ ! "

" የሚሆን ተሆነ ምናለበት ። "

" ኧረ ባባጃሌው ! ነገርኩሽ ። "

" እኔም ባባጃሌው ይዣዎታለሁ ። ልጅ የሚያስወልድ መላ ታለ ይንገሩኝ ! " ከጉልበታቸው ላይ ተደፍታ ለመለመን የከጀላት ትመስላለች ።

" ይልቅስ ያውራ ዶሮውን ታሪክ ነግሬሻለሁ ? "

" እኔ የዶሮ ታሪክ ምን ይሠራልኛል ። ያመጡትን ይንገሩኝ ነው ያልኩት እንጂ " ስትል ተማጠነች ታንጉት ብሰክሰክ እያለች ።

" እሱምኮ የልጅ ጉዳይ ነው ! እንድዋ እንዳንችው ልጅ እምቢ አላትና ፣ ተቀሚዷ ሥር መዓት ጨርቅ ጉዝጉዛ ባሏን አርግዣለሁ እያለች ስትዋሽለት መክረም ! "

" እህ ! ማታ ሲተኙ አያያትም ? " ስትል ታንጉት ጠየቀች ፣ ድንገት ነገሩ አስገርሟት ።

" ያመኛል እያለች ለብቻዋ እየተኛች ነዋ ! ዘጠኝ ወር ተሞላት በኋላ ምን ታርገው ። አውራ ዶሮዋን አርዳ ደሙን ታልጋው ላይ አፈሰሰችና ፣ ' አስጠረደኝ ' አለችው ይባላል ። ዛዲያ ምን ተብሎ ተዘፈነላት መሰለሽ ። ጌጤ ነው ስሚ እንግዲህ ። " የጌጤ አውራ ዶሮ ዘንድሮ ከበረ ፣ ዘጠኝ ወር ተረግዞ አልጋ ላይ ሠፈረ ። " ወይዘሮ ደብሬ ይህንን ጨዋታ ያመጡት የፊተኛውን ለማረሳሳት ነበር ።

ታንጉት ግን ፣ ጨዋታው ቅንጣት እንዳላማታት ሁሉ ጥያቄዋን አላስረሳትም ። " እኔ ይንገሩኝ የምለው ገብርዬ መካን ቢሆንስ ብለው የጀመሩትን ነው ። ምናለ እርሶማ የልጅ ልጅ አይተዋል ። የኔ ጭንቀት መቸ . . . " ስትል በመከፋት አንገቷን አቀረቀረች ።

" ተይ እንጂ ፣ እንደዚህ አትውኝ ! "

" ዛዲያ ይንገሩኛ ! "

" አይሆንሽም ፣ አትስማሚም ይሆናል ብዬ ነው ! "

" መጀመሪያ ልስማው ። "

" ታልሽ ምን ችገረኝ ። አየሽ ፣ አንድ ልጅ እናቱ ናት እንጂ አባቱኮ በርግጠኝነት የሚታወቅ አይደለም ። አባቱ ማን መሆኑን ምናልባት በርግጠኝነት የምታውቅለት እናቱ ብቻ ናት ። አሁን ለምሳሌ እኔ ልጆቼን ለአባታቸው ልጆችህ ናቸው አልኩት እንጂ ፣ ተሌላ አርግዣቸው ቢሆን በምን ያውቅ ነበር ? እና አሁንም የሆነ እንደሆነ . . . " መጨረሱ የከበዳቸው ይመስል ተዉት ።

ወይዘሮ ደብሬ ፣ እንደ ሠጉት ሐሳቡ ታንጉትን በጣም አላስደነገጣትም ። " እና ለገብርዬ ልጅ ተሌላ ወንድ ላርግዝለት ማለትዎ ነውን? " ስትል ከመገረም ጋር ጠየቀች ።

" አንቺን አርጊው አላልኩሽም ፣ ንገሪኝ ስላልሽ ነው ፣ ባላቸው መካን ተሆነ የሚያደርጉ ሴቶች ግን አሉ ። ወንዱስ ቢሆን የጨነቀው እርጉዝ ያገባል ሲባል አልሰማሽም ? "

" ግና ኃጢያት አይሆንም ? "

" የልብን ሞንቶት አይቶ ባወቀ ይፍረዳ ! ለነገሩማ እንደዚሁስ ይመስለኛል ። "

" እኔ እንጃ ! ተዚያ በኋላ የገብርዬን ዐይን ደፍሬ ማየት የምችል አይመስለኝም ። "

“እሱማ የት ያውቅና ! ”

“ ቢሆንም ሕሊናዬ መውቀሱን ሙች ይተወኝና ! ”

“ እሱማ እንደየስዉ ሆድ ነው ፣ የማይችልለት አለ ። ”

“ እረ እኔ እንጃ ! ” ስትል ታንጉት ራቢን ነቀነቀች ። የሚቀዩ ነገር እንዳየች ፈቷን ሞፍግግ ታድርግ እንጂ እነጋገርዋ የተረጋጠ የመጨረሻ እምቢታ አልነበረም ።

—3—

ታንጉት ፣ በአብዛኛው በራስዋ ሐሳብ ብትዋተም ቴምድሮስ የማ ለባትን እደራ ደግሞ ችላ አላላችውም ነበር ። የንብርዬ ፍላጉት እንዲ ሚላለት ከልብ የምትጨነቀውን ያህል ቴምድሮስም ቅር እንዲሰኝባት አትፈልግም ። ‘ትንሽ ሥጋ እንደ መርፌ ትወጋ’ እንደሚባለው ነው ትላ ለች በሐሳብዋ ። ከሁለቱም በኩል ግልጽ ሆኖ አለመውጣቱ ቢከነክ ናትም ፣ በተለየ መንገድ ለቴምድሮስ ያላትን ፍቅርና አሳቢነት ፣ ብት ፈልግም ከልብዋ ልትፍቀው አትችልም ። ሌላው ቢቀር ‘ እንግች ’ ብሎ በዚያ አስተያየቱ ሲመለከታት ፣ በተለየ ልቡን በእጁ ይዞ የሰጣት ይመስላትና ገና ላልጠየቃት ነገር በሆድዋ ‘ እሺ ! እሺ ’ የሚል ስሜት ያድርባታል ። ከዚህም ጋር ቴምድሮስ ለእርሷ ያለው አስተያየት ከንብርዬ ጋር የምትመሬውን የጋራ ሕይወትም ይመለከታል ። ቴም ድሮስ ለእርስዋ በነ ሐሳብ እስካለው ድረስ ንብርዬ ሊያስከፋት እንደ ማይፈቅድ ይታወቃታል ። የቴምድሮስ በነ አሳቢነት እንዳይቀነሰባት ደግሞ ከእቡን ስላግ አካባቢ ፣ ከወይዘሮ ደብሬ ፣ ከሌሎችም ያነኝች ውን ይዛለት መቆየት ይጠቅታል ።

ከእቡን ስላግ መንበር ፣ የካህናቱ ስብሰባና ምክክር መቀጠል ብቻ ሳይሆን ፣ ቴምድሮስን አድራጉት በግልጽ ወደ መታወም እያመራ መሆኑን ተገንዘበች ። ካህናቱ ለብቻ ከእቡን ጋር ከሚያልቱበት አዳራሽ መቆየት ባትችልም ፣ መስቀል ለመሳለም ስትገባ ብዛታቸውን ታያለች ። ከቤት ሠራተኞቹም አንዳንድ ወሬዎች ትሰማለች ። ታንጉት የተገነዘበችው አዲስ ነገር ፣ አክሊሉ ከእነርሱ ቤት እንደ ቀረ ሁሉ በእቡን ግቢም አለ መታየቱን ነው ። ሁለቱም ሆነ ብለው የተደበቁ ይመስላል ። ሌላው በጉንደር ከተማ የሚወራው ፣ አገው ንጉሤ የሚባል ሽፍታ በስሜን መነ ሣቱ ነበር ። ብዙ ሠራዊት እንዳለው ይነገርለታል ። ጉንደር ውስጥ ሰዎች አሉት ፣ ከካህናቱም ጋር ይላላካል ይባላል ።

ቴምድሮስ ገና በለሳን ሳይሻገሩ ፣ ‘እጨ ቴምድሮስ እጅግ ተዋረዱ ፣ የወሎን ሰው ሁሉ እጅ ነሥተውት ሔዱ ’ ከሚለው ግጥም እንሥቶ ፣ “ምነቢንስ ታጉርሰኝ ምሽቱ ። እቦ እቦ እንትእንስ በምን እባቱ ” እስ እንድ ወሎዬ ተብሎ እስከ ተነገረው ቀልድ ድረስ ፣ በወሎ የፈጸሙት አስፈሪ የትጣት ወሬ ቀድሞ ጉንደር ገባ ። ጉንደር በፍርሃትም በወሬም እየታመሰ ስነበተ ። ቴምድሮስ አካላቸውና መንፈሳቸው የታከተው የሚ ያስመስል የጠወለገ ገጽታ ይዘውለት መጡ ። እንደ ወትሮው ግብር አላ ጠቡም ።

ምናልባት ከእርስዋ ባነጉት መረጃ ብቻም ባይሆን ታንጉት ያየ ችውን ፣ የሰማችውን ፣ የተገዘነበችውን እንዲሁም የመሰላትን በነገረቻ ቸው በሁለተኛው ቀን ቴምድሮስ ካህናቱን ጉባኤ ጠሩ ። ዙፋን ተዘርግቶ በአዳራሹ ውስጥ ሳይሆን መደዛዘርቱም ፣ ጨዋውም ወንድ ፣ በተመልካ ችነት ወይም በወፌ አድማቂነት የተገኘበት የመስክ ስብሰባ ነበር ።

ካህናቱ ግብር እንደ ተጠራ የክት ልብሳቸውን እየለበሱ ፣ ጥምጥማቸ ውን እየከሸኑ ፣ መጅማያቸውን እያዘመሙ ፣ አቡነ ሰላማን እጅበው ጃን ተክል በር ላይ ተሰበሰቡ ። ቴምድሮስ የመር አለቆቻቸውን አስከትለው ከቤተ መንግሥቱ ወጡና ከነሙሉ ልብሱና ከነሙሉ ጥምጥሙ ጋር በረዶ መስሎ የፈሰሰውን ምድረ ካህን ሲመለከቱ ፣ ‘ ይች ቆማጣ ቆመጥማጣ ፊስቁን መምጣሚ ወገቧን ሰባቂ ሁላ አስቸገረችኝ አደይስ ?’ አሉ ከአጠገባ ቸው ለነበሩት የመር አለቆቻቸው ። አቡነ ሰላማ መንበር ተቀምጠዋቸ ዋል ፣ ድባብ ተዘርግቶላቸዋል ። ቴምድሮስ ግን ፣ ትሕትና ይውን መከ ፋታቸውን ለማሳየት ከእሸዋው ላይ ተቀመጡ ።

“ አባቶቼ ምን በይልኳችውና ነው ጀርባችውን የሰጣችውኝ ? ወንጌ እንዲጠላኝ የምትመክሩብኝ ፣ በክፉ የምታነሙኝ ፣ ክፉ የምታስቡብኝ ? የግዘር ሰዎች ነን ትላላችሁ ፣ ዛሬያ ይህን እግዘር ይወደዋል ? ” ሲሉ ዘርጋታ ጠየቁ ።

“ እንደ ጥንቱ ፣ እንደ ዛሉ እንደ ቀደምቱ ነገሥታት ያኑሩን ” አለ አንዱ ተጠራ ደብተራ ።

“ እኩሌታውን የመስቀል መፌት ፣ እኩሌታውን ሪም ፣ ኃጻም እየላችሁ ከመስጻችሁ ፣ እኔ ምን ልብላ ? ሠራዊቴንስ ምን ላብላው ? ” ሲሉ ጠየቁ ቴምድሮስ ፣ ንዴታቸውን እንደ ምንም ግትተው ።

ሌላው ካህን ቀበል አደረገ ። “ እራት መር በጉንደር ተቀምጠው እርግጭሆን ፣ ፀነዲን ፣ ወልታደትን ስሜንን ይብሉ ” አላቸው ።

“ ተዚያስ ? ”

“ እራት መር በዓራንት ተቀምጠው በጌምድርን ላስታን የጀን ወረዳመኑን ፣ ወሎን ፣ ሽዋን ይብሉ ። ”

“ የትቀረውን ? ” የቴምድሮስ እጠያየቅ የትዝብት ወይነት ነበር ።

“ ይባባ ላይ ተቀምጠው ፣ ሚጫን ፣ እገውን ፣ ኖምትን ፣ ጉጂምን መብላት ነዋ ! ”

ቴዎድሮስ ፣ በምሬትና በፈዝ ከት ብለው ሣቁ ። “ ብልጤ ፣ ብልጣ ብልጤ ! ሕዝቤ ሲጠላኝ ፣ ሠራዊቴ ሲከዳኝ ፣ ብቻዬን በሆንሁልሽ ጊዜ እንዳጤ ኢያሱ በሻሽ እንቀሽ ልትገይኝ ! ”

ክርክሩ ከተከፈተ በኋላ ፣ ከካህናቱ በኩል ብዙው እየተደፋፈረ መነሣት ጀመረ ።

“ ንጉሥ በሠራዊቱ ብዛት አይድንም ብሏል ዳዊት ። ”

“ እንግዲያውስ አሮንን ለካህንት ፣ ሙሴን ለመሪነት ለምን መረጠው ? ልጠይቃችሁ ! ”

“ ሁሉም በየተመረጠበት ፣ በየተመደበበት እንዲሠራ ፣ ካህኑ በካህንነቱ ። ”

“ ሠራዊቱም በሠራዊትነቱ ” አሉ ቴዎድሮስ ኮስተር ብለው ።

“ ዛዲያስ ? ”

“ ዛዲያማ እናንተ በሥራት የነበረ አሁን ምን ቀረባችሁ ? ወንጌል ይፋረደኝ ” አሉ ቴዎድሮስ ። ማፋረድ ወይም መፍረድ ሳይሆን እንደ ተራ ተሟጋች እየተነሡ የሚከራከሩት ራሳቸው ነበሩ ። ሠራዊቱና የጦር አበጋዞቻቸው ግን አልወደዱላቸውም ።

“ ለሁለቱም ሥልጣናቸውንና ድርሻቸውን ወስኖላቸዋላ !” አለ አንድ ካህን ተነሥቶ በድፍረት ።

ቴዎድሮስ ፣ አንገታቸውን ደፋ አድርገው በቅሬታ ዋቂት አሰቡ ። ‘እንድም እያለ ነገር ሲበልት ፣ ሲሰንዋቅ ፣ ሲከፋፍል ፣ ሥራ ፈትቶ ተረብ ሲያወጣ ሲያወርድ የሚውል ደብተራን ማን ይችለዋል ? ’ የሚል ይመስላል አስተያየታቸው ። “ ክርስቶስ ዳኛችን ያሁን ” አሉና የሚደማመጡበት የጃቸው ወንጌል እንዲቀርብላቸው አዘዙ ።

“ በፍትሐ ነገሥት ነው የምንፋረደው ” አለ ሌላው ደብተራ እጁን ቀስሮ ።

“ ይምጣ ! ፍታ ነገሥቱንስ ቢሆን ማን ይፈራዋል ! ”

ፍትሐ ነገሥቱ መጣና ፣ በፍትሐ ነገሥት ለታወቁት ለደብረ ብርሃን ሥላሴው አለቃ ተሰጠ ። የደብረ ብርሃን ሥላሴ አለቃ ትልቁን የብራና መጽሐፍ ገለጥ ፣ ገልበጥ - ገልበጥ አደረጉና የሚፈልጉትን አንቀጽ ሲያገኙ ፣ ሌባ ጣታቸውን ከብራናው ላይ ጠንቁለው ጉሮሮዋቸውን ጠራረጉ ። “ ከመቅደስ የገባ አይወጣም ” ይላል አሉ ።

“ ዛዲያን ? ” ቴዎድሮስ ነገሩ ቢገባቸውም ያላወቁ መሰሉ ።

“ ዛዳያማ ፣ ” ሲሉ የአደባባይ ኢየሱሱ የፍትሐ ነገሥት መምህር ተተኩ ። “ መቅደስ የገባ ሲባል ፣ በየሱስ ሥጋ ደም የሚሠየመው ‘ ጎብስቱ ወይኑ ብቻ አይደለም ’ እንደ ጥንቱ ፣ እንደ ጢቱ ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ፣ ለካህናት ሁሉ የዋለው አይቀነስም ፤ አይነካም ። እንደ ጎብስቱ ፣ እንደ ወይኑ ማንም ምድራዊ ሥልጣን አያዝበትም ሲል ነው ! ”

“ አንድሽ አንባቢ ፣ አንድሽ ተርጓሚ ። ” ቴዎድሮስ የቁጣቸው ግንፍላት እየተናነቃቸው እንደ መወሪጨት አሉ ።

“እንግዲህ መቸስ ፍትሐ ነገሥቱ እንደሚለውና ያገርዎ ሊቃውንት እንደ ተረጉሙት ነው ” አሉ አቡነ ሰላማ በማቅማማት ሪዛቸውን እየጐተቱ ።

ቴዎድሮስ፣ አምቀው የያዙት ንዴት ትንሽ ፍልቅ ብሎ ወጣባቸው። “ ብልጤ ብልጣ ብልጤ ! ለነገርማ ግን ብሎሽ ? እርስ በርስሽ ትተካከኪ ያለሽ ። እና ማን ይፈርዳል ?” ሲሉ በመወሪጨት ተነሥተው የተሰበሰበውን ካህን ሁሉ ጠየቁ ።

“ እርስዎ ይፍረዱት ” የሚል መልስ አስተጋባ ።

ቴዎድሮስ ፣ ብዙ ጊዜ እንደሚያደርጉት ሁለት ክንዳቸውን ከወገባቸው አስደግፈው ፣ ያንን ካህን ሁሉ በትዝብት ቃኙት ። በክርክር እንደረቱ ተሰምቷቸዋል ። “ ዛዲያ ምን ላርገው ?” ሲሉ ራሳቸውን ጠየቁ ። ከዚያ በፊት እንደሚያደርጉት ከሆነ የቀራቸው ሁለት መንገድ ብቻ ነበር። በነገር መግባባትና ማሳመን ፤ አልሆን ከአላቸው ደግሞ መምታት ወይ ጥሎ መሔድ ። ከነራስ አሊ ጋብቻ ሆነው ሲያዋርዱዋቸው ለጊዜው ዐቅማቸውን ገምተው ገሸሽ ብለዋል ። በኋላም የዐቅማቸውን ጥንካሬ ሲያረጋግጡ ተጋጥመው ሁሉንም ተራ በተራ መትተዋል ። አሁን ያንን ሁሉ ጠምጥሚ ለመምታት ምንም አያቅታቸውም ነበር ። ነገር ግን ነፍጥ ቀርቶ የረባ ዱላ ካልያዘ ካህን ጋር ይዋጣልን ማለት በጣም መቅለል ሆነባቸው ። ያንን ዕብራዊ ካህን ቢቀጡ ራሳቸው እንደ ዕብራዊ ይታያሉ እንጂ ከጅግንነት አይቁጠርላቸውም ። የነገሩ አጉልነት የባሰውን አበሸቃቸው ። ግራ እጃቸውን ከወገባቸው ላይ እንዳስደገፉ በቀኝ እጃቸው የጉራዴያቸውን ሰደፍ እንደ መነቅነቅ እያደረጉ ፣ “ እንተው ፍረድ ! እኔማ ምኑን አፈርደዋለሁ ? እናንተው ጨርሳችሁት የለ ! እናንተ ከጠላችሁኝ ፣ እናንተው የወደዳችሁትን አስቀምጡበት ። እኔ እንደሆነ እንደ ወትሮዬ እየዘረፍኩ ፣ እያደንኩ መኖር እያቅተኝም ” አሉና በመወራጨት ወደ አዳራሻቸው እንደ መሔድ ሲቃጡ ፣ ዙሪያውን ሆኖ ሲያዳምጥ የነበረው ሠራዊት ማዕበል እንደ ነካው ባሕር አብሮ ተናጋ ። አብዛኛው ካህንም በሁኔቴው መልሶ ተደናገጠ ። የፈለጉት ቴዎድሮስ ፣ ‘ አባቶቼ እንዳላችሁ ፣ እሽ ከፈቃዳችሁ አልወጣም ’ እንዲሉ ነበር ። ‘ የፈለጋችሁትን አስቀምጡበት ። እኔ አድኝ ፣ ዘርፌ እበላ

ለሁ ’ ሲሉ ግን ፣ እምቢታ እንጂ እሺታ አለ መሆኑ ግልጽ ነበር ። የሚዘረፉትስ ያው እነሱው እያደሉ የሚሆኑት ? ገበሬና የእጅ ባለሙያ ንግ አትንኩብኝ ብለዋል ። ቴዎድሮስ ከነሠራዊታቸው ልት ሆነው በአልጋው ላይ ደፍሮ የሚቀመጥስ የት ይገኛል ? እነራስ አሊ እንደሆኑ ደብዛቸው ጠፍቷል ።

‘ ይለመኑን ! ይቅር ይበሉን !’ የሚል ደምፅ እንደ ምሕላ ባንድ ነት እስተጋባ ።

ቴዎድሮስ ተመልሰው ተቀመጡ ። ግን እጅግ የሚጠሉትና የሚጠየፉት ነገር ቢኖር ፍርሃትና ፈሪን ስለሆነ፣ ከካህናቱ የፊተኛው ደፍረት ይልቅ የአሁኑ መርበትበታቸው የባሰ እናደጻቸው ። ‘ ፈሪ ከብር አደገባ ውም ’ ባይ ናቸውና በውርደት ሊቀጡዋቸው ፈለጉ ። “ጠምጥማችሁ ከፊቴ እንዳትቀርቡ ከልክዬ አልነበረም ? ይኸስ ድፍረት አይደለም ?” ሲሉ ወይናቸውን አፈጠጡባቸው ።

ደፍሮ መልስ የሚሰጥ ጠፋ ።

“ በሉ እንጂ ተናገሩ ! ” አሏቸው ። እንደገና ሁለም እርስ በርሱ እየተያያ ጭጭ አለ ።

“ እንተ ፍታ ነገሥት ተርጓሚው ። ስለ ትሽር ጥምጥማችሁ መጽሐፉ ምን ይላል ? መልስ ስጥ” አሉዋቸው የአደባባይ ኢየሱሱን መምህር።

“ እኮ በል !”

“ መቸስ መቸስ ” የአደባባይ ኢየሱሱ መምህር በመቋሚያቸው ጫፍ ወይናቸውን መሬት ላይ ተክለው እንደ ማመንታት አሉ ። “ጥምጥም ክብራችን ፣ መለያችን ነው ። እንደ ችሮታዎ ይበይኑልን ።”

“ ዛዲያ መለያችሁ ፣ ክብራችሁ ተሆነ ከታቦት በገባችሁ ጊዜ ለምን ጥምጥማችሁን ታወልቃለችሁ ?”

“ እሱማ እግዚአብሔር አድሮበታል ብለን ነው !”

“ በኔስ ላይ አላደረም ፣ ”

ማንም አላስተባበለም ።

በጃቸው ወደ አቡነ ሰላማ እያመለከቱ ፣ “አባታችን ፣ የለም ፣ በኔ ላይ ያደረው ይበልጣል ብለው የሚክራከሩኝ ተሆነ መቸስ እሰጥ አገባ አልሚገትዎትም ። ግን ያንድ ሀገር መሪ ደግሞ ያገሩ ተምሳሌት ነው ። እኔም ያገሬ ተምሳሌት ስለሆንኩ ፣ ዋንታዊቷ ፣ ባለታሪካዊቷ ኢትዮጵያ ሀገሬ በኔ ላይ አድራለችና ፣ ፍቅርዋ ጳራቅሊጦስ በልቤ ውስጥ ሠርጿልና ለኔ አይምሰላችሁ ፣ ከበሬታዉ ለርሷ ነው ።”

“ በሉ እንጂ !” አሉ ቴዎድሮስ፣ ጥቂት ከጠበቁ በኋላ መከራከሪያ የሚያቀርብ እንደሌለ ሲገነዘቡ ። ብዙው ካህን ነገራቸው አልገባውም ። ጥምጥምህን አውልቅ የተባለ መሰለውና ሠራዊቱ ተሰቆ በዱላ ሳይዝ ልጠው ወይም በጉራዴ ሳያወሪ ርደው ፣ አንዳንዱ ውሉን እየፈታ ይተረትር ፣ ሌላው እንዳስ ከሞንቅላቱ ላይ እየመዘዘ በጉያው ይሸጉጥ ጀመር። መላጣ ፣ ሽበታም ፣ ከምከሞ ፣ ዐልር ዐልርም ለምጥና በሽታ የወረሰው ራስ መጋለጡ እየበረከተ መሔዱን ቴዎድሮስ ሰ መለከቱ ቅር አላቸው። ‘ ጥምጥም ስንቱን ጉድ ሸፍኗል ’ አሉ በሆዳቸው ።

“ እኔማ ሥራት ላሰተምራችሁ ብዬ ነው እንጂ ተሆድ ያልሆነ ከበሬታ ምን ሊጠቅመኝ ? ጥምጥማችሁ ምን ሊጐዳኝ ? ራሳችሁ ተገለጠናስ ምን ሊረባኝ ? እንዳፈቀዳችሁ ሁኑበት ” አሉ በመታከት መልክ እጃቸውን እያወዛወዙ ።

ካህኑ ሁሉ ፣ እንደገና ጥምጥሙን እያስተካከለ ለመበተን ሲል ለወረደው ዕርቀ ሰላም ማሳረጊያ ግብር ታደመ ።

ግዎሽውን በሥራ ከፍላቸው ለማናገር ሲያስጠሩዋት ለፊተኛው ዐይነት ጉዳይ መሰላትና ታንጉት የተለያየ ሐሳብ መጣባት ። ‘ ሊያመሰግኝ ነው፣ ወይንስ ለወደፊቱም እደራሽን ሊለኝ ? የእነ ጋረደና የገብርዬን ነገር ሰምቶ ለምን ደበቅሽኝ ብሎ ይጠይቀኝ ይሆን፣ በምን ያውቃል ? ማን ይነግረዋል ? ገብርዬ እንደሆነ አልነግረውም ብላ ። ዛዲያ እኔስ ብሆን ገብርዬ እንደዚህ ያለ ሕልም አየብህ ብዬ መንገር ነበረብኝ ?’

“ ቁጭ በይ እንጓች ” አሏትና ጎዘን ይሁን ቅፌታ በሰፈነበት አስ ተያየት ተመለከቷት ። “ ይኸውልሽ ተንከራተት ብሎኝ ነገ ደኅሞ ወደ ጐጃም መዝመቴ ነው ! ገብርዬን ይዤብሽ ! ”

“ ወትሮስ ቢሆን ተኔ ጋር ቁጭ ብሎ መኖር አለመደ ” ስትል መለሰች ። ለዚህ ፍሯል የጠራኝ እያለች በሆድዋ ።

“ተመነሣቱ በፊት ግን ፣ ነገ ጧት ተተዋበች ጋር ልንቆርብ ነው!” አሏት በድንጉት ።

ታንጉት ፣ የምትናገረው ጠፍቷት በመገረም ብቻ አፍዋን ያዘች ። የቴዎድሮስና የተዋበችን ፍቅር ፣ እንኳን እርሷ የቅርቧ ቀርታ አገሩ ሁሉ የሚደነቅበት ቢሆንም ፣ ያቆርባሉ የሚል ግምት በሐሳብዋ መጥቶ አያውቅም ።

“ እም ! ተዋበች ተኔ ጋር ስትንከራተት ጢናም እያጣች ሔዳለች ። በዚህ ላይ ልጅ የላት ! ”



‘እኔስ ብሆን የታለኝ’! ሲል ሆድዋ የጮኸ መስሎ ተሰማት ።

“እና ፣ ባንድ በኩል ትንሽ መጽናኛ ቢሆናት ብዬ ነው ” ሲሉ ቂም ድርስ ቀጠሉ። “ዕድሜዋን ታረዘመልኝ እኔእንግዲህ ተዩ, ሌላ አልመኝ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ፣ስሌላው ምላሌ የሆንኩ መስሎኝ ነው ። በምግባር ፣ በጠባያም ፣ በጭዋነትም ፣ በትዳሩም ሆነ በሥራ እንዲያው በማን ኛውም ነገር እኛ ሆነን ታላላየነው ፣ ሌላዉን ‘ይህን አታድርግ ፣ ይህን አትሥራ’ ብለን ብንመክረው ብንገሥጸው ም ን ብሎ ይሰማናል ? ለምንስ እንፈርድበታለን ? ስለዚህ እስቲ ተኔው ልጀምር ብዬ ነው ። ገል መቸም ያው ዐይኑየሚያርፍባትን አላገኘም ።” ታንጉት ፣ ‘ወይስ በዘራዎ ከንያት እሺ የምትለው አግራ አላገኘም ?’ የሚል ጥያቄ በሐሳብዋ መጣባት። “ዓለሚና ሴሎች ግን ፣ነገ ተኛው ጋር ሲቆርቡ ነው ። ‘እኔእንደሆነ አግኝቸው ነው ! በኋላ አባቸው ተኮንነው እንዳያበሰንኑኝ እንጂ ! ’ እያ ለች ትንሽ እንዲያ እንዲህ ያለችው የጉንደሬ ጠባይዋ ገና ያለቀቃት የእንግዳ ሚሽት ናት ። ተሁለቱ የትኛቸው እውነተኞች ይሁኑ እኔ ወላ ውቅም ። ለሁለም እነሱም ነገ እንቆርባለን ብለዋል ።” ቂምድርስ በማ ሰብ ዐይነት ንግግራቸውን ገታ አደረጉ ።

ታንጉት ፣የሚቀጥለውን ለማወቅ ከመጓጓቷ የተነሣ ከመቀመጫዋ እስክ መነሣት ቃጣት ። ለቅጽበት ስሚታን ያነጠረው እና አሁንም ‘አን ቺና ገብርዬ እንደሚኖሩ እንደ ሌሎቼ ሁሉ’ የሚለውን ጥያቄ ለመስማት ነው፣ እሽታዋን ከአልፅታ ባላነሰ ሰሚት ለመመለስ መላ ሰውነታ እንደ ሙር ተሰበቀ ፣ እንደ ቀስት ተወጠረ ፣ በሐሳብ ሲያስጨንቃት ለኖረው የልጅ ጉዳይ አንድ የማታለያ ተሰሩ ብልጭ ብሎባት ። ገብርዬ ከርሰዋ ልጅ አለ ማስወለዱ እሱንም እያንም የሚያሳዝን ቢሆንም ፣ ጋብቻቸው ፍቅሬ ራል ። ገብርዬም በጉን ከሌላ ሴት የመውለድ ሐሳብ ከነበረበት አከተመ፣ ወይዘሮ ያብሬ እንዳሉት ራሱ መኸን ካልሆነ በስተቀር ። ግን መሆነን በዋ ን ያውቀዋል ! ከእርሰዋም ቢሆን እያያረ ተሰሩ ቄርጦ ከጊዜ በኋላ ይረሳው ይሆናል ። የቆረቡ ባልና ሚስቶች በዓመት በዓሉም በጌሙ ሌላውን ነገር እንደሚተዉት ሰምታለች ። ወይ ደግሞ ከጊዜ በኋላ ከቆ ርበናቸው ጋር ጀም እሱቱን ካጠነከሩት እሱ ባወቀ መርቆ ዘር ይሰማ ቸው ይሆናል ፣ ማን ያውቃል !

“ አንቺና ገብርዬ ” የሚሉት ቃላት ከቂምድርስ ሲወጡ በአንጻኛ ዐይነት ሰሚት መዋቃ፣ ‘ግን ’ የሚለው ተከታይ ቃል እንደ መብረቅ መታት ። ቂምድርስ ዐረፍተ ነገራቸውን እስኪጨርሱ መጠበቅ አላስ ፈለጋትም ። ‘ ግን ’ የሚለው አንድ ዐይነት ቃል እንደ ቦር ተሰክባት፣ ቂምድርስም በዚያው ቅጽበት የሁሩቂዋን መለወጥ ተገንዝበው ንግ ግራቸውን አቋረጡና በመገረም አተኩሩ ። “ምነው ተንደኞችሽ ላለመ ለየት መቁረብ ትረልጊ ነበር ?” ሲሉ ጠየቋት ፣ ሰሚታ የቅሬታ መሆኑ ወዲያው ገብቷቸው ።

“ እረቲ ! አንተ እንደ መሰለህ !” ሰትል መለሰች ድምፅዋም ፣ ገጽ ታዋም የምትናገረውን በግልጽ እያስተባበለባት ።

ቂምድርስ ፣ ፊታቸውን በመጻፋቸው እየፈተጉ ቁንጻላቸውን እዬ ጉተቱ አሰቡ ። ሰለ እርዩ እንደርዩ, በመጪነት ፊታቸው ተጨፈገገ ። “ ምን መሰለሽ አንቺች ” አሉ በሚያባብል ድምፅ። “እንደውነቴ ተሆነ እኔ ተገብርዬ የቀረበ ወንድም የለኝ ። አንቺም ተሱ የሚሻል ባል አታ ገኝም ። እናንተ ያልቆረባችሁ ግን ይቆርብ ነበር ። ዛሂያ እንደምታው ቂው ገብርዬ የጠር አዝማች በመሆኑ ፣ ታንቺ እየተለየ ተብዙ አገር ተብዙ ዘመቻ መሔዱ የግዴተር ነው። ወንድ ልጅ ስሪጀም ጊዜ ተቤቱ ሲለያ ደግሞ መቸበ ። እና በዚህ ላይ ደግሞ አንቺም እንደ ተዋበች እሰተ ዛሬ ለልጅ አላያለሽም ። እኔ መቸም እንዳልኩሽ ተዋበች ልጅ ብትሰጠኝ ያስታውን አልችለውም ነበር ። ታልሆነ ግንነየወንሬ ልጅ ሁሉ ልጂ ነው ብዬ እጽናናለሁ ። ገብርዬን ግን እንደኔ ሁን ማለቱ ይከብደኛል ። ልጅ እንደሚወድ ዐውቃለሁ ። ለኔ ሲል እየተጋደለ በዘህ ላይ ታለ ዘር ቅር ማሰቱ እጉል መጨከን መሰሎ ይታየኛል ። ስለዚህ የሁለታችሁ መቁ ረብ ቢቆይ የተሻለ መሰሎኛል ። ”

ታንጉት ‘ እ ! ’ የሚል ድምፅ ብቻ አሰማች ። አጥንት የተሰነቀ ረባት ያህል ጉርርዋን ተናነቃት ። አነጋገራቸውን ምክር ያከመሰሉት እንጂ ውሳኔ ወይም ጎጉዛዝ መሆኑ ገብቷታል ።

“እንቺም ብትሆኝ ገና ልጅ ነሽ ፣ይቆይሽ ! ” አሉ ጉዳዩን ለማቃ ለል በቀልድ መልክ ።

ታንጉት የምትናገረው አልነበራትም ። የምታስበው ሳያቆር ጠፋ ባት ። አእምሮዋ ድንገት ባዶ ሆነባት ። በደመ ነፍስ እጅ ነሥታ ወጣች ።

በበነጋው ጧት ፣ በደብረ ብርሃን ሥላሴ የቅዳሴውና የቁርባኑ ሥነ ሥርዓት ተካሒደ ። ከጨለማው ጋር ተፋጥጣ አብዛኛውን ሌሊት እን ቅልፍ ሳያወስዳት ያደረችው ታንጉት ወትሮ ይመስጣት ፣ መንፈስ ቀን ወደ ተረጋጋ ዓለም ይስብላት የነበረው ቅዳሴ አሁን የሚያስጠላ ልቅሶ ሆነባት ። ከዘማው እስከ ቃሎሱ፣ ከጧፉ እስከ መንፀላዕቱ ሁሉም ነገር አስጠላት ። ሥነ ሥርዓቱ እንደ አንድ ዓመት መከራ ረዘመባት ። ከሁሉም ያሠቃያት ፣የውስጥ ሰሚታን ፣ ሌሎች በተለየ የሚቆርቡት መለሎጂ እንዳያውቁባት ለመደበቅ የምታደርገው መጪነትና መጠበብ ነበር ። ገንፍሎ ለመውጣት የሚተናነቃትን ልቅሶ አምቃ ይዛ በሹክ ሹክታ ሲያንጋግሩዋት መመለስ ፣ ፈገግ ሲሉ አብራ ዋርያን መገልፈጥ ነበረባት ። ድርብ ሥቃይ ነበር ።

እንዳያልቅ የለም ሥነ ሥርዓቱ አለቀ ። የታንጉት መከራ ግን አላ ለቀላትም ። ገብርዬና ታንጉት ፣ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ሲያርሱ

ከክብቶቻቸው ወርደው በመሳለም ሰዎቻቸውን አስቀድመው ታንጉት ከአንድ ነገር የምትሸሽ ይመስል ፣ ከአረማመድዋ ፈጠን ፈጠን እያለች ገብርዬ የመንገድ ጓዙን ለማዘጋጀት የተጣደፈች መስሉት ፣ ሰለ ጉዞው እያሰበ በእግራቸው ትንሽ ኤልፍ እንዳሉ ከጋረድና ከአክሲሉ ጋር ደን ገት ተገናኙ ። እነ ጋረድ እንደ አጋጣሚ ያስመሰሉት እንጂ ፣ ትክክለኛውን ሁናቴ ለማወቅ ያብረ ብርሃን ሥላሴ ቆይተው ፣ ሥጋ ወደሙ እንደ ወረደ ቀደም ብለው በመጠጣት ፣ ሆነ ብለው መገጣጠሚያ ላይ ጠብቀ ዋቸው ነበር ።

በግዕጽ እንጻልተጣሉ ባላጋሪዎች የመተፋፈር ሰላም ተሰፋ ወጡ ። ታንጉት ተሰይታ ወደ ፈት ቀደም አሰች ።

"ምነው ጠፋችው ? ባገር አላችው እንዴ ?" አለ ገብርዬ የመዉረሻ ቀን ዉውታቸውን የሚያስታውስ በሚመስል ትዝብት ።

"የዜመት አንሩን ልናደ ወደ ወገራ ዉጥጥን ነበር " ቢል አክሲሉ መለሰለት ።

"እረ ! አልሰማሁም ነበር " ብሎ ገብርዬ ተሰናብታቸው መነ ዴን ሲቀጥል ቢል ፣ እነርሱም ወደ እርሱዉ እንጣጫ ታጠሩ ።

"ምነው ተሰይታችሁ ቀረችሁ ?" ሲል ኑክሲሉ በፈገግ ዐይነት ዐይነን አዉንቁር እያተመሰከተ ጠየቀው ።

"ተሞነ ?" ገብርዬ ያላወቀ መሰለ ።

" በተክለል ተመታሰሩ ነዋ ! 'ተክተል አስታሆን' ተብሎ የለም"

" መታሰር ማን ያስ ይለዋል ?" አለ ገብርዬ ነገሩን አቃልሎ እንደ ሙተው በማድረግ ።

" እንተነህ እይ እሰራሁን የፈራችሁት ? ያናራችሁ በምትባሉበት ገዜ ግን እኔ ያብር ሎዛ ማርያም ነው የማቆርባችሁ ። "

"ለዘያ ያብቃን " አለ ገብርዬ ። አንድ ዐይነት ሥውር አሸሙር ያለበት ዉዋታቸው አልተም ብሎት አመለየት አረማመዱን አፋጠነ።

" ምን ታወራለህ ተነሱ ጋር ደሞ ?" ሰትል ታንጉት ከሰተር ብላ ጠየቀችው ፣ አድሮ ያረፈደ እምት በማታ ምክንያት እንደለገ ።

"ሰላም ሲሉኝ ዛዲያ ዝም ብያቸው ልሰፍ ?"

"ዛዲያ የግዜር ሰላምታ የሚያሣጭ ነገር አለበት ?" ሆን ብለው መንገዱ ላይ እንደ ተጠባበቁዋቸው ከገብርዬ ይልቅ ታንጉት ጠርተራ ነበር ።

"አይ ! ለምን በቁርባን አልታሰሪችሁም ብለው ቀላለዱ ። "

" እና ፣ ምናልክቸው ?" ካለወትሮዋ አጠያየቅዋ የማሩጠጥ ዐይነት ነበር ።

" መታሰር ማን ያፈልጋል ነዋ !"

ውጋት ንዝር እንዳያረጋት ያህል ፣ 'እሱ !' ብላ እንደ ፉሙር እየ ተያናበረች ወደ ቤትዋ ገሠገሠች ። አሁን የገብርዬ እንደ ቃል ሰበብ ሆኖ ያስገነፈሰባትን ፣ ሲተናነቃት የቆየውን ሠቀቀን ብቻዋን ሆና እስገነፈሰ ታወጣው መድኃኒት እንደ ቀመሰ ሰው አጣደሩት ።

ገብርዬ ፣ ሰገዚው ታንጉት ያበሳጫትን ትክክለኛ ምክንያት ያጎ ምች እንጂ ፣ የሠቀቀንዋን ዋልቃት ፣ የሥቃይዋን ክብደት አይተንበት ። ሲገነዘብ የሚችልበት መንገድም አይነበረም ። ሌሎቹ እንዲቆርቡ መጠየቃቸው ፣ እነርሱ ግን እንዲቆዩ ለታንጉት የተነገራት መሆኑን ፈጽሞ አያውቅም ነበር ። ሌሎቹ መቁረባቸውን ያጠቀው ጣት ሲቆርቡ ነው ። ቂዎድርዘን ለማስያዝ ወይም ሥነ ሥርዓቱን ለማደመቅ ሲሉ ለየራሳቸው አስበው በፈቃዳቸው ያነረጉት መሰለው ። ንብር መሰፋሩን ባያጠላው ፣ ተለያተው መቆረቃቸውን ያማም ክባይ ግምት ውስጥ አላስገባም ። በፈጹ ያማም እዚያው ተነሥተው መቁረብ አያችሉም ነበር ። ታንጉትን እንደ ሌጀችው የያሩለት ቂዎድርስ ናቸው ። አሰቀድሞ ግማኩር ፣ የማደግሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ እንደለበት ያውቀዋል ።

ገብርዬ ፣ ተኳቃትሎ ቤት እንደ ያረሰ እንደ ዋዛ ታንጉትን ያጋግሞ በማሪ ጎዳ አደናጣ ዝም አሰችው ። ከጥቂት ገዜ በኋላ የሚጠሩ ገዜ ያሚ ቅሬታ እንደሆነ አድርጎ በመገመት ፣ ' እስቲ ይሰናሳት ! ' አለና በሆዱ ፣ ልጓዜ አሰረሽነት ተወው ። ከዚያም የኩርቻ ከብቱን ያረጎንት መሪዎር የሚያዘውን ገዝ ሲፈታ ትሸ ከቆየ በኋላ በተ መንግሥት ሐዲ ።

ታንጉት ፣ ብርቱ ቁርጠት እንዳመመው ሰው ከሥር በእጅዋ ሙላዋ አድርጋ ይዛ ፣ ከአልጋው ላይ በሆድዋ ተኝታ ነበር ወደ ዘር ያላሬ ያዋን ቀት ። በሠርቅና በትሪስ መኝል የተቀበረ ፈቷን በእገዋዋ መለስ አደ ረገና ችኩር ብለው ተመለከቷት ። ቀደም ሲል መላ ሰውነቷን እንደ መር እየሰበቀ ያንሰቀሰቃት ልቅሶ ፣ በኋይል ተጎናፋ እየተነፈሰ መሚሸሽ እንደ ጀመረ ፈሯ ጋብ ብሳል ። ዕንባዋም ቢዘን እንዳባራ ዝናም ጠፈኖ ግሰት ይዛል ። የፈሰሰው ዕንባዋ አሥዎሮ ነተወው የጎንጭ ፈር ጋር ጠቅላላ ፈቷ እሳት እንደ ገረፈው ብራና ተኩማትሯል ። ዐይኖዎ በርበሬ መስለዋል ። የጎንሮዎ ሰርጉዶች ጠፍተዋል ። ያ ሙሉ ገጓጭ ተንገ ርገፀ እንደ ቆየ ጥሬ ወደ ውሰጥ ተመዋጧል ። "ኡሎ ! ምን እየሆንሽ ነው ፣ እረ ባባጀሲው !" አሉ ወደ ዘር ያብሬ በእናት ዐይነት ቁጣ መነ ዉት ማድረግ እየቃጡ ። ጥያቂ አልነበረም ። የቁርባንንና የቆራቢዎችን ወሬ እንደ ሰሙ ተጠራጥረው ነበር የመጡት ።

“ እሺ እደርገዋለሁ ! ” አለች ታንጉት ፣ የኮሶ መድኃኒት ድንገት ለመጨለጥ እንደ ደፈረ ሰው ዐይነት ድንገት ተወራጭታ ።

“ ምኑን የእኔ ልጅ ?” ሲሉ ጠየቁ ወይዘሮ ደብሬ ፣ ምን ማለቷ እን ደሆነ እያወቁ ትከሻዋን ዕቅፍ አድርገው በማባበል ።

“ ስለ ልጅ መውለድ ያሉትን ! ” አለች አሁንም በኃይለ ቃል ።

“ እሺ ! እሺ የኔ ልጅ ! ” አሉ ፣ እንደ ሕፃን ትከሻዋን ዕቅፍ እድ ርገው እንደ ዐቅፏት ።

“ አደርገዋለሁ እኮ አልኩ ! ” እነጋገርዋና አስተያየቷ ሁሉ የን ጫድ ቅዠት ይመስል ነበር ።

“ እሺ እኮ አልኩሽ ” አሉ ወይዘሮ ደብሬ ፣ አሁንም በማባበል ትከ ሻዋን በመዳፋቸው ሙታ ሙታ እያደረጉ ።

“ እሺ መች ! ”

“ እረ ዊኒኤሌው ! ቆዲያ ቀስ ብሎ ረጋ ብሎ ነው እንጂ ! ”

“ እንድ ጊዜ ! እንድ ጊዜ ! ” ታንጉት እንደ እንቆቅ እንድ ጊዜ ቋንቋ እድርጋ ስትውለው ታያት ።

“ ቆዲያ እንድ ጊዜ ቢሆንስ ? ድግሞ ዊደሆንስ ? ለውስጡ ቁጭ ርስ ብሬ መሄሙሉ እደደለም ? ነብርዬስ እብር ሌያጅ እደደለም ? ”

“ እሱማ ነው እንግዲህ ። ”

“ እረ ባባጂሌው ! ጅል ፡ ጅላ ጅል ነሽ ልበል ! ” አሉ ወይዘሮ ደብሬ ከብግጫ ያልት በመነሪም ።

“ ምነው ?”

“ እህ ቆዲያ እርግዘሽ ልትቆይው ናሪል ? እንድያውን ባቀጅ ጉዴን ዕወቁልኝ ማለት አይቻልም? ”

ታንጉት ገባት ። “ እሺ ሊመለስ !”

—4—

ታንጉት ፣ እንቆቅዋን ለመጨለጥ አንድ ጊዜ ብትወስንም ፣ የነብር ዬን ከጉጂም ዘመቻ መመለስ ሲጠብቁ ፣ ጉቶው ሁሉ አውሬ እንደሚ መስለው የጨለማ መንደኛ ብዙ ዐይነት ጥያቄ እየፈ ደቀነባት ሐሳ ብዋ መለስ ቀለስ ማለቱ አልቀረም ነበር ።

“ እረ እማማ ደብሬ ! አባትየው በኋላ ምሥጢር ቢያወጣስ ?” ትላቸዋለች ።

“ በምናባቱ ዐውቆ ?” ሲሉ ይመልሱላታል ።

“ ገብርዬ እኔን አይመስልም ብሎ ቢጠራጠርስ ? ” ስትል ትጠይ ቃቸዋለች ።

“ ልጅ ሁላ አባቱን ይመስላል ያለሽ ማነው ? ‘ማጅራቱ አባቱን ይመስላል ’ እየተባለ ሲተረት አልሰማሽም ?” የሚል መልስ ታገኛለች ።

“ እንዲያው ለመሆኑ ያደረግነውን ሰውየው ቢያወራብኝስ ?”

“ ማዲለሽም ። ለኔ ተይልኝ መላውን ። እንኳን እሱ እንቺም ማን መሆኑን እንዳታውቂው እናረጋለን ” ሲሉ ያጽናኑዋታል ።

“ እንደዚያም ሠርቶ ያልሆነልኝ እንደሆንስ ? ጳግሜኝስ የምሞ ከረው እይመስለኝም !”

“ የሱ ፈቃድ ተሆነ ዘርና ዕውቂያ እንድ ቀን ተብሏል ።”

“ ውይ እማማ ደብሬ ፣ እኔኮ የሴላ ወንድ ጠረን አላውቅም ! ”

“ ላንዳፍታ እንደ ምንም መቻል ነዋ !”

ነብርዬ ፣ ከሁለት ወር ያህል በኋላ ተመልሶ ጉንደር እስኪመጣ ፣ ወይ ዘር ደብሬና ታንጉት ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ጥያቄዎች በመካከላቸው በማንሳት መልሱን ተነጋግረውበት ነበር ። ነብርዬ ከመጣ በኋላ ፣ “ሐላ ብሽን ታልቀየርርና ይውን ታልሽ እንግዲህ መጀጋጅት ነው ”እኔ ወይዘሮ ደብሬ የመጨረሻ ውሳኔዋን ጠየቋት ።

“ እሱንማ ሠርጀን የለ !”

“ እንግዲያው በወራሽ በስምንቱ ቢሆን ነው የማይስተው ” ሲሉ ትክሚውን ጊዜ ገለጹላት ። የወር እበሳዋን ማለታቸው ነበር ።

“ ለመሆኑ ሰውዬው ማነው የሚሆነው ?” ታንጉት ማወቅ ባት ፈልግም ማንነቱ ከንከናት ።

“እረ ባባጂሌው ! እንዲት ተዋወቁ ነው የሚሆነው ብየሽ ! ለሕ ሊናሽም ፣ በኋላ ለልጁም ጥሩ አይሆንም ” ነጣለት መለሱላት ።

በተስማሙበት የቀጠሮ ቀን ቡን እየተጠጣ በዋዛ ፈዛዛው ጨዋታ መክክል ወይዘሮ ደብሬ ፣ “ነገ የጊዮርጊስ ዋዜማ ነው ። የአምባ ጊዮር ጊስ የሚነግሥበት እና ለመሳለም ም ፣ ዘመድ ለመጠየቅ ከለም ሔድ የምት ፈቅድ ተሆነ ታንጉትን ተኒ ጋራ ልውሰዳት ” ሲሉ ገብርዬን ጠየቁት ።

“ እረ በመድኃኔ ዓለም ! አሁን ማን ይሙት የትም ስትዞሩ እኔን ወይቃችኋል ?” አለ ገብርዬ ነገሩን በማቃለል ።

“ ድንገት ያደርገም እንደሆነ እንዳታስብ ብዬ ነዋ !” አሉ ወይ ዘሮ ደብሬ ፣ በተመሳሳይ የሚቃለል አነጋገር ።

ታንጉት ፣ ወደ ጎንደር ተመልሳ በአምባ ጊዮርጊስ የሆነውን ሁሉ እንደገና ስታስበው የሚታያት እንደ አንድ ሕልም ነው ።



. . . . አምባ ጊዮርጊስ ሲደርሱ ከመንደሩ ዳርቻ ላይ አንድ ትልቅ ፣ ሁለት ትናንሽ የሣር ቤቶች ወደ አሉበት አንድ አጥር ግቢ አመሩ ። አስቀድመው የወሰኑ ወይም የተሰናዱበት ይመስል ፣ ታንጉትን ከአንደኛው አነስተኛ ጐጆ አስገቡዋት ። ወይዘሮ ደብሬ ወደ ትልቁ ቤት ሔደው ከጥቂት ጊዜ በኋላ የነብስ ቆሎና ኮረፌ ጠላ ራሳቸው ይዘው ተመለሱ ። “ እንግዲህ ከዚሁ ቆይ ፣ ግንም አያስቸግርሽ ፤ እኔ ቤተ ክርስቲያን ተሳልሜ ልምጣ !” በማለት ብቻዋን ተዋት ። ጊዜው አልገፋ ብሏት ጣራና ግድግዳ ስትቆጥር ፣ የኩታዋን ጫፍ እየተረተረች እንደገና መልሳ ስትቋጭ ቆየች ። ውሎ መሰላት ። እንደዚሁ ከመጠበቅ በስተቀር የፍርሃትም ይሁን የጉጉት አንዳችም የለየለት ሐሳብ አይሰማትም ነበር ። ወደ ማታ ገደማ ወይዘሮ ደብሬ እንደገና ሲመጡ ፣ እንጀራ በክክ ወጥና አረቄ ይዘው ነበር ። ‘አይዞሽ’ አሏት ያመጡትን እያቀረቡ ። “ ኮረፌው ብቻ ሆድሽን ይነፋዋል ፤ አረቄውን ጠጭበት ፤ ደሞም ፍርሃት ሽን ያጠፋልሻል ፤ ” ሲመሽ ‘ በይ እንግዲህ ዐረፍ በይ ’’ አሉና በጨለማው ውስጥ ብቻዋን ጥለዋት ሔዱ ። አውን ልብዋ ክፉኛ ይመታ ጀመር ። ካለ ዐመልዋ አረቄውን አንድ ሦስት መለኪያ ስትጠጣለት ሞቅታ ተሰማት ። ‘ ምናለበት ! ’ ስትል ራሷን አደፋፈረች ። ከትልቁ ቤት ጠበል ጠዲቅ መኖሩን የሚያበሥረው የሰዉ ሁካታ እየቀነሰ ሔዶ ጨርሶ ሲጠፋ ታንጉት መቀነቷን ፈታችና ከጠፍር አልጋው ላይ ተጋደመች ። መጀመሪያ የሰው ድምፅ በሩቁ ሰማች ። ጆሮዋን እንትታ ስታዳምጥ ዲክ ፣ ዲክ የሚለው ኩቱ እየቀረበ መጣ ። ገርበብ ብሎ የነበረው በራፍ ሲከፈት በውጭው ደብዛዛ የከዋክብት ውጋጋን የሰውዬው ቅርጽ ጥላ መስሎ ታያት ። ትንፋሽዋን ያዝ አደረገችው ። ልብዋ ደረትዋን ተርትሮ የሚወጣ መስሏት ነበር ። ከአልጋው ጠርዝ ተቀምጦ ልብሱን ሲያወላልቅ ፣ ‘ ምነው ዛሬ ይህንን አረቄ ዝም ብላ ጋተችኝ እባካችሁ ! ’ አለ ሰውዬው ከራሱ ጋር ፣ መጠጥ ትንሽ ባሰረው አንደበት ። ከአልጋው ላይ ወጥቶ ሲጋደም ነበር ሌላ ሰው መኖሩን ያወቀው ። ‘እህ !’ አለ በመገረምም በመደንገጥም ። ታንጉት እንቅልፍ የወሰዳት መስላ ዝም አለች ። ለማረጋገጥ በእጁ ዳበስ ዳበስ አድርጎ ቁንዳላዋን ሲነካ እንደ ገና ‘እህ’ አለ ። ‘ ተነሥቶ ይሔድ ይሆን ? ’ የሚል ሐሳብ መጣባት ። ግን አልሔደም ። የጋለ ሰውነቱ ተጠጋት ፤ በእንቅልፍ ልብ ዐይነት አስተኛገደችው ፤ ዶሮ ሊጮህ አቅራቢያም ሁለተኛ ጊዜ እንደዚሁ ። ታንጉት ባትደሰትበትም እንደ ፈራችው አላስፈራትም ፤ አልቀፈፋትም ፤ የሰው ዐይን ለማየት የፈራ ይመስል ገና ወፍ መንጫጫት ሲጀምር ተነሥቶ ሔደ። ቀይ ይሁን ጥቁር አላየችውም ፤ እሱም አላያትም ፤ ከረፋዱ ላይ ወደ ጐንደር ተመለሱ .....

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ፣ “እማማ ደብሬ መሆኑ ነው መሰለኝ!” አለቻቸው ፣ የደስታ ፈገግታ እያሳየች ።

“ እሰየው ! እሰየው ! ስሉቱን አስገባለኋ ! ” አሉ ወይዘሮ ደብሬ ፣ እንደ ልጅ መፈንደቅ ቃጣቸው ።

“ ይኸው አራት ቀን ዐለፈኝ እንግዲህ ። ለጉብርዬ ልንገረው !” ስትል በጥርጣሬ መልክ ጠየቀች ።

“ ትንሽ ቆይ ፤ ያደርስሻል !”

“ግን እንዲያው እንዳችም ፍንጭ አይወጣም ብለው ነው ? ”

“ በምን መንገድ ። እኔን እንጂ አንቺን አላየሽ ! ግን መሆንሽን ዐያውቅ ! ደፍሮም አይናገረው እንጂ ! ” በጥያቄ አስተያየት ተመለከተቻቸው ። “ዲያቆን ነበራ !”

“ ምን ? ” ታንጉት በመብረቅ እንደ ተመታ ክው አለች ።

“ አይዞሽ አትደንግጭ ! ግፍረሱም የማይቀር ነበር ። ” ታሪኩን ነገሩዋት ። “ ሦስት ልጆች የወለደችለት ሚስቱ ከሞተች ሁለት ዓመት ሊሆናት ነው ። እጉቱ ሌላ ሚሽት እንዲያገባ ትፈልጋለች ። በዚህ ዕድሜው ምን በወጣው ! አይቀስስ ! አይመነኩስ ባይ ናት ።”

“ ግን እጉቲቱን ምን ብለው አማከሯት ? ”

“ወንድ የማያስጠጋ ዐይነ ጥላ ያስቸገራት እንዲት እጉቱ ነበረች ፣ ዐዋቂ ብንጠይቅ ምሽቱ የሞተችበት ካህን ይገፍላታል አለን አልኳታ! ወትሮውንም የወንድሟ ነገር ሲከነክናት ቆይቶ ናሮ ደስታውንም አልቻለችው ። ”

“እንዲት መጣልም እንደዚህ ያለው መላ እቱ ! ” በመገረም ራስዋን እያወዛወዘች .....

በዚያው ሰሞን ግን ፣ ጋረድና አክሊሉ የተጨዋወቱት ስለ አምባ ጊዮርጊሱ ምሥጢር ነበር ።

ከጋረድ ቤት ጠጅ እየኮመኮሙ በመጠጥ ጋይል ተኩራርቶ ፣ “ ራስ ታልኩት መቸ አነሰውና ” እያለ ከአገው ንጉሤ ጋር ስለሚያደርጉት ስምምነት ፣ ስለ ቴዎድሮስ ደብረ ታቦር ላይ መከተም ሲያወጉ ነገሩን በመኸል ያነግው አክሊሉ ነበር ።

“ ኧረ እንዲያው አንድ ነገር ሰምቸ ! ” አለ አክሊሉ መገረሙን ለማሳወቅ ዐይኑን ጨንቄር አድርጎ ።

“ ምን ? ”

“ የአምባ ጊዮርጊሱን አለታ መንክር ታውታቸዋለህ ?” ጋረድ በእሱታ ራሱን ነቀነቀ ። “ወዳጄ ናቸው ። ዛሬያ በቀደምለታ በጨዋታ